በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ፣ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በኩስሜ ብሔረሰብ

በ

ብሩክ ያሬድ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ሰኔ 2006

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በኩስሜ ብሔረሰብ

ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር የኤምኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ብሩክ ያሬድ

አማካሪ ዶክተር ፈቃደ አዘዘ

ሰኔ 2006

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣
የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና
ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በኩስሜ ብሔረሰብ

በ

ብሩክ ያሬድ

የፈተና ቦርድ አባላት

| ስም | ፊርማ |
|---|---|
| አማካሪ | |
| ፈቃደ አዘዘ(ዶ/ር) | --------------------- |
| የፈታኝ ስም | |
| አቶ ዓለሙ ካሣዬ | --------------------- |
| ዘላለም ተፈራ (ዶ/ር) | ---------------------- |

ሰኔ 2006

# ምስጋና

አማካሪዬ ዶክተር ፍቃዴ አዘዘ በመደበኛ ክፍለ ጊዜ ከእርሶ ዘንድ የመማር እድሉን ባላገኝም በዚህ የጥናት ወረቀት ሳቢያ ብዙ አስተምረውኛል፡፡ይህም የጥናት ወረቀት በእርሶ ያላሰለሰ ድጋፍ ባይቃና ኖሮ ከዚህ አይደርስምና ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ እህቴ ቤተልሄም ለእኔ እዚህ መድረስ ትልቁን ድርሻ ስለተወጣሽ አመሰግናለሁ ፡፡እናቴ አልማዝ ሙሉጌታ ሁሌም ስለምታደርጊልኝ ድጋፍ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡በጥናት ስራዬ ትልቁን ድርሻ የነበራችሁ የመስክ አጋሮቼ አቶ መንግስቱ ገኖና አቶ ዳንኤል ምክሬ አመሰግናለሁ፡፡ የደራሼ ወረዳ የስራ ኃላፊዎች ሁሉ ላደረጋችሁልኝ ድጋፍ ከልብ አመሰግናለሁ::

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ‹‹ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በኩሰሜ ብሔረሰብ›› በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡በጥናቱ የግጭት አፈታት ገፅታና የብሔረሰቡ አባላት እርስ በእርስና ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚያጋጥሟቸውን ግጭቶች ተጋጪዎቹ ወደ ሀገረሰባዊው የፍትህ ተቋም እንዲያመጡ የሚያደርጋቸው ምክንያቶችና የባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርአቱን አጠቃላይ ሂደት ለማወቅ ይቻል ዘንድ በተለያየ መልኩ ከተለያዩ የብሔረሰቡ ክፍሎች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

በመረጃ መሰብሰቢያ መንገድነት ጥቅም ላይ የዋሉት ቃለ መጠይቅ ፣ የቡድን ውይይትና ምልከታ ናቸው፡፡

የተገኘው መረጃ በገላጭ ተንታኝ (Descriptive Analysis) ስልት ተተንትኗል፡፡ በዚህም ብሔረሰቡ ከቀላል እስከ ከባድ ወንጀሎች መፍትሄ ለመስጠት የሚሄድበትን መንገድ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

በጥናቱ በኩስሜ ብሔረሰብ ዋነኛ የግጭት መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችም ተለይተዋል፡፡ከግጭቶቹም ዋና ዋና የሚባሉት ማለትም ድንበር መግፋት ፣ የቤተሰብ ጠብ ፣ ወንጀልና የቡድን ጠብ ተመርጠው ባህላዊው የእርቅ ስርአት እንዴት እንደሚፈታቸው ታይቷል፡፡

ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቱ ራሱን የቻለ  የስልጣን ተዋረድ እንዳለውም በጥናቱ ታይቷል፡፡ በብሔረሰቡ የግጭት አፈታት ሥርዓት ውስጥ ሴቶች ሚና ባይኖራቸውም ከሰውም ሆነ ተከሰው ሲቀርቡ ከመሸንጎያው /ከሞራው/ ራቅ ብለው ግን ጉዳያቸውን የማስረዳት መብት አላቸው፡፡


የባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ ከመደበኛ ፍርድ ቤት ጋር ተቀራርቦ የሚሰራ ነው፡፡ በተለይ የሐሰት አጣሪ በሚል በብሔረሰቡ የተቋቋመው 16 አባላት ያሉት ኮሚቴ መደበኛ ፍርድ ቤት በተሳሳተ መልኩ ውሳኔዎችን እንዳይወስን መረጃን በሚገባ በመሰብሰብ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በኩሰሜ ብሔረሰብ ዘንድ በተለይ ለግድያና ለብሔር ግጭት እርድ የእርቅ ሥነ ሥርዓት የመጨረሻው ስርዓት ነው፡፡ሌሎቹ ጉዳዮች ግን በካሳ ክፍያና በገንዘብ ቅጣት ብቻ እንደሚጠናቀቁ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቱ በትክክል ይፈርዳል ተብሎ ከመታመኑም በላይ ፍርዱን የማይቀበሉት ከብሔረሰቡ ስለሚገለሉ ተቀባይነቱ  የጎላ ነው፡፡


## የኢትዮጵያ ካርታ




## የደቡብ ክልል ካርታ



# የኩስሜ ብሔረሰብ መኖሪያን የሚያሳይ ካርታ




የኩስሜ መኖሪያ ጋቶ
ቀበሌ

## ማውጫ

ርዕስ ገፅ


ምስጋና ------------------------------------------------------------------------------------i
አጠቃሎ ---------------------------------------------------------------------------------ii
ካርታ -------------------------------------------------------------------------------------- iii
1.መግቢያ--------------------------------------------------------------------------------1
1.1. የጥናቱ አደረጃጀት-------------------------------------------------------------- 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት------------------------------------------------------2
1.3. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች -------------------------------------------------3
1.4. የጥናቱ ዓላማ----------------------------------------------------------------------- 4
1.4.1. ዝርዝር አላማዎች---------------------------------------------------------- 4
1.5. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች---------------------------------------------------- 4
1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ-------------------------------------------------------------------- 4
1.7. የጥናቱ ወሰን------------------------------------------------------------------------ 4
1.8. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ--------------------------------------------------------------5
1.9. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው---------------------8
2. የኩሰሜ ብሔረሰብ አካባቢያዊ ማህበራዊና ባህላዊ ዳራ--------------------- 10
2.1. የኩሰሜ ብሔረሰብ መኖርያ አካባቢ------------------------------------------ 10
2.2. የብሔረሰቡ የትመጣነትና ስያሜ----------------------------------------------10
2.3. የብሔረሰቡ የኢኮኖሚ መሰረት-------------------------------------------------12
2.4. የብሔረሰቡ ቋንቋና እምነት----------------------------------------------------- 13
2.5. ስም አወጣጥ ----------------------------------------------------------------------13
2.6. ጋብቻ(ሃሚታ)-----------------------------------------------------------------------14
2.7. ለቅሶ--------------------------------------------------------------------------------14
3. የፅንሰ ሀሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት------------------------------------------ 15
3.1. የግጭት ምንነትና ትወራዊ ቅኝት----------------------------------------------15
3.2. የግጭት አነሳሽ ምክንያቶችና ዓይነቶች ------------------------------------- 18
3.2.1የግጭት አነሳሽ ምክንያቶች---------------------------------------------- 18
3.2.2. የግጭት ዓይነቶች---------------------------------------------------------- 20
3.3. የግጭት አፈታት ዘዴዎች--------------------------------------------------------- 21
3.4.የተዛማጅ ጥናቶት ቅኝት---------------------------------------------------------- 22
4. ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩሰሜ ብሔረሰብ-----------------------27
4.1. የግጭት ምንነት በኩሰሜ ብሔረሰብ-------------------------------------------27
4.2.የግጭት ዓይነቶችና መንስኤዎቹ በኩሰሜ ብሔረሰብ----------------------- 27
4.2.1.የግጭት መንስኤዎች-------------------------------------------------------27
4.2.2.የግጭት ዓይነቶች----------------------------------------------------------29
4.2.2.1.**ድንበር መግፋት**-------------------------------------------------29
4.2.2.2. የቤተሰብ ጠብ-----------------------------------------------------30
4.2.2.3. ወንጀል --------------------------------------------------------------31

4.2.2.4. የቡድን ጠብ------------------------------------------------32
4.3.ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትና የአፈታት ሂደት በኩሰሜ ብሔረሰብ---33
4.3.1.ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት-------------------------------------- 33
4.3.2.ባህላዊ የግጭት አፈታት ሂደት በኩሰሜ ብሔረሰብ--------------- 36
4.3.2.1.ክስ (ሆለታ)--------------------------------------------------- 36
4.3.2.2.ማስረጃ------------------------------------------------------ 38
4.3.2.3.ሽማግሌ መጥራት--------------------------------------------38
4.3.2.4 የቅጣት አስተያየት----------------------------------------- 39
4.3.2.5.ብይን------------------------------------------------------- 39
4.3.2.6. ማዕቀብ(ዱፌና)-------------------------------------------- 40
4.3.2.7 ይቅርታ (ማርካ)-------------------------------------------41
4.4.ትዕምርቶች በኩስሜ ባህላዊ የእርቅ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ---------------- 43
4.4.1.ቅጠል---------------------------------------------------------------------43
4.4.2.እርድ--------------------------------------------------------------------- 43
4.5. ከመደበኛው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት ውጪ የሚታዩና የሚፈቱ የግጭትዓይነቶች ----------------------------------------------------------44
4.5.1.ግድያ---------------------------------------------------------------44
4.5.2.የብሔር ግጭት-----------------------------------------------------47
4.6.የኩሰሜ ባህላዊ የፍትህ ስርዓትና ሴቶች-------------------------------------49
5.ባህላዊና መደበኛ ፍርድ ቤት በኩሰሜ ብሔረሰብ-------------------------------51
5.1.ሀገረሰባዊ የፍትህ ስርዓት ከመደበኛው ጋር በንፅፅር ሲቃኝ -------------51
5.1.1. በኩሰሜ ብሔረሰብ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት----------------------- 51
5.1.2. ከጊዜና ከኢኮኖሚ አንፃር-------------------------------------------- 52
5.1.3. ትክክለኛ ፍርድን ከመስጠት አንፃር----------------------------------- 52
5.1.4. ዘላቂ እርቅን ከማስገኘት አንፃር-----------------------------------------53
5.2.ባህላዊና መደበኛው የፍትህ ተቋማት ያላቸው ግንኙነት--------------------- 55
5.2.1.ባህላዊና መደበኛው የፍትህ ተቋማት ተባብሮ ከመስራት አንፃር------ 55
5.2.2.ባህላዊው የፍትህ ስርዓት ለመደበኛው ፍርድ ቤት ብይን የሚያደርገው አስተዋፅኦ --------------------------------------------------- 55
6.ማጠቃለያና ይሁንታ---------------------------------------------------------------59
6.1.ማጠቃለያ-------------------------------------------------------------------- 59
6.2.ይሁንታ--------------------------------------------------------------------- 60
ዋቢ መፃሃፍት ------------------------------------------------------------------ 62
የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል
የመረጃ አቀባዮች መግለጫ ሰንጠረዥ
ስዕላዊ መግለጫዎች
ጥናቱ የተሰራበት የአማርኛ ቴምፕሌት

# 1. መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በስድስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ የጥናቱን ዓላማ፣ ጠቀሜታ፣ ወሰንና የአጠናን ዘዴን በተመለከተ ዝርዝር ማብራሪያዎች ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ ሁለት የጥናቱ ዋነኛ ትኩረት የሆነው ብሔረሰብ የት ቦታ ይኖራል፣ ስለየት መጣነቱ የሚነገሩ ጉዳዮች፣ የኢኮኖሚ መሰረቱ፣ እምነቱ፣ ቋንቋው፣ ስያሜውና ማህበራዊ ሁኔታውን በተመለከተ ዝርዝር ጉዳዮችን ቃኝቷል፡፡

ምዕራፍ ሶስት ግጭትን በተመለከተ የተሰጡ የምሁራን ብያኔዎች አካቷል፤ ስለ ግጭት መፍቻ ስርዓቶች የቀረቡ የተለያዩ አተያዮችን ለማስቃኘት ይሞክራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በባህላዊ ግጭት ዙርያ የተሰሩ መሰል ጥናቶችን በራሱ መስፈርት መርጦ ደካማና ጠንካራ ጎናቸውን ይፈትሻል፡፡

ምዕራፍ አራት የጥናቱ አበይት ክፍል ነው፡፡ ስለዚህም በሚጠናው ብሔረሰብ ውስጥ ስለ ግጭት የሚሰጠው ብያኔ፣በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የግጭት ዓይነቶችና የሚፈቱበትን መንገድ በዝርዝር ለማሳየት ይሞክራል፡፡ በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ግጭት ለመፍታት የሚመረጡ ሽማግሌዎች በምን መስፈርት ይመረጣሉ? የሚለውንም ይመለከታል፡፡ እንዲሁም ባህላዊው የፍትህ ስርአት ሁሉንም የብሔረሰብ ክፍሎች እኩል በማየት ረገድ ያለበትን ሁኔታ በዝርዝር ይተነትናል፡፡

ምዕራፍ አምስት ባህላዊ የግጭት አፈታት ከዘመናዊው ጋር ያለውን መደጋገፍ አልያም መቃረን ይመለከታል፡፡ የብሔረሰቡ አባላት በንፅፅር ሲታይ ከዘመናዊውና ከባህላዊው የቱን ይመርጣሉ?ለምን? የሚለውም ጉዳይ በዚህ ክፍል ምላሽ ያገኛል፡፡

ምዕራፍ ስድስት የኩሰሜ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት ስርዓትን ገምጋሞ ማጠቃልያና ይሁንታ ይሰጣል፡፡ እንዲህ ቢሆን ደግሞ ይበልጥ ቀጣይነቱን አስጠብቆ ይዘልቃል የሚሉ የአጥኚው አመለካከትም ከጥናቱ ጋር በተዛመደ መልኩ የቀረበበት ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን የጥናት ርዕስ ለመምረጥ ምክንያት የሆነኝ በስራ አጋጣሚ እጄ ገብቶ ለማንበብ የቻልኩት በደቡብ ክልል የብሔረሰቦች ምክር ቤት የባሕል ቋንቋ ታሪክና ቅርስ ተቋም በ2001 ዓ.ም የተዘጋጀ ‹‹የብሔረሰቦች ፕሮፋይል›› የተሰኘው መፅሐፍ ነው፡፡ በተለይ በመፅሀፉ ስለ ኩሰሜ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት የተፃፉት ሁለት አንቀፆች ናቸው፡፡

> የብሔረሰቡ ባህላዊ አስተዳደር በበላይነት የሚመራው በንጉሥ ሲሆን ከእርሱ ሥር አልጋሌ፣ አልማሌ፣ እግዴና ባደቱን የተሰኙ መንፈሳዊ መሪዎች ይገኛሉ፡፡ ንጉሱ መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ ሥራዎችን በበላይነት የመምራት ሥልጣን አለው፡፡ ንጉሱ ከማስተዳደር ሥራው ባሻገር በየዕለቱ የፀሎት ሥነ ሥርዓት ያከናውናል፡፡ ሕዝቡ የንጉሡ ፀሎት የአንበጣን መንጋ ያጠፋል፤ ሰብልን ከጥፋትና ከውድመት ይታደጋል ብሎ ስለሚያምን፣ ንጉሡ ይህ እንዳይከሠት በየዕለቱ ይፀልያል፡፡ ወንጀል ሲፈፀም መፍትሔ መስጠት የንጉሡ ድርሻ ነው፡፡ የግድያ ወንጀል ሲፈፀም ገዳይ ሮጦ ንጉስ ቤት ይገባል፡፡ ንጉሡ የገዳይንና የሟችን ወገን በማቀራረብ ያስታርቃል፡፡ በዚህ የዕርቅ ሂደት ከሌሎች ጋር በመሆን ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በገዳይ ወገን ላይ ጉማ (ካሣ) በመወሰን ፀበኞች ለበቀል እንዳይፈላለጉ ያደርጋል፡፡ በቤተሰብ ደረጃ የሚነሱ ግጭቶች መንስዔና ውጤታቸው በጎረቤት ሽማግሌዎች ይታያሉ እንጂ ወደ ንጉሡ አይደርሱም፡፡
>
> ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚከሠቱ ግጭቶች በቅድሚያ ከየብሔረሰቦቹ በተውጣጡ ታዋቂ ሽማግሌዎች እንዲታዩ ይደረጋል፡፡ ይህ ሣይሳካ ሲቀር ግን የየብሔረሰቦቹ የጎሣ መሪዎች በጉዳዩ ዙሪያ ከሽማግሌዎች ጋር በመሆን በጥልቀት መክረውበት አጥፊው ወገን ካሣ እንዲከፍል ያደርጋሉ፡፡ የህይወት መጥፋት ጉዳይ ከሆነ ገዳይና ሟች ለወደፊቱ በቂም በቀል እንዳይፈላለጉ ለማድረግ ፍየል በማረድ ደም የመርጨትና አጥንት የመከስከስ ባህላዊ ሥርዓት ይከናወናል፡፡ ባህላዊ

ሥርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሁለቱም ወገኖች የጥፋት አላማን ከማሰብ የሚገድባቸው እና እንዳያፈነግጡ እርግማን ተከናውኖ የዕርቅ ሥርዓቱ ይጠናቀቃል (የደ/ብ/ብ/ህ/ፕሮፋይል፣/2001/፣ ገፅ 197-198)፡፡

በእነዚህ ሁለት አንቀፆች ላይ ስለባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት የቀረበው ፅሁፍ ስለ ብሔረሰቡ የግጭት አፈታት የሰጠኝ ጥቂት መረጃ ከሁለት ነገር አንፃር ቢጠና ዝርዝር ማብራሪያ ይገኝበታል የሚል እምነት አሳደረብኝ፡፡ አንደኛው በመፅሃፉ የተገለፀው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት አሁን ሙሉ በሙሉ እየተተገበረ ነው ወይንስ ለውጥ አለው? የሚለውን በጥናት አረጋግጦ ክዋኔውንና ማህበራዊ ፋይዳውን በዝርዝር ያሳያል፡፡

ሁለተኛው ምን አልባት በመፅሃፉ ከተገለፀው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት የቀረ ካለ በምን ተተካ ለምንስ ቀረ የሚለውን በጥናቱ ለማሳየት በማሰብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኩሰሜ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት በዝርዝር ቢጠና በሌሎች እንዲታወቅ ይረዳል በሚል የብሔረሰቡን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት አጥንቼያለሁ፡፡

### 1.3.የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል፡-

1. የኩስሜ ብሔረሰብ እርስ በእርሳቸው እና ከአጎራባቾቻቸው ጋር የሚጋጩባቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
2. የኩስሜ ብሔረሰብ እርስ በእርሳቸው እና ከአጎራባቾቻቸው ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶችን እንዴት ይፈታሉ?
3. የኩስሜ ብሔረሰብ አባለት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ምን ይመስላል?
4. የብሔረሰቡ አባላት ከባህላዊና ከዘመናዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት የትኛውን ይመርጣሉ ? የሚሉ ጥያቄዎችን ይመልሳል፡፡

### 1.4.የጥናቱ ዋና ዓላማ

- ጥናቱ ዋነኛ አላማው የኩሰሜ ብሔረሰብ በተለያየ አጋጣሚ የሚከሰቱ የእርሰ በእርስ ግጭቶችንም ሆነ ከሌላ ማህበረሰብ ጋር የሚከሰቱ ግጭቶችን በምን አይነት ዘዴ እንደሚፈታቸው ማሳየት ነው፡፡

### 1.4.1.የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- ብሔረሰቡ እያንዳንዱ ግጭት ከመፈጠሩ ጀምሮ እስከ መጨረሻው እርቅ ድረስ የሚሄድበትን መንገድና የሚከተለውን ስርአት መግለፅ፡፡
- የባህላዊ ግጭት የመፍቻ ዘዴው በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ያሳያል፡፡
- ብሔረሰቡ ግጭቱን እንዲፈቱ የሚመርጣቸውን ሽማግሌዎች በምን መስፈርት ይመርጣል የሚለውን ይገልፃል፡፡
- ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርአቱ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን የተቀባይነት ያሳያል፡፡

### 1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ

- የኩሰሜ ብሔረሰብን አስመልክቶ ከዚህ በፊት በባህላዊ ግጭት አፈታት ስርአት ዙርያ የተካሄደ ጥናት ባለመኖሩ የብሔረሰቡን የግጭት አፈታት ስርአት ለማስተዋወቅና ሰንዶ ለማስቀመጥ ይረዳል፡፡
- የኩሰሜ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት ከዘመናዊው የፍትህ ስርአት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሳየት ያስችላል፡፡
- በኩሰሜ ብሔረሰብ ባህላዊ ግጭት አፈታት ዙሪያ ወደፊት ለሚሰሩ ምርምሮች መረጃ ይሰጣል፡፡

### 1.6.የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት የኩሰሜ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርአትን ማሳየት ነው፡፡የኩሰሜ ብሔረሰብ አባላት በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች በደረሼ ወረዳ በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች የሚገኙ ቢሆኑም ጥናቱ ግን የብሔረሰቡ አባላት

በዋናነት ተሰብስበው በሚኖሩበት ጋቶ በሚሰኘው ቀበሌ ላይ ባሉት ላይ ብቻ ትኩረቱን አድርጓል፡፡ ይህ ማለት በሌሎች የወረዳው አካባቢ የሚኖሩ የብሔረሰቡ አባላትን የጥናቱ አካል አያደርግም፡፡

በጥናቱ ሁሉንም የግጭት መንስኤዎችና የሚሰጣቸውን ባህላዊ መፍትሄ ለማሳየት አስቸጋሪ በመሆኑ በብሔረሰቡ ዘንድ በተደጋጋሚ የሚከሰቱትንና በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ጥፋት ተደርገው የሚወሰዱትን ማለትም ስርቆት፣የውርስ ጠብ፣የድንበር ግጭት፣ግድያና መሰል ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠር ግጭትና የአፈታት ስርአቱም የጥናቱ አካል ነው፡፡

## 1.7.የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ይህን ጥናት ለመሥራት በፎክሎር ጥናት የመስክ ምርምር ዘዴ እንደ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢ ዘዴ የሚያገለግሉትን ስልቶች ማለትም ቃለመጠይቅ፣ ስምምነታዊ ምልከታንና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን ዋነኛ ስልት አድርጌ ተጠቅሜያለሁ፡፡ (ፈቃደ፡ 1991፡90)፡፡

በመሆኑም በቃለ መጠይቅ ከብሔረሰቡ አባላት የተመረጡና በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ የጎላ ሚና ካላቸው ሽማግሌዎችና የጎሳ መሪዎች ጋር ስለ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርአቱ በቂ መረጃ ያስገኘ ቃለ ምልልስ አድርጌያለሁ፡፡ በዚህም መሰረት ከሽማግሌዎቹና ከጎሳ መሪዎቹ ጋር በነበረኝ ቆይታ የእርቅ ስነስርአቱ የሚከናወንበት ቦታ፣ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርአቱ እንዴት ይከናወናል፣ ሽማግሌ በምን መስፈርት ይመረጣል፣ ለየግጭት አይነቶቹ የሚከተሉት የተለየ የአፈታት ሂደት ምንድን ናቸው የሚሉትን ጉዳዮች በሚመለከት ዝርዝር መረጃ አግኝቻለሁ፡፡

የባህሉን ቀጣይ ሁኔታ ለማወቅ ከወጣቶች ጋር ቃለ ምልልስ አድርጌያለሁ፡፡ ሴቶች፣ የፍትህ አካላትና የቀበሌ አመራሮችም በቃለ ምልልሱ ተካተዋል፡፡ ከእነዚህ አካለት ጋር በነበረኝ ቃለ መጠይቅ ወጣቶቹ ስለ ባህላዊው የግጭት መፍቻ ስርአት ስላላቸው ግንዛቤ፣ ለሥርአቱ ስለሚሰጡት አትኩሮትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች

መረጃ አግኝቻለሁ፡፡ ከሴቶቹ ጋር በነበረኝ ቆይታም ባህላዊ የግጭት መፋቻ ሥርዓቱ ለእነርሱ የሰጠውን ቦታ ተቀብለውታል ወይ፣እኩል ያየናል የሚል አመለካከት አላቸው ወይ ስለሚለው ነገር በቂ መረጃ አግኝቻለሁ፡፡ዘመናዊ የፍትህ ስርአቱ ውስጥ ተሳታፊ ከሆኑት አካላት ጋር በነበረኝ ቆይታ ደግሞ ከባህላዊ ሥርዓቱ ጋር አብረው የሚሰሩበትን መንገድ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ሁሉም ቃለ ምልልስ በቴፕሪከርደር ተቀርጿል፡፡ ከሁሉም ጋር በነበረኝ ቆይታ የተጠቀምኩት ዝግና ክፍት ጥያቄዎችን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቀጥታ ስለምፈልገው ጉዳይ እንዲነግሩኝ በማሰብ ዝግ ጥያቄዎችን አብዝቻለሁ፡፡የግል አስተያታቸውን እንዲሰጡኝ ለፈለኩት ጉዳይ ደግሞ ክፍት ጥያቄዎችን ተጠቅሜያለሁ፡፡በአጠቃላይ በቃለ ምልልሱ 17ወንዶችና ሶስት ሴቶች ተሳታፊ ነበሩ፡፡የሴቶቹ ቁጥር ያነሰው በባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርአቱ ያላቸው ተሳትፎ ከመክሰስና ከመከሰስ ያለፈ ባለመሆኑ ነው፡፡

ከቃለ መጠይቁ በተጨማሪ ከዘጠኙ ቀጠናዎች በሁለቱ ቀጠናዎች የተከናወኑ የእርቅ ሥነ ስርዓቶች ከነተፈጥሯዊ መቼታቸው ማግኘት ተችሏል፡፡ ስለዚህም በሁለቱ መሸንጎያዎች (ሞራዎች) በመገኘት የባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቱ ክዋኔ ከመነሻው እስከ መድረሻው ምልከታ ተደርጓል፡፡የምልከታው አይነት ስምምነታዊ ነው፡፡ይህም ማለት የብሔረሰቡ አባላት እንደምመለከት አውቀው የተከናወነ ነው፡፡ ምልከታ ባካሄድኩበት ወቅት በአንደኛው ቀጠና አንድ ጉዳይ ብቻ ሲቀርብ በሁለተኛው ቀጠና ላይ በነበረ መሸንጎያ(ሞራ) ስድስት ጉዳዮች ቀርበው ዕልባት ሲሰጣቸው መመልከት ችያለሁ፡፡ ይህን የምልከታ ሂደት በቪዲዮ ካሜራ መቅረፅም ተችሏል፡፡ ሸንጎዎቹ በእኩል ሰአት የሚታዩ በመሆናቸው በሁለት የመቅረጫ መሳሪያ ለመጠቀም ተገድጃለሁ፡፡ በሁለቱም ቦታዎች በአንዴ ተገኝቼም ምልከታ ማድረግ ስለማልችል የአንዱን ሸንጎ አጀማመሩን የሁለተኛውን ደግሞ ሙሉ ሂደቱን ለመመልከት ችያለሁ፡፡ሆኖም ሙሉ በሙሉ በመቀረፁ በመረጃው ላይ ያመጣው ለውጥ የለም፡፡

በሁለቱም ሸንጎዎች የቀረቡት ጉዳዮች የቤተሰብና ጎረቤት ጠብ እንዲሁም ከንብረት ውድመት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በእነዚህ የግጭት መነሻነት የተካሄደው የእርቅ ስርአት ከመነሻው ጀምሮ ፍርድ አስኪሰጥ ድረስ ምን አይነት መንገድን ይከተላል የሚለውን ለማየት ችያለሁ፡፡ በዚህም ከሽማግሌዎቹ ጋር በነበረኝ ቃለ ምልልስ የተረዳሁት ነገር በተግባር ምን እንደሚመስል እንድመለከት አስችሎኛል፡፡

በሁለት ዘዴዎች የተሰበሰበውን መረጃ ይበልጥ ለማጎልበት ይረዳ ዘንድ አራት የተተኳሪ ቡድን ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ እነዚህም ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከጎሳ መሪዎች፣ ከሴቶችና ከወጣት ወንዶች ጋር የተደረጉ ናቸው፡፡ በተተኳሪ የቡድን ውይይቱ፣ በግል ተካሂዶ በነበረ ቃለ መጠይቅ ክፍተት ታይቶባቸው የነበሩ ጉዳዮች በጥያቄነት ተነስተው በየቡድኑ አባላት እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ የጎሳ መሪዎች (ስምንቱም) በቡድን ውይይቱ ተሳታፊ ሆነዋል።

የሽማግሌዎቹ ቡድን ሰባት አባላት ነበሩት። የሴቶቹ ቡድን ሲጀምር አምስት የነበረ ሲሆን ኋላ ላይ እስከ ዘጠኝ ድረስ አድጓል። የወጣቶቹ ቡድን ግን ሰባት አባላት ነበሩት። ይህ የቡድን ውይይት ሁሉም በፎቶ፣ ግሚሱ ደግሞ በቪዲዮ ተቀርጿል፡፡ ይሁን እንጂ ቀረፃው ተወያዮቹ ሀሳባቸውን ከመግለፅ ይልቅ በቪዲዩ ካሜራው ላይ ትኩረት በማድረጋቸው የቡድን ውይይቱን በስርአት ለመምራትና መረጃውን በሚገባ ለማግኘት ሲባል በፎቶ ብቻ እንዲያዝ ተደርጓል፡፡

በዚህ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ክፍተት ከታየበትና አደናጋሪ ከነበሩ ጉዳዮች በተጨማሪ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቱን በተመለከተ ከመነሻው አንስቶ ያለውን አጠቃላይ ሂደት በመደጋገም እንዲገልፁ ዕድል ተሰጥቷል፡፡

በዚህ መልኩ የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን በዋነኛነት የተጠቀምኩት ገላጭ የምርምር ዘዴ (Descriptive study) ነው፡፡ ይህም አላማዬ የብሔረሰቡን የግጭት አፈታት ስርዓት ማሳየት ስለሆነ ካሰብኩት ግብ አድርሶኛል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሳገኝም ስለ ግጭት አፈታት ስርአት ከመረጃ አቀባዮች የተሰጠኝን መረጃ ቃል በቃል በቀጥታ ጥቅስ ወስጃለሁ፡፡

## 1.8.በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው

በዚህ ጥናት ሂደት ሶስት ችግሮች አጋጥመዋል። እነሱም፡- የአካባቢ ርቀት፣ በጀት እና ቋንቋ ናቸው።

የጥናቱ ትኩረት የሆነው የኩሰሜ ብሔረሰብ የሚኖረው ከአዲስ አበባ 675 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው፡፡ ብሔረሰቡ የሚኖረው በዘጠኝ ቀጠናዎች በተከፋፈለ አንድ የገጠር ቀበሌ በመሆኑ ለመጤ እንግዳ ማረፊያ የሚሆን ሆቴል በፍፁም የለም፡፡ የመብራት አቅርቦትም በሰአት የተገደበ ነው፡፡ በመሆኑም ከብሔረሰቡ ጋር አብሮ ከመዋል ውጪ በቅርበት እዛው ተረጋግቶ ለማደር አስቸጋሪ ነበር፡፡ ከዚህ በፊት ወደ ብሔረሰቡ ለተመሳሳይ የጥናት ተግባር የመጡ አልያም በእንግዳነት በአካባቢው የቆዩ ሰዎች ባለመኖራቸውም ከአንዱ የብሔረሰቡ ተወላጅ ቤት ተጠግቶ ለመኖር የተደረገው ሙከራም አልተሳካም ፡፡ ምክንያቱ እንዲህ አይነቱን እንግዳን የማስተናገድ ልምድ ስላልነበረ ሙሉ ፍቃደኝነቱን አሳይቶ ለማስተናገድ የወሰነ ሰው አልነበረም፡፡ ስለዚህ በየቀኑ ከጊዶሌ የ17 ኪሎ ሜትር መንገድ በሞተር መመላለስ ግድ ነበር፡፡ በመፍትሄነት የተወሰደውም ተግባር ይሄው ነው። ዋና ማረፊያዬን በጊዶሌ ከተማ በማድረግ ጠዋትና ማታ የደራሼ ወረዳ በሰጠኝ ሞተርና እርሱ ለስራ ሲፈለግ ደግሞ በምከራየው ሞተር ወደ ብሔረሰቡ መኖርያ ጋቶ ቀበሌ መመላለስ።

ይህ የመፍትሄ እርምጃም ቢሆን ከችግር የፀዳ አልነበረም፡፡ ሞተር የመንዳትም ሆነ በሞተር የመጓዝ ልምድ አለመኖር ከመንገዱ ጠመዝማዛና አስቸጋሪ መሆን ጋር ተደማምሮ ጉዞውን ሁሌም በሰቀቀን የተሞላ አድርጎት ነበር፡፡

የበጀት ማነስም በዚህ የጥናት ሂደት ያጋጠመ ችግር ነው፡፡ዩኒቨርሲቲው ለዚህ ጥናት የመደበው በጀት ስድስት ሺህ ብር ብቻ በመሆኑ በዚህ የገንዘብ መጠን ጥናቱ የሚፈልጋቸውን መረጃዎች አሟልቶ መሰብሰብ አዳግቷል፡፡ የደራሼ ወረዳ አስተዳደር የሞተር ብስክሌት በመስጠት ቢተባበርም በቀይታዬ ሁሉ ነዳጅ መሙላት የኔ ድርሻ ነበር፡፡ ሞተሩ ለስራ ሲፈለግም ሌላ ሞተር መከራየት ግዴታዬ ነበር፡፡ ይህ ለሞተረኞች ከሚከፈለው ገንዘብ ለማደሪያና ለምግብ ከሚወጣው ወጪ

ጋር ሲደመር ስድስት ሺህ ብሩ ለጥናቱ ማከናወኛ የማይበቃ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የጎደለውን ወጪ በራሴ በመሸፈን ተገቢውን መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት አድርጌለሁ።

በቋንቋን ረገድም ያጋጠሙ ሁለት ችግሮች ነበሩ፡፡ አንደኛው የብሔረሰቡ አባላት በመጠኑም ቢሆን የአማርኛ ቋንቋ መቻላቸው የባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርአት እርከኖችን በኩስምኛ ከመናገር ይልቅ በአማርኛ አቻው ይጠሩት ነበር፡፡ በሂደትም ኩስምኛው ስለተዘነጋ የኩስምኛውን አቻ ቃል ማግኘት አስቸጋሪ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አማርኛ መቻላቸው የሚጠየቀውን ጥያቄ በሚገባ ለመረዳት እንዲችሉ ስላደረጋቸው በአንድ በኩል ጥቅም ነበረው፡፡ በሚገባ አማርኛ የማይችሉት ምላሻቸውን በኩስምኛ እንዲናገሩና በአስተርጓሚ እንዲተረጐም ለማድረግ ተችሏል፡፡ ከቋንቋ ጋር ተያይዞ ያጋጠመው ሁለተኛው ችግር የሸንጎ ስርአቱ የሚካሄደው ሙሉ በሙሉ በኩስምኛ ቋንቋ መሆኑና እያንዳንዱን ቃል ለማስተርጐም መሞከሩ ደግሞ በመሸንጎያው የሚካሄደውን ስርአት የሚያስተጓጉል ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡ ይህንንም የእርቅ ስርአቱ ከተካሄደ በኋላ የክሱ ነጥብና የተሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ በአስተርጓሚው ተጠቃሎ እንዲያቀርብ በማድረግ ለማስተካከል ተችሏል፡፡

# 2. የኩሰሜ ብሔረሰብ አካባቢያዊ ማህበራዊና ባህላዊ ዳራ

## 2.1. የኩሰሜ ብሔረሰብ መኖርያ አካባቢ

የኩሰሜ ብሔረሰብ የሚገኘው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሰገን ዞን በደራሼ ወረዳ በጋቶ ቀበሌ ነው፡፡

ቀበሌውን በደቡብና በምስራቅ ከኮንሶ በሰሜን ከደራሼ በምዕራብ ደግሞ ከማሾሌ ጋር ይዋሰናል፡፡

ዋነኛ የአስተዳደር ማዕከሉ የጋቶ ቀበሌ ነው፡፡ ቀበሌውን አቋርጦ የሚያልፈው እያንዳ ወንዝ ለሁለት ይከፍለዋል፡፡ ከወንዙ በስተቀኝ ያለው መንደር ኩሰሜ በመባል ሲጠራ በስተግራ ያለው ደግሞ ከሸሌ ይባላል፡፡

በከሸሌ መንደር ከኩሰሜዎች በተጨማሪ ከአጎራባች ቀበሌዎች መጥተው መኖር የጀመሩ የደራሼና የማሾሌ ብሔረሰብ ተወላጆች ይኖራሉ። በኩሰሜ መንደር ግን ሁሉም ለማለት በሚያስችል ደረጃ ነዋሪዎቹ ኩሰሜዎች ብቻ ናቸው፡፡

የጋቶ ቀበሌ የአየር ፀባይ ቆላማ ነው፡፡ የመሬት አቀማመጡም ተራራማ፣ ሜዳማና ሸለቆማ ነው፡፡ እንደ ማዕከላዊ እስታስቲክስ ባለስልጣን መረጃ በ1999 በተደረገ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የብሔረሰቡ ብዛት 7470 ደርሷል ፡፡

## 2.2. የብሔረሰቡ የትመጣነትና ስያሜ

ኩሰሜ ማለት በኩስምኛ እንብርት ማለት ነው፡ ከዋነኛ መረጃ አቀባዮቹ አንዱ ስለ ስሙ ትርጓሜ እንዲህ ይገልፃሉ፡፡

> ኩሰሜ ማለት ኩሰሜ የተሰየመበት ጉዳይ በመጀመሪያም እዛ አካባቢ ደረቅ ነበረ (በእጃቸው ወደ ሰሜን አቅጣጫ ወደ ደራሼ እያሳዩ) በአባቶቻችን ስንሰማ በዚያን ጊዜ የእህል ዘር በመጥፋቱ እዚህች አካባቢ ከገደሉ ወይም ከተራሮች ላይ የሚፈሰው ተፋሰስ እዚህ አካባቢ እህል ተገኘ፡፡ ዘር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ነው ስያሜ የተሰጠው ማለት ነው፡፡

እንብርት ነው እህል መገኛ ቦታ ነው ብለው እዚህ ነው የተገኘው ኩሰሜ ተብሎ ተሰይሟል (ክፍሌ ተዋኖ፣ጋቶ ቀበሌ፣መጋቢት 7፣ 45) ፡፡

የኩሰሜ ብሔረሰብ ከስምንት ጎሳዎች የተዋቀረ ነው፡፡ እነርሱም፡- ሰውደታ፣ ከረካይታ፣ ኤሻላይታ፣ አርገማይታ፣ የኩማሊታ፣ ኤለይታ፣ ትግሳይታ እና ማሌታ መሆናቸውንም ስማቸውን በዝርዝር በመጥቀስ ከዋና መረጃ አቀባዮቼ አንዱ አቶ ሉዳይዶ ጎጋ በጋቶ ጤና ጣቢያ ግቢ የካቲት 20 ባደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀውልኛል፡፡

የኩሰሜ ብሔረሰብ አሁን ወደሚኖርበት የጋቶ ቀበሌ በ1980 ዓመተ ምህረት በሰፈራ ምክንያት ከመምጣቱ በፊት በተለያዩ አካባቢዎች ኖሯል፡፡

> የኩሰሜ ብሔረሰብ ከቆላ ማሽሌ ልዩ ስሙ ‹ታላል› ከሚባል አካባቢ ተነስቶ ቢንጎ በሚባል አካባቢ ከሰፈረ በኋላ እንደገና ወደ መኩሉ ወደ ተባለ ቦታ ተንቀሳቀሰ፡፡ በዚያ የእርስ በእርስ ግጭት ሲፈጠር ማንዲና ናያ ተብሎ በሚጠራ ጉብታማ አካባቢ ሰፈረ፡፡ በዚህ ስፍራ ነባር ህዝቦች ስለነበሩ ከነኝህና ከታለስ አካባቢ ከተንቀሳቀሱ ህዝቦች ጋር በመደባለቁ የኩሰሜ ብሔረሰብ አጠቃላይ ስርወ ምንጭ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ብሔረሰቡ በጋብቻና በተለያዩ ሁኔታዎች ተቀላቅሎ ይኖርበት ከነበረው ማንዲያና ናያ ቀበሌዎች ወደ ጋቶ የተንቀሳቀሰው በሰፈራ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል (የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል (2001፣ 197) ፡፡

በመፅሀፉ የተገለፀው ጉዳይ እውነት ስለመሆኑ ከዋነኛ መረጃ አቀባዮቼ አንዱ አቶ ጌታቸው ዲምባ ያብራራሉ፡፡

> መጀመሪያ ላይ የደራሼ ልዩ ወረዳ በነበረ ሰዓትም የነበረው የኩሰሜ ብሔረሰብ አደረጃጀት አሁን ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ምንም ለውጥ የለውም፡፡ አስቀድሞ የደራሼ ልዩ ወረዳ ከመሆኑ በፊት በደርግ ጊዜ የነበረውና ከደርግ ጊዜ ከ1980 ዓ.ም በፊት የኩሰሜ ብሔረሰብ የሚባለው በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተበታትኖ የሚኖር ነበር፡፡ የተለያዩ ቀበሌያት ላይ፡፡ ለምሳሌ ያንጎ የሚባል ቀበሌ አለ፣ ማንደያ የሚባል ቦርዴ የሚባል ቀበሌ አለ ፣ሴራቱ የሚባል ቀበሌ አለ፣ ከሻሌ የሚባል ቀበሌ አለ፣ መንዝ የሚባል

ቀበሌም አለ፡፡ እነኚህ ሁሉ በተለያዩ ቦታዎች የሚኖሩበት ናቸው፡፡ መንዝ የሚባል ቦታ ላይ የሚኖሩት ኩሰሜዎች ብቻ አይደሉም፡፡ ከሰሙ እንደምትረዳው መንዜዎች አሉ፡፡ አማራዎች አሉ፡፡ እነርሱን ተጠግቶ ደግሞ የኩሰሜ ብሔረሰብ አብሮ ተጠግቶ ይኖራል፡፡ በኋላ በሂደት እነርሱ ሲለቁ ኩሰሜዎች እዛ ኖሩ፡፡ ሰፈሩ ግን መንዝ ሰፈር ተብሎ ይጠራል፡፡ ይሄ የሆነው እንግዲህ ከ1980 ዓ.ም በፊት ነው፡፡ 1980 ዓ.ም ላይ ደግሞ የመንደር ምስረታን እንትን በሚባልበት ጊዜ እነኝህ ሁሉ ቀበሌያት አሁን እንደ አንድ ቀበሌ የሚጠሩ ጋቶ ወደሚባል አካባቢ ህብረተሰቡ መጣና ከደርግ ውድቀት ኢህአዴግ እስካሁን እስካለበት ድረስ ሁሉም የብሔረሰቡ አባል በአንድ ቀበሌ ይኖራል ማለት ነው፡፡የአሁን አደረጃጀት ማለትም ከ1980 የተካሄደው አንድ ለማድረግ የተካሄደ የመንደር ምስረታ ነው (ጌታቸው ዲምባ፣ጊዶሌ፣የካቲት 17/2006 ፣ገፅ11) ፡፡

## 2.3. የብሔረሰቡ የኢኮኖሚ መሰረት

የኩሰሜ ብሔረሰብ በዋናነት የሚተዳደረው በግብርና ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንስሳትም ያረባል፡፡ ባህላዊ መስኖ በመጠቀምም በአመት ሁለቴ ያመርታሉ፡፡ ለዚህም መንደሩን አቋርጦ የሚያልፈው የእያንዳ ወንዝ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ጥቂት በዕደ ጥበብ ሙያ በመሰማራት ኑሯቸውን የሚደጉሙ የብሔረሰቡ አባላት የነበሩ ቢሆንም አሁን አሁን ቀንሰዋል፡፡ ስለዚህም ብዙዎቹ የኩስሜ ሴቶች የሚለብሱትን ኦሎላ (ባህላዊ ቀሚስ) ከአጎራባቻቸው ከኮንሶ ብሄር ገዝተው ነው፡፡ የእደ ጥበብ ሰራተኞቹ መመናመንን በተመለከተ መረጃ አቀባዪ ምክንያት ነው ያሉትን ይገልፃሉ፡፡

> የሴቶች ባህላዊ ልብሱ በኛ /አሎላ/ ይባላል፡፡ የኩሰሜውን ባህላዊ ልብስ የሚሰሩ አሉ፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ነበር፡፡ አሁን እየለበሱ ያሉት የኩሰሜውን ሳይሆን የኮንሶውን ነው፡፡ ሁለት መሰረታዊ የሆነ ምክንያቶች አሉት አንደኛ አሁን ያለው ጄኔሬሽን ሞደርን ወደ መሆን ደረጀ እየደረሰ ስለሆነ ከኮንሶውም ከራሱም ከኩሰሜውም ታላቆ የከተማ ልብስ መልበስ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ጉርድ አሰፍቶ መልበስ ይፈልጋል፡፡ ቀሚስ ኖርማል ቀሚስ አሰፍቶ መልበስ ስለሚፈልግ ይሄ ሞደርናይዜሽን ተከትሎ የሚሆን ነገር ነው፡፡ ሁለተኛ የራሱን የሚሰሩ ሰዎች ከህዝቡ መካከል የሉም፡፡ አብዛኛው ህብረተሰብ ወደ ግብርና ስለዞረ ይሄን የሚሠራ ሰው ስለሌለ አሁንም ያንን ስራ የሚሰሩ ሰዎች የኮንሶውን ነው የሚሰሩት፡፡ እና በገበያ ላይ አዋጪው ከኩሰሜው ይልቅ የኮንሶው ስለሆነ ከአዋጭነቱ ጋር ተያይዞ

ሰው የኮንሶውን ባህላዊ ልብስ በደንብ ስለሚሰራው እነርሱም ደግሞ ገበያ ላይ እርሱን ስለሚያገኙት ነው የሚጠቀሙት እና የሚሰሩት ሰዎች ብዙም አሁን የሉም የኩሰሜ ተወላጆች ሆነው ይሄንን የሚሰሩት የለም (ጌታቸው ዲምባ፣ጊዶሌ፣የካቲት 17/2006 ፣ገፅ11)፡፡

መረጃ አቀባዬ የለም ይበሉ እንጂ እኔ በቆይታዬ በከሸሌ መንደር ካሉ ሰዎች አንዱ በቤቱ ደጃፍ የሸማ ስራ ሲሰራ ተመልክቻለሁ፡፡ በመሆኑም የእደ ጥበብ ሙያተኞች የለም ከሚለው ይልቅ ቁጥራቸው ቀንሷል የሚለው ያግባባል፡፡

### 2.4. የብሔረሰቡ ቋንቋና እምነት

የኩሰሜ ብሔረሰብ የአፍ መፍቻ ቋንቋው ‹‹ኩስምኛ›› ይሰኛል፡፡ ከኩሻዊ የቋንቋ ቤተሰብ ይመደባል፡፡ ከኮንሶና ከኦሮምኛ ቋንቋዎች ጋር ይቀራረባል፡፡ የብሔረሰቡ አባላትም ከኩስምኛ ቋንቋ በተጨማሪ ኦሮምኛ ኮንሶኛና ደራሼኛ ይናገራሉ፡፡ እስካሁን ቋንቋው ከንግግር በዘለለ የትምህርትና የስራ ቋንቋ ሆኖ ማገልገል አልቻለም፡፡ በመሆኑም የስራና የትምህርት ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡

በእምነት ረገድ ኩስሜዎች የፕሮቴስታንትና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡

## 2.5.ስም አወጣጥ

ኩሰሜዎች ስም ሲያወጡ ሁለት ዓይነት መንገዶችን ይከተላሉ፡፡ የመጀመሪያው ህፃኑ/ኗ የተወለደበትን ቀን ወራትን የሚጠቁሙ የስም አወጣጥን የተከተለ ነው፡፡ ሁለተኛው አዋላጅ አልያም እናትና አባት በአቅራቢያቸው የሰሙትን ስም ለልጃቸው የሚሰጡት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በብሔረሰቡ መካከል ሙሉ በሙሉ የአማርኛ ስያሜ ያላቸው ሰዎች አሉ፡፡ የኩስምኛ ስም ያላቸው ግን ቋንቋውን ለሚያውቀው ሰው ስያሜያቸውን በማየት ልጆቹ መቼ ቀን እና በምን ወቅት እንደተወለዱ ማወቅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ“ሃሙሳ ማለት ሃሙስ የተወለደ ማለት ነው፤ቦና ማለት በድርቅ ዘመን የተወለደ ማለት ነው፤ካፒዎ ማለት በመሀር ጊዜ

የተወለደ ማለት ነው፤ ለአያ ማለት በርሃብ ዘመን የተወለደ ማለት ነው፤ (Tadele,2006፡72 )፡፡

## 2.6.ጋብቻ (ሃሚታ)

በኩሰሜ ብሔረሰብ ጋብቻ የሚፈፀመው በአራት አይነት መንገድ ነው፡፡ እነርሱም ካሰታ፣ ሸዊታ፣ ቲና እና ዳሃለ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ካሰታ የሚባለው የጋብቻ ዓይነት ወንዱ ልቡ የፈቀደለትን ሴት በጓደኛው አማካኝነት አግባብቶ መስማማቷን ሲያውቅ ወደ ቤተሰቦቿ ሽማግሌ ልኮ የሚያገባበት ሂደት ነው፡፡

ሸዊታ የተሰኘው የጋብቻ ዓይነት ሴቷና ወንዱ በመፈቃቀድ በድብቅ ከተጋቡ በኋላ ለቤተሰብ የሚያሳውቁበት ነው፡፡ ይህ ግን ሙሽራው እንዲቀጣ ያደርገዋል፡፡

ቲና በጠለፋ የሚፈፀም የጋብቻ ዓይነት ነው፡፡ ዳሃለ የውርስ ጋብቻ የምንለው ዓይነት ሲሆን ታላቅ ወንድም አግብቶ ሳይወልድ ቢሞት ታናሹ ሚስቱን ይወርሳል፡፡ የሚወለዱት ልጆች ግን የሚጠሩት በታላቁ ስም ነው፡፡ ከወለደ ግን የውርስ ጋብቻ የለም (Tadele, 2006፡58) ፡፡

## 2.7.ለቅሶ

ኩሰሜዎች ለቅሶ የሚያበዙት ህፃን ልጅና ወጣት ሲሞት ነው፡፡ ትልቅ ሰው ሲሞት ግን ዕድሜውን ጠግቦ ነው የሞተው ብለው ስለሚያምኑ ተሰብስበው ይጨፍራሉ እንጂ የመረረ ለቅሶ አያደርጉም፡፡ የጎሳ መሪ ከሞተ እስከ አንድ አመት ድረስ ሳይቀበር አንጀቱ ወጥቶ እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ በአመቱ ግን ተተኪው ተገልፆ በጭፈራ ይቀበራል፡፡ ይህ ስርዓት ግን አሁን ከሚከተሉት እምነት ጋር በተያያዘ እየቀረ ነው፡፡ ሆኖም ትልቅ ሰው ሲሞት መጨፈር አሁንም ያለ ባህል ነው፡፡ ለመስክ በወጣሁበት የመጀመሪያ ቀን የ65 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሴት አዛውንት የብሔረሰቡ አባል ሞተው ሲጨፈር አይቻለሁ፡፡

# 3. የፅንሰ ሀሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የግጭት ጥናት ምሁራንን በማጣቀስ ከግጭት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጉዳዮች ይዳሰሱበታል፡፡ በተለይ ምሁራን የግጭትን ምንነት በተመለከተ የሚያነሷቸውን ነጥቦች የግጭት ዓይነቶችና አነሳሽ ምክንያቶች፣ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚዳሰሱ ሲሆን የቀደም ጥናቶች ቅኝትም በዚሁ ምዕራፍ ተካቷል፡፡

## 3.1. የግጭት ምንነትና ትወራዊ ቅኝት

ግጭት ምንድን ነው? መነሻውስ ? ግጭት እንዴት ይፈታል? ወዘተ ለሚሉ ጥያቄዎች ቀጥተኛና ወጥ መልስ መስጠት ቢያዳግትም በተለያዩ የግጭት መስኮች ጥናት የሰሩ ምሁራንን አጣቅሶ ስለ ጉዳዩ ማብራርያ መስጠት ይቻላል፡፡

የግጭት ምንነትን በተመለከተ በቀጥታ ወደ ባለሙያዎች ሙያዊ ብያኔ ከመግባት በፊት መዝገበ ቃላዊ ብያኔውን ማስቀደሙ የተሻለ ነው፡፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ግጭትን ‹‹ጥል ጠብ›› በሚል ይተረጉመዋል (1993፣ 510) የ Leslu አማርኛ እንግሊዝኛ አውዳዊ መዝገበ ቃል ግጭትን ‹‹ትግል፣ ልዩነት፣ አለመስማማት፣ ጠብ፣ ውጊያ፣ ግጭት፣ አለመግባባት›› Lesiu (1973፣ 226) ፡፡ በማለት ይበይነዋል፡፡

በተለያዩ የጥናት መስኮች ምርምር ያካሄዱ ምሁራንም ከራሳቸው የምርምር ውጤት በመነሳት የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ አንዳንድ ምሁራን (Schmid 2000; Fisher,1990፡12)ግጭትን ከፍላጎት አለመሳካትና ከአቅርቦት እጥረት ጋር ያያይዙታል፡፡(Schmid 2000፡22) ‹‹ግጭት ከፍ ያለ ቦታ ወይንም ደረጃ ለማግኘት በሚድረግ ጥረትና በሀብት ውሱንነት የሚከሰት አለመግባባት ነው፡፡›› ሲሉ (Fisher 1990፡12) ‹‹ግጭት ግንኙነት ባላቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቡድኖች መካከል በሚኖር የዓላማ ልዩነት አንዱ የሌላኛው የበላይ ለመሆን ሲሻ የሚፈጠር ተቃርኗዊ ስሜት ነው›› በማለት ይበይነዋል፡፡

Deutch and Coleman, (2000; 32) ደግሞ ከላይ በSchmid እና Fisher ከተሰጠውና የግጭት መንስኤ ላይ ካተኮረው ብያኔ ወጣ ብለው ሰለ ውጤቱ የሚያትት ገለፃ ይሰጣሉ፡፡ ‹‹ግጭትን የምንቆጣጠርበት ወይንም የምንፈታበት መንገድ ውጤቱን ገንቢ ወይንም አፍራሽ ሚያ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡›› በማለት፡፡

ይህ Deutch and Coleman, (2000; 32) የሰጡት ብያኔ ግጭትን በሰው ልጅ መካከል በሚፈጠር ማህበራዊ ግንኙነት መከሰቱ አይቀሬ ቢሆንም ወደ አንዳች መልካም ግብ ማምጣት እንደሚቻልም ያመለከተ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በመዝገበ ቃላቱ የተሰጠው ፍቺ (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም 1993፣ 510፣ 1973፣ 226) ጉዳዩን ከጥፋት ጋር ብቻ በማቆረኘት አንዱን ፅንፈ ብቻ መያዙን ያሳያል፡፡

ይህ አገለለፅ ይበልጥ ትክክል የሚሆነው coser (1956፡26) ግጭት በሰው ልጆች ማህበራዊ ግንኙነት ላይ ዘርፈ ብዙ አዎንታዊ ጎን እንዳለው በመግለፅ የዘረዘራቸውን የሚከተሉትን ጥቅሞች ስንመለከት ነው፡፡

- ❖ ግጭት ማንነትን ለመገንባትና ራስን ሆኖ ለመገኘት አስተዋፅኦ የጎላ ነው፡፡ ግጭት ግለሰቦች ወይንም ቡድኖች ማንነታቸውን በዙሪያቸው ካሉ ሌሎች ነገሮች ለይተው እንዲመለከቱ ያደርጋል፡፡
- ❖ ግጭት ሰዎች ህብረትን እንዲፈጥሩ ያደርጋል፡፡ ግጭቶች ግንኙነትን እንደሚያጠነክሩ ሁሉ በጠላትነት የሚተያዩ ቡድኖችን ወይንም ግለሰቦችን ወደ አንድ የጋራ ግብ እንዲመጡና ግባ ቸውን እንዲያሳኩ በማድረግ በመካከላቸው የተፈጠረውን ስጋት ለመፍታት ይቻላል፡፡

ስለዚህ Deutch እና Coleman (2000፣ 32) የሚሉትን ግጭት በራሱ ጠቃሚም ጎጅም አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ እርሱን የምንፈታበትና የምንቆጣጠርበት ዘዴ ጎጂና ጠቃሚነቱን ይወስናል የሚለው ሀሳብ ተገቢነት ሚዛን ይደፋል፡፡

Lambert እና Myers የተባሉ ምሁራንም ይህን ሀሳብ በማጠናከር ግጭቶችንግጭቶችን ገንቢና አፍራሽ የሚያስብሉ ነጥቦችን ይገልፃሉ፡፡

> Conflict is destructive when: The conflict prevents or stops people from working, the dispute hurts or relationship and there are un controlled emotions and conflict is constructive when: opens people up to new ideas, develops common goals and builds a strong relationship (Lambert and Myers, 1999: 44)

ይህ አይነቱ የመስኩ ምሁራን ገለፃ የሚያሳየው ነገር በግለሰቦችም ሆነ በቡድኖች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች መፈታት እንዳለባቸውና ሲፈቱም አዎንታዊ ጎን እንዲኖራቸው ጥረት ሊደረግ እንደሚገባ ነው፡፡

ግጭቶችን በአዎንታዊ ጎን በመፈታትና ዘላቂ እርቅን ከመፍጠር አንፃር ደግሞ ባህላዊ የፍትህ ተቋም ከመደበኛው የፍትህ ተቋም የተሻለ እንደሆነ የሚገልፁ ምሁራን አሉ፡፡ Bendeman (2007; 137) ከእነዚህ አንዱ ነው፡፡ ጉዳዩ በእርቅ ስለሚያለቅ ወደ ቀድሞ ሰላማዊ ግንኙነት ለመመለስ ቀላል ነው በማለት፡፡

> Alternative dispute resolution is often regarded as better option than the conventional mechanism, because of lower cost, greater speed involved and as optional of presenting a more successful and sustainable solution (Bendeman, 2007, 137)

ከ Bendeman ገለፃ ለመዳት እንደሚቻለው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስልቶችን ከዘመናዊው ጋር በንፅፅር ሲታዩ የተሻለ ከሚያደርጋቸው ጉዳይ ጊዜና ወጪን መቀነሳቸው ቢሆንም ዋናው ጉዳይ ግን በዘላቂነት ችግሮቹን ፈተው ወደ ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች ዳግም ተመልሰው ወደ ሰላማዊ ህይወት እንዲመለሱ የማድረግ አቅማቸው ነው፡፡ ስለዚህ ዘላቂ መፍትሄ መስጠት መቻላቸው ተመራጭነታቸውን ያጎለዋል፡፡

## 3.2. የግጭት አነሳሽ ምክንያቶችና ዓይነቶች

ለግጭት ይህ ነው የሚባል ቁርጥ ያለ አነሳሽ ምክንያት ማስቀመጥም ሆነ በዓይነት ከፋፍሎ ማጥናት አስቸጋሪ ቢሆንም ምሁራን ግን የተለያዩ ጉዳዮችን በማንፀሪያነት በማየት ስለ አነሳሽ ምክንያቱም ሆነ ስለ ዓይነቶቹ የሰጡትን ማብራሪያ በዚህ ክፍለ እናያለን፡፡

### 3.2.1. የግጭት አነሳሽ ምክንያቶች

የብዙ ግጭት መነሻ ምክንያት በትክክል ይሄ ነው ብሎ መናገር አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ግጭቶች በአንድ ጊዜ በሚፈጠር ሁነት ብቻ የሚመጡ ሳይሆኑ የበርካታ ችግሮች ድምር ውጤት ናቸው፡፡ በአንድ ቡድን ወይም ማህበረሰብ ውስጥ ያለ የሀሳብና የፍላጐት ተቃርኖ ድንገት ምክንየት ሲያገኝ ፈንድቶ በመውጣት ሁለቱን አካላት ወደ ለየለት ግጭት እንዲያመሩ ምክንያት ይሆናል Katz የተባሉት ምሁር ይህንን ከግምት በማስገባት ግጭት በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ማለትም በኢኮኖሚ ፣ በእሴት እና በስልጣን እንደሚከሰቱ ይገልፃሉ (Katz፣ 1965፣ 110) ፡፡

**ኢኮኖሚያዊ ግጭት** (Economic Conflict) ፡- የግጭት መነሻ ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ነው ስንል ቡድኖች ወይም ግለሰቦች የተፈጥሮ ሀብት ውሱንነት ሲያጋጥማቸው አንዳቸው ከአንዳቸው የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያደርጉት ጥረት ወደ ግጭት እንዲገቡ ምክንያት ይሆናቸዋል ማለት ነው፡፡ ሁለቱ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ያላቸው ፍላጎት እየናረ ሲመጣ ይህን ፍላጐት ለማሳካት ፉክክር ውስጥ ስለሚገቡ መጨረሻቸው ግጭት ይሆናል፡፡

**የእሴት ግጭት** (Value Conflict):-እነዚህ የግጭት መነሻ ምክንያቶች በሰው ልጆች የአኗኗር ዘይቤ ፣ የርዕዮተ ዓለም ምርጫና ፍላጐት መቃረን ማለትም የኑሮ መርህና እምነት መለያየት የሚፈጥሯቸው ናቸው፡፡ ይህም ማለት የእነርሱ ስለህይወት ያለ አመለካከትና እምነት ከሌላው ጋር አልጣጣም ሲል አልያም

የሌሎችን የአኗኗር ዘይቤ በግድ እንዲከተሉ ጫና ሲደርስባቸው ይህ አይነቱ ግጭት ይፈጠራል፡፡

**የስልጣን ግጭት** (Power Conflict)፡- ይህ የግጭት መነሻ የሚፈጠረው አንድ ቡድን ወይም ግለሰብ በሌላኛው ቡድን ወይመ ግለሰብ ላይ የበላይ ለመሆን ተፅኖ ሲያሳርፍ ነው፡፡ አንዱ ወገን በሌላኛው ላይ የበላይ ለመሆን የሚያደርገው ጥረት ሁሌም የግጭት መንስኤ ነው፡፡ ተፅኖ የደረሰባቸው ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች የተነጠቁትን የሀይል ሚዛን ወደ ራሳቸው ለማስመለስ ጥረት ማድረጋቸው ስለማይቀርም የስልጣን ሽኩቻው አይቀሬ ይሆናል፡፡ ይህ ግጭት እልባት የሚያገኘው አንዱ ወገን ተሸናፊነቱን ተቀብሎ የሌለኛውን ወገን የበላይነት ሲያፀድቅ ነው፡፡ ይህ የግጭት መንስኤ በግለሰቦች፣ በቡድኖች ወይም በሀገር ደረጃ ሊፈጠር ይችላል፡፡

እነዚህ የግጭት ምክንያቶች በተናጥል ለአንድ ግጭት ምክንያት የሚሆኑበት አጋጣሚ የኖራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሶስቱ አልያም ሁለቱ ምክንያቶች ለአንድ ግጭት ምክንያት የሚሆኑበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡

በዋናነት የግጭት ምክንያቶች ተብለው እነዚህ ተጠቀሱ እንጂ በተግባቦት ሂደት በሚፈጠር አለመጣጣም ሳቢያም የሚፈጠሩ ግጭቶች ይኖራሉ፡፡ ሁሉም ሰው አንድን ነገር በራሱ አመለካከት ብቻ አጥሮ ሲተረጉም ተግባቦት ይቀንሳል፡፡ ይህ ደግሞ ለግጭት ምክንያት ይሆናል፡፡

### 3.2.2. የግጭት ዓይነቶች

የግጭት ዓይነቱ የተለያየ ቢሆንም Fisher ግን ቀደም ሲል ስለግጭት ብያኔ ሲሰጡ ባስቀመጡበት መልክ በግጭቱ በሚሳተፉ አካላት ልክ ዓይነቶቹን ከፋፍለው አስቀምጠዋል፡፡ ክፍፍሉ ከግለሰብ ጀምሮ እያደገ በመሄድ ድንበር ተሻጋሪ ወደሆኑ አለም ዓቀፍ ጉዳዮች  ይደርሳል (Fisher1990፡48) ፡፡ ከዚህ አንፃር በሶስት ዋና

ዋና ክፍሎች ማለትም ግለሰባዊ፣ቡድናዊና ዓለም አቀፋዊ በሚል ይከፍሏቸዋል፡፡ እነርሱም፡-

**ግለሰባዊ ግጭት** (Interpersonal conflict) ፡- ይህ የግጭት ዓይነት የሚፈጠረው ሁለት ሰዎች በፍላጎት ፣ በዓላማ ፣ በአቀራረብ በተግባቦት ማጣጣም ሲያቅታቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ልዩነታቸውን ለማጥበብና የዓላማ ልዩነታቸውን አቻችለው ማስኬድ ከቻሉ በመካከላቸው ያለው ተቃርኖ ይቀንሳል፡፡ እንዲየውም Fisher የተግባቦት አቅምን በትምህርት ማበልፀግ እንዲህ አይነቱን ግጭት ለማስቀረት መፍትሄ ነው ይላሉ፡፡

ቡድናዊ ግጭት (Intergroup conflict)፡- ይህ የግጭት ዓይነት አንድ አይነት አመለካከት ባህልና ዝርያ ባላቸው ሰዎች የተፈጠረ ቡድን በተመሳሳይ ከተፈጠረ ሌላ ቡድን ጋር የሚያደርጉትን ግጭትን ያጠቃልላል፡፡ ይህ አንድ ቡድን በሌላኛው ላይ የበላይ ለመሆን ሲሻ፣ ሲያገልና ሲንቅም የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው፡፡ መገለልና ንቀት የደረሰበት ቡድን ይህን የበታችነት ስሜት አምኖ ሳይቀበል ሲቀር ተቃርኖው የከፋ ይሆናል ፡፡ በአቅም ውሱንነት አልያም በተለያዩ አመለካከቶች ሳቢያ ዝቅተኛነቱን አምኖ ሲቀበል ግን ግጭቱ ዘላቂ መፍትሄ ባይኖረውም ይረግባል፡፡

**አለማቀፋዊ ግጭት** (International conflict) ፡- እነዚህ ግጭቶች በአለምአቀፍ ደረጃ የሚታዩ ሲሆን በሀገራት መካከል የሚከሰቱ ናቸው፡፡ ምክንያታቸው እንደየሁኔታው የተለያዩ ቢሆም አንድ ሀገር በሌላኛው ሀገር ላይ የሚከፈተው ጦርነትና ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ ዋነኛ መገለጫዎቹ ናቸው፡፡

## 3.3. የግጭት አፈታት ዘዴዎች

በግጭት አፈታት ላይ የተለያዩ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ግጭት የሚፈታባቸውን ስልቶች በየራሳቸው መንገድ ያስቀምጣሉ፡፡ ቀደም ሲል ለግጭት ብያኔ ከሰጡት

ምሁራን Deutsch እና Coleman ሀሳብ ስንመለከት ግጭት መፈጠሩ ያለ ቢሆንም የሚፈታበት መንገድ ገንቢ አልያም አፍራሽ ሊያደርገው እንደሚችል ያስቀምጣሉ፡፡

በቡድኖችም ሆነ በግለሰቦች መካከል የሚፈጠሩ ግጭት ወደ ከፋ ጥፋት ከማምራቱ በፊት የተለያዩ እልባት የሚሰጥባቸው መንገዶች እንዳሉ Imobighe የተባሉ ምሁን ይገልፃሉ፡፡ እንደ Imboighe (2003:5) ገለፃ ዋና ዋና የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚባሉት ድርድር ሽምግልና እና ዳኝነት ናቸው፡፡

**ድርድር** **/Negotiation/፡-** ድርድር በግለሰብ፣ በቡድን፣ በብሄርና በሀገር መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ከሚያገለግሉ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዘዴው የሁለቱ ተቃራኒ ወገኖችን ፍላጐት ይሻል፡፡ይህም ማለት ተቀራርቦ ለመነጋገርና ልዩነታቸውን በውይይት ለመፍታት መፈለግ ይኖርባቸዋል ምክንያቱም ሁለቱም ወገኖች ይሁነኝ ብለው መርጠው ወደ ድርድር ከልገቡ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም አብዛኛውን ጊዜ ሁለቱን አካላት አቀራርቦ ለድርድር ዝግጁ የሚያደርግ ሶስተኛ ወገን ያስፈልገዋል ሂደቱም በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

**ሽምግልና** **(Mediation)** ፡- ሽምግልና ከግጭት መፍቻ ዘዴዎች አንዱ ሲሆን የሁለቱም ወገኖች ይሁንታ የተቸረው አካል ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚጓዝበት መንገድ ነው፡፡

በዚህ የግጭት መፍቻ ስልት ሽምጋይ ሆኖ የሚቀርበው አካል ሶስተኛ ወገን ቢሆንም የመጨረሻው የእርቅ ውሳኔ የሚተላለፈው በሁለቱ አካላት የጋራ ስምምነት ነው፡፡

ይህን የግጭት አፈታት ስልት ከድርድር የሚለየው በሁለቱ ጠበኞች መካከል ገብቶ የማስታረቅ ስራ የሚሰራው ሽማግሌ ሁለቱን አግባብቶ ወደ ቀድሞው ሁኔታቸው ለመመለስ እስከመጨረሻው ድረስ የሚሄድ መሆኑ ነው፡፡ ድርድር ከአንዱ ወገን እንቢታ ሲሰማ ይቋረጣል፡፡ ሽምግልናን ውጤታማ የሚያደርገው ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት ለሽምጋዩ የሚሰጡት ክብርና እውቅና ነው፡፡ በሁለቱም ወገን ይሁንታ ካላገኘና ቃሉንም ለማክበር ዝግጁነት ከሌለ እርቁ ዘላቂ አይሆንም፡፡

**ዳኝነት** (Arbitration) ፡- ይህ ከላይ ከቀረቡት የግጭት ስልቶች የሚለየው ሶስተኛው ወገን ለግጭቱ እልባት ይሆናል የሚለውን ውሳኔ የመስጠት ህጋዊ አቅም ያለው መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም ሁለቱን ወገኖች በአንድ ላይ አወያይቶ ጥፋተኛ የተባለውን አካል ለይቶ ወደ ነበሩበት ሰላማዊ ጊዜ የሚመልስ ውሳኔ ያስተላልፋል አጥፍቷል በተባለው ላይም ቅጣት ያስተላልፋል ፡፡ ዳኝነት ከሌሎቹ የሚለየው የጠበኞቹን ይሁንታ ሳይፈልግ ጉዳዩን ማየቱና ህግን ተከትሎ ውሳኔ የመስጠት አቅም ያለው በመሆኑ ነው፡፡

## 3.4. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ምልከታዬ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንትቲትዩት እና በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ቤተ መፃህፍት ካታሎግ ውስጥ የተቀመጡ 26 የሚደርሱ በተለያዩ ብሔረሰቦች ላይ የተሰሩ የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናቶችን አይቻለሁ፡፡ ሆኖም ከኔ ጥናት ጋር የበለጠ ቅርበት ያላቸውና በደቡብ ክልል ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ዙሪያ የተሰሩት ጥናቶች ላይ በማተኮር በዓላማ ተኮር የመምረጫ ስልት ከየዓመተ ምህረቱ አንድ አንድ በመምረጥ በአራት የጥናት ወረቀቶች ላይ ቅኝት ተደርጓል፡፡

በዚህም ከ1998 ጀምሮ እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ለሁለተኛ ዲግሪ ማማያ የተፃፉ አራት ስራዎች በ1998፣ 1999 ፣ 2004 እና 2005 ላይ ተመርጠዋል፡፡የተመረጡትም በድንገቴ መረጣ(random sampling) ነው፡፡ በመሃል 2000 እስከ 2003 ያሉ ት ዓመታት ከላይ በተጠቀሰው ክፍለ ትምህርት ውስጥ ባህላዊ ግጭትን የተመለከተ ጥናት ስላልተሰረባቸው ተዘለዋል፡፡

ከየዓመቱ አንድ አንድ የመምረጡ ዋነኛ ዓላማ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓትን አስመልክተው የተሰሩ የሁለተኛ ዲግሪ ማማያ ጽሑፎች ከዓመት ዓመት የተለየ መንገድ ተከትለው ይሆን? ምን አዲስ ነገር ታይቶባቸዋል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ሊሆን የሚችል አንዳች ነገር ይኖራቸው

ይሆናል በሚል ነው፡፡ ሆኖም በተከታይነት በዝርዝር የሚገልፅ ቢሆንም የተለየ የጥናት አደረጃጀት የተከተሉና አዲስ መንገድ ያስተዋወቁ የጥናት ስራዎች እኔ ባየኋቸው ውስጥ አልተገኘም፡፡

በቅኝቱ የታዩት የጥናት ስራዎች የወንድወሰን (1998)፣ የአብርሃም (1999) የአንዱአለም (2004) የተመሰገን (2005) ናቸው፡፡

ቅኝቱ በጥናቶቹ መረጃ አሰባሰብና አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በእነዚህ ክፍሎች በጥናቱ የታዩ ጠንካራና ደካማ፣ ጐኖች ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳሰሎና ልዩነትንም ለማየት ተሞክሯል፡፡

የወንድወሰን አመላቸው በ1998 ‹‹የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ የግጭት አፈታትና አስተዳደር ስርዓት›› በሚል ርዕስ የሰራው ጥናት ቅኝት ከተደረገባቸው ስራዎች የመጀመሪያው ነው፡፡

ይህ የጥናት ወረቀት በፎክሎር ጥናት መረጃ ለማሰባሰብ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባቸዋል ተብለው በምሁራን የሚጠቀሙትን መረጃ የመሰብሰቢያ ስልቶች ተጠቅሟል፡፡ የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግም የሰባት ቤት ጉራጌ ብሔረሰብ ስለ ግጭት ካለው አመለካከት አንስቶ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በጎሳ መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት እንዴት እንደሚፈቱ አሳይቷል፡፡ይህም በጥንካሬ የሚገለፅ ነው፡፡

ከጥናቱ ዋነኛ ጭብጥ ጋር የሚገናኙ ጥናቶችን በአፍሪካዊ ሆነ በኢትዮጵያ የተሰሩትን ለመግለፅ ያደረገው ሙከራም ከበጎ ጐኖቹ የሚደመር ነው፡፡

ብሔረሰቡ የግጭት አፈታት ሂደት ላይ የሚጠቀማቸውን ተረቶችና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይሆነኝ ብሎ መሰብሰቡ ተገቢ ሆኖ ሳለ በግጭት የመፍታት ሂደት ያላቸውን ሚና አለማሳየቱ ግን በድክመትነት የሚጠቀስ ነው፡፡

በሁለተኛነት ጥናት የተከለሰው ስራ አብርሃም (1999) ‹ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሔረሰብ›› በሚል ርዕሰ የቀረበው ነው፡፡ ይህ ጥናት ከአደረጃጀት

አንፃር በመግቢያው ላይ ስህተት ፈጥሯል፡፡ ይህም በመግቢያው ስለ ግጭት ከአፈ ታሪክ ጀምሮ በኢትዮጵያ ያለውን አስተሳሰብ ይተነትናል፡፡ እንዲሁም ከዘመናዊው ይልቅ በባህላዊው ደንብና ስርዓት መዳኘት መልካም መሆኑን ይገልፃል፡፡ ይህን ርዕሰ ጉዳይ ባነሰባት የመግቢያ ፅሁፉ ላይ ምንም ዓይነት ንኡስ ርዕሰ ሳይከፈት ደግሞ በዚያው በመቀጠል ስለጥናቱ አደረጃጀት ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ይህ ተነጣጥሎ አለማቅረቡ እንዳለ ሆኖ ገና በመግቢያው ላይ የተከሰተ በመሆኑ ደግሞ ስለ ጥናቱ ያለን አስተያየት ያዛባል፡፡

ይሁን እንጂ ወደ ጥናቱ በጥልቀት ሲገባ ጥናቱ በመረጃ አሰባሰብ ዘዴውም ሆነ የተነሳበትን ዓላማ በመግለፅ ረገድ የጎላ ክፍተት አይታይበትም፡፡

ግጭትን በተመለከተ በምሁራን የተሰጠ ብያኔን የሲዳማ ብሔረሰብ የተለያዩ ግጭትቶችን የማፈታበትን መንገድ በሚገባ አሳይቷል፡፡ በተለይ ብሔረሰቡ ከሌላ ብሔረሰብ ጋር የሚፈጠር ግጭትን እንዴት ይፈታል ለሚለው ጉዳይ ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል፡፡

እርሱም እንደ የወንድወሰን ሁሉ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ ግጭትን በመፍታት ሂደት ውስጥ ያላቸውን ሚና አያሳይም እንጂ በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ ብሔረሰቡ ጥቅም ላይ ያውላቸዋል ያላቸውን ተረትና ምሳሌያዊ አነጋገሮች በሚገባ ሰንዷል፡፡

በሶስተኛነት ቅኝት የተደረገበት አንዱ አለም በ2004 የሰራው ‹‹ባህላዊ የግጭት አፈታት በመአኒት ብሔረሰብ›› በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት ነው፡፡ ይህ የጥናት ወረቀት ስለሚያጠናው ብሔረሰብ ዝርዝር መረጃ በመስጠት እኔ ካየኋቸው ስራዎች የተለየ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

በተለየ ስለ ብሔረሰቡ አመጣጥ ፣ የጋብቻና የለቅሶ ስርዓቶችን ትኩረት ሰጥቶ ለማስተዋወቅ ያደረገው ሙከራ ከሌሎቹ ይለየዋል፡፡ እንዲህ ማድረጉም ሌሎቹ አጥኚዎች እያንዳንዱን ርዕሰ ጉዳይ እንደዋነኛ የጥናት ርዕሰ ወስደው ዝርዝር ጥናት እንዲያደርጉበት መነሻ ይሆናል፡፡

ይሁን እንጂ በድክመትነት የሚጠቀሱ ጉዳዮችም አሉት፡፡ ከእነዚህ አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴውን ሲገልፅ እነዚህን ተጠቅሜያለሁ ከማለት ባለፈ በዝርዝር ይህንን ለዚህ ተግባር ተጠቅሜያለሁ በዚህም ይህን ውጤት አግኝቻለሁ የሚል ግልፅ መረጃ አልሰጠም፡፡

የተሰበሰቡትን መረጃዎች በገላጭ በትንተና ስልትና በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ እንደሚመረመር ተናግሮ ነገር ግን በጥናቱ ውስጥ አንዱን በቻ ማለትም ገላጭ የትንተና ስልትን ብቻ ሲጠቀም እናየዋለን፡፡

በአራተኛነት ቅኝት የተደረገበት የተመስገን በ2005 "ረጋማጋ ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት በማረቆ ብሔረሰብ" የሚል ርዕስ የተሰራው ስራ ነው፡፡ ይህ ስራ በጥናት አደረጃጀቱም ሆነ በአቀራራረቡ ካየኋቸው ጥናቶች በተሻለ ግልፅ አቀራረብን ይዟል፡፡ ከሶስቱም ስራዎች በተለየ ነገረ ጉዳዩን የሚያይበትን የትወራ ማዕቀፍ ይህ ነው ብሎ ለይቶ አስቀምጧል፡፡

የምርምር ጥያቄዎችን ማስቀመጡ በመግቢያው ስለፎክሎር ምንነት በምሁራን የተሰጡ ብያኔዎችን ማንሳቱም በጠንካራ ጎን የሚነሳ ነው፡፡

በዚህ ስራ ላይ በድክመት የሚነሳው ነጥብ አስቀድሞ ጥሬ መረጃዬን እተነትንበታለሁ ያለውን የትወራ ማዕቀፍ በትንተና ወቅት ሲጠቀምበት አለመታየቱ ነው፡፡ ይህም ትወራው ከጥናቱ ተነጥሎ ብቻውን እንዲቀር አድርጎታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተቃኙት አራት ጥናቶች በየጥናት አካባቢያቸው ያሉትን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት አሰራር፣ አወቃቀር ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማብራራት በተቋማት የሚተገበሩ የግጭት አፈታት ሂደቶችን በመግለፅ፣ የግጭት ዓይነቶቹንና መነሻ ምክንያቶችን በማሳየት ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡

ሆኖም አራቱም ጥናቶች የተሰሩባቸው ብሔረሰቦች ከእኔ ጋር ሲነፃፀሩ በህዝብ ብዛትና በሚኖሩበት ቦታ የቆዳ ስፋት የበለጡ መሆናቸው የባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት መዋቅሩን የበዛ ስላደረገው ከእኔ ጥናት እንዲለዩ አድርጓቸዋል፡፡

ተጨማሪ ፍቺ የሚፈልጉ ትዕምርቶችን ለይቶ በማብራራትም የአኔ ጥናት የተለይቷል፡፡

# 4.ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩሰሜ ብሔረሰብ

## 4.1. የግጭት ምንነት በኩሰሜ ብሔረሰብ

ኩሰሜዎች ስለ ግጭት የሚሰጡት ብያኔ በየዕለቱ ከሚያጋጥማቸው የግጭት ዓይነት ጋር የተዛመደ ነው፡፡ ከዋነኛ መረጃ አቀባዮች አንዱ የሰባ ዓመት አዛውንት ሉዳይዶ ጉጋ እንደሚሉት ግጭት ማህበረሰቡ ተገቢ አይደለም የሚለውን ጉዳይ መፈፀምና የሰውን ነገር የራስ ለማድረግ የሚደረግ ጥረት ነው፡፡"በእኛ መካከል መተሳሰብ አለ ሆኖም አንዳንድ ሰው የሰውን ንብረት ይወስዳል፣ ከብቶቹ ከሰው እርሻ ያገባል ያለተራ የመስኖ ውሃ ይጠቀማል እና በዚህ ምክንያት ጠብ ይፈጠራል" (ሉዳይደ ጉጋ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣የካቲት 20/2006፣ 19) ፡፡

ሌላው መረጃ አቀባዬ አቶ ጌታቸው ዲምባ "ግጭት የራስ ያልሆነን በመመኘትና ማህበረሰቡ ተገቢ አይደለም የሚለውን በመፈፀም የሚመጣ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግጭት የንብረት መውደም ምንጭ ፣የሰላም ጠር ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመፈናቀል ምክንያት የሚሆን ነው፡፡"ተብሎ እንደ ሚታሰብ ነው የነገሩኝ፡፡ በተለይ ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠር ግጭት በ1985 ተከስቶ ብዙ ውድመት ስላስከተለባቸው ኩስሜዎች ዋነኛ የጥፋት ምንጭ አድርገው ይወስዱታል ፡፡ በምንም አጋጣሚ ግጭት ሲከሰት ውድመት ሳያስከትል በባህላዊው የእርቅ ሰርአት እንዲፈታ የሚያደርጉትም ለዚሁ ነው፡፡

## 4.2.የግጭት ዓይነቶችና መንስኤዎቹ በኩሰሜ ብሔረሰብ

### 4.2.1.የግጭት መንስኤዎች

በኩሰሜ ብሔረሰብ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ግጭቶች መነሻቸው ኢኮኖሚያዊ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ዋነኛ መተዳደሪያቸው ግብርና በመሆኑ የእርሻ ቦታን ለማስፋት በሚደረግ ጥረት ድንበር መግፋት ተደጋጋሞ ይከሰታል፡፡ የመስኖ ውሃን ያለተራ መጠቀምም ዋነኛ የግጭት መንስኤ ነው፡፡ ይህ የተፈጥሮ ሀብት ውሱንነት የሚያመጣው ግጭት ብሔረሰቡን እርስ በእርስ ከማጋጨት አልፎ ከአጎራባች

ብሔረሰቦች ጋርም የግጭት መነሻ ምክንያት ይሆናል፡፡ ከዋነኛ መረጃ አቀባዮቹ አንዱ በብሔረሰቡ በተደጋጋሚ ስለሚከሰቱ ግጭቶች መንስኤ ሲገልፁ ‹‹አንደኛው ድንበር ላይ ነው ግጭቶች እየበዙ ያሉት ሁለተኛ ደግሞ በዚህ ግጦሽ ለከብቶች ሣር ሰፈሩ ሁሉ በእርሻ ተይዟል ሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ይሄ የመስኖ›› (ተፈሪ ታደሰ ፣በተጠያቂው መኖሪያ ቤት ፣የካቲት 15/2006 ፣ 9) ፡፡የግጭት መንስኤ ናቸው ተብ ለው የተነሱትን ሶስቱንም ጉዳዮች ስናይ ከተፈጥሮ ሀብት ውሱንነት ጋር ይዛመዳሉ፡፡ከዚህ በተጨማሪ እንደ ላይኞቹ ተደጋግመው የሚከሰቱ ባይሆኑም በሀሳብ አለመግባባትና በሰው ንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ ሳቢያ የሚከሰቱ አነስተኛ ግጭቶች አሉ፡፡ የግጭት አይነቶቹን በዝርዝር ከማየታችን በፊት በኩስሜ ብሔረሰብ ከግጭት መፍታት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን እናብራራ፡፡

ሞራ(መሸንጎያ)፡- ሞራ ማለት በቀጥታ ወደ አማርኛ ሲመለስ መሸንጎያ ወይም የፍርድ አደባባይ ማለት ነው፡፡ በየቀጠናው እና በየጎጡ ይገኛል፡፡ ዙሪያውን በድንጋይ የተካበ ሲሆን መሃሉ ላይ እንደጥላ የሚያገለግል ዛፍ አለ፡፡ ከዕርቅ ስነስርአት ውጭ ጎልማሶችና ሽማግሌዎች ገበጣ ይጫወቱበታል፡፡ ሙሉ ሁኔታውን ከታችየቀረበውምስልያስረዳል፡፡



ፎቶ 1፡- በአንድ መንደር ውስጥ ያለ ሞራ ምስል፡፡

በየመንደሩ ካሉት ከእነዚህ አይነቶቹ ሞራዎች በመጠኑ ሰፋ ያለ አንድ ሞራ አለ፡፡ ይህ ሞራ ቆራኦኛ(የኦኛ ዛፍ) በመባል ይጠራል፡፡ስያሜውን ያገኘው በሞራው መካከል ያለውን ዛፍ በተከለው ኦኛ በተባለው ሰው ስም ነው፡፡ የቀበሌው ህዝብ ሁሉ ሊመክርበት የሚገባ ጉዳይ ሲኖር ስብሰባ የሚካሄድበት ስፍራ ነው፡፡

አባ ዲባ(ዳኛ) ይህ በህረተሰቡ የሚመረጥ የባህላዊ እርቅ ስርአቱ መሪ ነው በማህበረሰቡ ውስጥ ስላለው ሚና ከመረጃ አቀባቹ አንዱ አቶ ሉዳይዶ ገልጸውልኛል፡፡

> "አባ ዲባ ማለት አጠቃላይ ህዝቡን ሰላም የሚጠበቅና ህዝቡን የሚያስተዳድር የሚያስታርቅ ማለት ነው፡፡ በአካባቢው ያለውን ባህል እየጠበቀ የሚያኖር ማለት ነው፡፡ አባ ዲባ የማይነካው ሁለት ነገር አለ ህገ መንግስቱን መናድ የለበትም ሃይማኖትን መናድ የለበትም፡፡ ከመንግስት የህገ መንግስቱን የበላይነት የሃይማኖትን እኩልነት አሰጠብቆ የሚኖር ማለት ነው፤ በዚህ ነው አባዲባ የሚለው ነው የአካባቢውን ሰላም የሚጠብቅና ህብረተሰቡን አስተሳስሮ የሚያኖር ነው፡፡" (ሉዳይደ ጉጋ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣የካቲት 20/2006 ፣ 19)

የኩስሜ ብሔረሰብ ተጠቃሎ በሚኖርበት በጋቶ ቀበሌ አንድ ዋና አባዲባ አለ፡፡ በቀበሌው ባሉ በዘጠኙም ቀየታ ወይንም ቀጠናዎች ደግሞ ንኡስ አባ ዲባዎች አሉ፡፡ተግባራቸው አንድ ነው ፡፡ዋናው አባዲባ የሚያያቸው ከፍ ያሉ እና ሁሉም የብሔረሰቡ አባል በጋራ ሊወስንባቸው ይገባል የሚባሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## 4.2.2.የግጭት ዓይነቶች

### 4.2.2.1.ድንበር መግፋት

ስለግጭት ዓይነቶች ስናነሳ ከመንስኤያቸው ጋር የጎላ ቁርኝት አላቸው፡፡የኩሰሜ ብሔረሰብ መኖሪያው የሆነው የጋቶ ቀበሌ አብዛኛው ክፍሉ ተራራማ ነው፡፡በዚህ የተነሳ ለእርሻ ምቹ የሆነው የመሬት መጠን አነስተኛ ነው፡፡ይህ ለእርሻ ምቹ የሆነ መሬት አነስተኛ መሆን በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ የተሻለውን መሬት የራስ የማድረግ ፍላጎት እንዲጎላ አድርጓል፡፡ ሰለዚህም ተደጋግመው ከሚነሱት ጠቦች

የጎላ ቦታውን የሚይዘው ከድንበር መግፋት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች ናቸው፡፡ ከዋና መረጃ አቀባዮቹ አንዱ አቶ ተፈሪ ታደሰ ቀድሞ ድንበር መግፋት በህብረተሰቡ ውስጥ የነበረው አመለካከት የከፋ በመሆኑ ድንበር በገፉ ሰዎች ምክንያትም ዝናብ አይዘንብም ተብሎ ይታሰብ ስለነበረ ድንበር መግፋት የተለመደ ወንጀል አልነበረም፡፡ አሁን ግን ሁሉም የብሔሩ አባል የፕሮቴስታንት አልያም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በመሆኑና የቀድሞውን አመለካከት በመተው ችግሩ ተደጋግሞ እንደሚከሰት ይናገራል፡፡

> በፊት ድንበር ገፍተህ ማስረጃ ቢያረጋግጥብህ ድንበር ከመግፋትህ የተነሳ ህዝቡ አንድ አመኔታ አለው ድንበር የገፉት ሰዎች ምክንያት ዝናብ አይዘንብም ይላሉ አባቶች በባህሉ መሰረት ዝናብ አይዘንብም ስለሚሉ ድንበር የገፋ ሰው ፍየል ሰጥቶ በድንበሩ ላይ ፍየል ይታረዳል ድንበር ስለገፋ ማለት ነው ፡፡ይቅር እንዲባል የሀጢያት ስርየት ማለት ነው ስ፡፡ለዚህ በአባቶች ወግና ስርዓት ጊዜ ጥብቅ ነው፡፡ ዛሬ ግን ይሄ ነገር ከቀረ በኋላ ሰው እየተደፋፈረ ድንበር በብዛት ይገፋል (ተፈሪ ታደሰ ፣በተጠያቂው መኖሪያ ቤት ፣የካቲት 15/2006 ፣ 9) ፡፡

የጋቶ ቀበሌ መደበኛ ፍርድ ቤት የዳኛ ረዳት የሆነችው ባዩሽ አንባየም ተደጋግሞ እኛ ጋር የሚመጣው በእርሻ ቦታ በድንበር ይገባኛል መገፋፋት ነው ትላለች፡፡“እኛ ጋር የሚመጣው በተለይ በጋቶ ቀበሌ እርሻ መሬት ክርክር ላይ ነው በድንበር ነው የሚጣሉት”(ባዩሽ አምባዬ፣ቀበሌው ፍትህ ጽ/ቤት፣የካቲት 22/2006፣38) ፡፡ ከሁለቱ መረጃ አቀባዮች እንደምንረዳው ድንበር መግፋት በኩሰሜ ብሔረሰብ ዋነኛ የግጭት መንስኤ ነው፡፡

#### 4.2.2.2. የቤተሰብ ጠብ

የቤተሰብ ጠብ በልጆችና በወላጆች መካከል በትዳር አጋሮች መካከል የሚፈጠሩ ከዕለት አለመግባባቶች አንስቶ እስከ ከረረ ጠብ የሚደርሱትን ያካትታል፡፡ ብዙውን

ጊዜ እንደዚህ ያሉ የጠብ ዓይነቶች ዘወትር የሚከሰቱ ባይሆንም በተከሰቱ ወቅት ግን በየቀጠናው ባለ ሞራ (መሸንጎያ) ዕልባት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ቤተሰባዊ ግጭቶች ናቸው ተብለው በዚያው እንዲቀሩ አይደረግም፡፡ በቀጠና ዘጠኝ ሞራ በነበረኝ ምልከታ አንድ የቀጠናው ነዋሪ ከአባቱ ጋር ተጣልቶ ክስ ሲቀርብበት ተመልክቻለሁ፡፡ ተከሳሹ ክስ የቀረበበት በአባቱ ነው፡፡ ሊመታኝ ሞክሯል በንዴትም የራሱን ተንቀሳቃሽ ስልክ ሰብሯል በሚል፡፡ ሞራውም ማስረጃ ካሰባሰበ በኋላ በ600 ብር ቀጥቶታል።

### 4.2.2.3. ወንጀል

በኩሰሜ ብሔረሰብ ዘንድ ድብደባና ግድያ የመሳሰሉትን ወንጀሎች ደረቅ ወንጀል በመባል ይጠራሉ፡፡ እነዚህ የወንጀል ዓይነቶች በብሔረሰቡ ዘንድ ተደጋግመው የሚከሰቱ አይደሉም። ይሁን እንጂ ሲከሰቱ ድብደባና የመግደል ሙከራ ከሆነ በባህላዊው ሸንጎ (ሞራ) እንዲታይ ሲደረግ አሁን አሁን ግን ግድያን የተመለከቱ ጉዳዮችን መረጃውን አጣርቶ ለዘመናዊ ፍርድ ቤት ከማቅረብና ሁለት ወገኖች ለበቀል እንዳይፈላለጉ ከማድረግ የዘለለ ሚና ባህላዊው ሸንጎ የለውም፡፡ይህንንም ያነጋገርኳቸው የሀገር ሽማግሌዎች ይገልጻሉ፡፡

> እኛ ማስታረቅ የምንችለው ተወግቶ በህይወት የተረፉ ከሆነ ነው፡፡ ይሄ ሰውን የወጋው ግለሰብ እሱ ታስሮ ቤተሰቡ እዚህ ለይ እንደሆነ ሰውየው የተወጋበት ቤተሰብ ሽማግሌ ይላክበታል ፡፡ሽማግሌ ወደዚያ ከተላከ የመታረቅ ስሜት ያላቸው እንደሆነ የተጎዳው አካል ይዳንልን፡፡ እስቲ መጀመሪያ ከሆስፒታልም ይምጣ፡፡ ወደዚህ ወደ ቤት ከመጣ በኋላ ሶስት ወር አራት ወር እስቲ እንይ፡፡ የእርሱን ደህንነት ጤናማ መሆኑን እናረጋግጥ፡፡ እንደዛ ብለው ወደ ሽማግሌ ይኬድና ሁለተኛው ቀጠሮ እስከሚያደርስ ሁለተኛው ቀጠሮ ሲደርስ ሽማግሌዎች ይሄዳሉ፡፡ሀሳቡን የሚያቀርብ ከሆነ እንግዲህ መታረቅ ያለበት ካሰዎች መከፈል ያለበት እርሱ ስራ ያጣው፣ በህክምና የፈጀው፣ ለቀለቡ የፈጀውን እነዚህን ያቀርባሉ፡፡በእነዚህ ካሳዎች ላይ ድርድር ያደርጋሉ፡፡ይሄን ድርድር ካደረጉና ለሰውየው ከከፈሉ በኋላ እንደገና ድጋሚ ሄዶ ደህንነቱ ሰላማዊ ጤነኛ መሆኑ በራጅ ይታይ ይረጋገጥ፡፡የአካባቢ ሽማግሌዎችና ጎሳ መሪዎች ብቻ ሳይሆን የተበዳይ ቤተሰብ የረሳቸውን የጎሳ መሪ ዋና ጎሳ መሪ

ያመጣሉ፡፡ይሄም በዳይ ቤተሰብ የራሳቸውን ዋና ጎሳ መሪ ያመጣሉ፡፡ የዚያን ቀን ሁለቱ የጎሳ መሪዎች ከመጡ ይሄ የመጨረሻ እርቅ ፍፃሜ ይሆናል። ሁሉንም ነገር ለመጨረስ በዚያን ቀን ካሳውንም ሁሉ ነገር ለመጨረስ ይወስናሉ እዛ አንድ ትልክ የፍየል ሙክት ይመጣል፡፡

ፍየሉ የታረዳ ዕለት እዛ ይሄ የልጅ የፈሰሰው ደም አሁን ከዛሬ ጀምሮ አጥበናል፡፡ ከዛ በፊት እንግዲህ የተጓዳዱ ለታ አንዱ የዘኛውን ጎሳ እህል አይበላም ጨቃ አይጠጣም ወደ እነዚያ ቤትም አይሄድም፡፡ ግን የዚያን ቀን ከዚህኛው የበዳይ ቤተሰብ ከወጋው ቤት ጨቃ ያመጣል ፡፡ከዚያኛው ተበዳይ ቤተስብም ጨቃ ያመጣል ፡፡እዚያን ቀን በቃ ጨቃውን ስጋውን በጋራ ይበላሉ፡፡ ጨቃውን በጋራ ይጠጣሉ ፡፡አንድ ይሆናሉ የዚያን ቀን እርቀ ሰላሙ ይሄ የተወጋው አካል በዚህ መልክ እርቀ ሰላም ይደረጋል፡፡ የመጨረሻ ሁለተኛ ቂም ያባቃል ነገር አያነሱም ተሰርዟል ይሄው ነው (ፈይሳ ቀዊቶ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣ የካቲት 20/2006 ፣34) ፡፡

### 4.2.2.4.የቡድን ጠብ

በኩሰሜ ብሔረሰብ እርስ በእርስ ድንበር በመገፋፋት በተደጋጋሚ ከሚከሰተው ጠብ ቀጥሎ በዛ ብሎ የሚከሰተው የጠብ ዓይነት በእነርሱና ከአጎራባቾቻቸው አንዱ በሆነው በኮንሶ ብሔረሰብ ዓባላት መካከል የሚፈጠር ጠብ ነው፡፡ ይህ ጠብ ሲከሰት ለብዙዎች ሞት ምክንየት እንደሚሆን ይገለፃል፡፡ በ1987 አካባቢ ተከስቶ በነበረ በዚህ ዓይነቱ ግጭት ከሁለቱም በኩል ብዙ ሰው ከተጎዳ በኋላ በባህላዊ የእርቅ ስነ ስርዓት ጉዳዩ እልባት ማግኘቱን መረጃ አቀባዮቹ ይናገራሉ፡፡

እኔ በራሴ የዚህ አካባቢ ነዋሪ ነኝ፡፡ የሀገር ሽማግሌ፤ የቡድን ግጭት እስከዛሬ ያየሁት ጎሳ ለጎሳ ተጋጮ የሚባለ ነገር አላየሁም፡፡ ከሌለ አጎራባች ቀበሌያት ጋር ግጭት ግን አሌ ፡፡ይሄ የአጎረባች ቀበሌያት ግጭት አንድ ድንበር ነው፡፡ በጉልበት ሴትን ልጅ ጠልፎ የራስ ሚስት ማድረግ ፣መንገድ ላይ ሰውን መግደል ፣መንግድ ላይ ሰውን መዝረፍ ፣በእንደዚህ ዓይነት ወንጀሎች ግጭት ይነሳል ፡፡ይሄ ግጭት ከተነሳ ብዙ ነፍስ ይጠፋል ብዙ የህዝብ ንብረትም ይጠፋል የቤት መቃጠል ይኖራል፡፡ እንግዲህ የዚህ ባህል እርቅ አፈታት እንደኩስሜ ባህል እንዲያስታርቁ ሽማግሎች ይመረጣል፡፡ከዚያ ለእርቁ አንድ ቤት ይቀመጣሉ፡፡ከዚያ መነሻ ምክንያቱን

ትንታኔ ከሰው ያዳምጣሉ፡፡ይሄ ሁሉ ከተነገረ በኋላ ምን እናድርግ ብለው ወደ መፍትሄ ይመጣሉ፡፡ አሁን ያለፈው አልፏል ወደፊት ያለውን በማየት ወደ ግጭት አንገባም፡፡ ይሄ የሰው ዘርንም ያጠፋል፤ ድህነትንም ያስከትላል ፤እኛ ሽማግሌዎች እያለን ይሄ ግጭት ይከሰት እንዴ? በኋላ ይሄ ግጭት ስር ሰዶ እንዳያድግ ጫፉን ቆርጠን እናሳጥረው ይላሉ ፡፡ለማሳጠር ባህል አለ፡፡

የሀገር ባህል የሆኑት ሽማግሌዎች የተወከሉት ከብት ይገዛሉ፡፡ ከብቱን ከገዙ በኋላ ከዚያ ወገን የመጡ ሽማግሌዎችና ከእኛ ቀበሌ የተወከሉት ያንን ከብት ካረዱ በኋላ አንዱን ታፋ ወደዚያ በኩል ያሉ እነዛ ሽማግሌዎች ጫፉን ይይዛሉ፡፡ እዚህ ወደዚህ ያሉትም ደግሞ አንዱን ጫፍ ይይዛሉ፡፡ ሃላፊ የሆኑት የበላይ የጎሳ መሪዎች ሁለተኛ ይሄ ግጭት መፈጠር የለበትም በማለት ይሄንን ጭን በቢላዋ ማሃሉን ይመታሉ ከዛ በኋላ እርቅ ይሆናል (ታደሰ ጉየታ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣የካቲት 20/2006 ፣26--28) ፡፡

## 4.3.ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትና የአፈታት ሂደት በኩሰሜ ብሔረሰብ

### 4.3.1.ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት

በኩሰሜ ብሔረሰብ በየቀጠናው አንድ አንድ በሸንጎ የተመረጠ አባ ዲባ አለው፡፡ ይህ አባ ዲባ ወይንም አስታራቂ ሁሉንም ጉዳዮች የማየት መብት አለው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጉዳይ በጥልቀት መታየት አለበት ብሎ ሲያሳብ ጉዳዩን ወደ በላይ ማለትም ወደ ዋናው አባ ዲባ ይልካል፡፡ ብሔረሰቡ በአንድ ቀበሌ ውስጥ ብቻ ተከልሎ የሚኖር በመሆኑ በቀበሌው ወይንም በብሔረሰቡ መካከል የሚኖረው አባ ዲባ አንድ ነው፡፡ ይህ ሰው እንዴት እንደሚመረጥ ከመረጃ አቀባዮቹ አንዱ አቶ በጎሮ ጠሊፋ ይገልፃሉ፡፡

ትልቁ አባዲባ የሚመርጠው ካለው በህዝቡ ውስጥ የሚያሳየው ሲነ-ምግባሩ አኗኗሩ ህዝብ ያለው አመኔታ ታይቷ ነው፡፡ ህዝብን ያስተዳድራል፡፡ አንድ ያደርጋል፡፡ በሂዝብ ማዕከል ሰላምን ይፈጥራል፡፡ ጥቅም ፈላጊ አይደለም፡፡ በሚል ሁኔታ ህዝብ አይቶ ነው ዘጠኙ ቀጠና አለ ፡፡የዘጠኙ ቀጠና ህዝብ ወጥቶ ትልቅ የፍርድ ቦታ ሞራ አለ፡፡ አደባባይ እና ቶራኦኛ ይባላል፡፡ እዛ

ሞራ /መሸንጎያ/ ትልቁ ሸንጎ ቆራ እኛ ማለት እንጨት ነው፡፡ ዛፍ ነው፡፡ እዛ ትልቅ ዛፍ አለ፡፡ እዛ ህዝቡ ይጠራና ከዚያ መካከል ህዝቡ ይመርጣል ፡፡ የፀደቀለት እና አሱን ከዛ ጀምሮ ህዝቡን ያስተዳድራል (በጎሮ ጠሊፋ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣የካቲት 20/2006 ፣26--28) ፡፡

አቶ ተፈሪ ታደሰ ደግሞ ለአባ ዲባነት ለመመረጥ ከእነዚህ ጉዳዮች በተጨማሪ የሚቀመጡ መስፈርቶችን ይገልፃሉ፡፡


አንድ ሰው ሽማግሌ ለመሆን በብዛት ከ40 ዓመት በላይ ቢሆን ነገሮችን ለይቶ እውነተኛ ፍርድ መፈረድ ይችላል ተብሎ ታይቶ ህዝብን ደግሞ መምራት ይቻላል፡፡ ቅን ይፈርዳል ፤ነገሮችን አያጣምም ፡፡አሁን ልጅ ነገር ከሆነ ብዙ ጊዜ ምንድን ነው አ ነገሮችን ይወስዳል በሀሳብ ፤ተበዳይንም በስነ ስርአት ማየት አይችልም ፡፡ያ ግን እድሜው ትንሽ ገፋ ያለ ከአርባ አመት በላይ ከሆነ ነገሮችን አመዛዝኖ ያያል፡፡ የልጅ አባት ስለሆነም ልጆች ምን እንደሚወዱ ፣ ቤተሰብ አስተዳደሪ ስለሚሆን ሴቶች ጋር ያለውን ድካም ምን አልባት የሚበደሉትን ነገር በትክክል ማየት ይችላል፡፡ ያለበለዚያ አሁን ወጣት ብታረግ ስለትዳር ስለልጅ እንዴት እንደሚያድግ አያይም ፡፡ስለዚህ እውነተኛ ፍርድ መስጠት አይችልም፡፡ አንዴት ሚስትህን እንደምታስተዳድር ያለውን መሸካከም አያይም፡፡ ለዚያ በብዛት እድሜው ጠና ያለ ከአርባ አመት በላይ ሲሆን ነው እዚህ የሚመጣው (ተፈሪ ታደሰ ፣በተጠያቂው መኖሪያ ቤት ፣የካቲት 15/2006 ፣ 7) ፡፡

ከተመረጠ በኋላ የማገልገያ እድሜው ገደብ የለውም፡፡

እሱ በታማኝነት ህዝቡን ካገላገለ በየአምስት አመት ምናምን ሳይሆን ገደብ የለውም እና እሱ በታማኝነት እየሰራ እስከታመነበት ድረስ ያገለግላል ከዚያ በኋላ እርሱ ደግሞ አሳርፉኝ ማረፍ እፈልጋለሁ ብሎ

አንዳንዴ ያሳውቃል ጥሩ እያገለገለም ማለት ነው ከዚያ ውጪ ደግሞ አንዳንድ ትናንሽ ጥቃቅን በደሎችን ከሰራ ከዚያ ጋር ተያያዞ ህዝቡ ደግሞ ከዚያ ሰፈር ያነሳዋል (ተፈሪ ታደሰ ፣በተጠያቂው መኖሪያ ቤት ፣የካቲት 15/2006 ፣ገፅ 8) ፡፡

በዚህ መስፈርት የሚመረጡት አባ ዱባዎች ማለትም ዋናው አባ ዱባና ንኡሳኑ ያላቸውን የተዋረድ መዋቅር ስናይ የሚከተለውን  ቅርፅ ይኖረዋል፡፡ይህ ቅርፅ ከመረጃ አቀባዮች የተገኘን መረጃ መሰረት በማድረግ ለግልፅነት ሲባል በአጥኚው የተዘጋጀ ነው፡፡




በዚህ የአደረጃጀት ቅርፅ መሰረት ዘጠኝ ንኡስ አባ ዱባዎች በየቀጠናው አንድ አንድ አሉ፡፡ እንደቀጠናው ትልቅነትና ትንሽነት ደግሞ የጎጥ ንኡስ አባ ዱባዎች ከቀጠናው አባ ዱባ ስር ይኖራሉ፡፡ የብሔረሰቡ አባላት በጋራ መክረው ውሳኔ የሚሰጡበት ዋናው የፍርድ አደባባይ ግን አንድ ብቻ ነው፡፡ መጠርያ ስሙ ከሌሎቹ ሞራዎች  በተለየ በሰው ስም  ቆራኦኛ ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህም የኦኛ እንጨት ማለት ነው፡፡ ተዋረዱን በተመለከተ ከመረጃ አቀባዮቹ አንዱ አቶ ፈይሳ ቃዊቶ ይገልጻሉ፡፡ “በቀጠና ኃላፊውን እንቢ ካለ ወደ ዋናው ሞራ (መሸንጎያ) ይተላለፋል

አባዲባ በየቀጠናው አለ፡፡ ዋናው አባዲባ ግን አንድ ብቻ ነው"(ፈይሳ ቀዊቶ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣የካቲት 20/2006 ፣24) ፡፡

## 4.3.2. ባህላዊ የግጭት አፈታት ሂደት በኩሰሜ ብሔረሰብ

ኩሰሜዎች አብዛኛዎቹን የግጭት ዓይነቶች የሚፈቱበት ወጥ የሆነ አካሄድ አላቸው፡፡ ዋና ዋና የሂደት ደረጃዎችን ስንመለከት በስድስት ይከፈላሉ፡፡ ብሔረሰቡ የኩስምኛ መጠሪያ የሰጣቸውን ከአማርኛ አቻቸው ጋር ለማስቀመጥ ተሞክሯል። እንደ ሂደት ተቆጥረው ስም ያልተሰጣቸው ነገር ግን በግጭት አፈታት ሂደቱ ላይ ለውጥ የሚያሳዩ ደረጃዎች አሉ፡፡እነዚህ ለጥናቱ ያመቹ ዘንድ ከድርጊቶቹ በመነሳት ለዚህ የጥናት አቅርቦት ብቻ የሚውል ስያሜ በአጥኚው ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሶስተኛውና አራተኛው ደረጃ ላይ ያሉት የቅጣት አስተያየትና ፍርድ የሚሉት ከነዚህ ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡

### 4.3.2.1. ክስ (ሆለታ)

በኩሰሜ ብሔረሰብ አንድ ተበዳይ እገሌ በድሎኛል ስለዚህም ይታይልኝ ፍርድም ይሰጠኝ ብሎ ሲያስብ ጉዳዩን ወደ ሞራ ይዞ ይመጣል፡፡ ይህ ሂደት ሆለታ ወይንም ክስ ምስረታ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ክስ የሚመሰርተው በቀጠናው ካለ ንኡስ አባ ዲባ ጋር ነው፡፡ አባ ዲባው በየሳምንቱ ማክሰኞ አርብና እሑድ ክሶችን ለማየት በማለዳ ተነስቶ የቀጠናው ነዋሪዎች በጋራ በሰሩትና በድንጋይ ተክቦ ማሃሉ ላይ ጥላ ያለው ዛፍ በተተከለበት ሞራ ላይ ይገኛል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሞራው የሚሰራው በቀጠናው ነዋሪዎች ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ በቀጠናው ያሉ ሽማግሌዎች ፣ጎልማሶች፣ በተለያየ ዕድሜ ያሉ ወንዶች ከአባ ዲባው ጋር በዚያ ይሰየማሉ፡፡ ሌሎቹ በሞራው ዙርያ ከበው ሲቀመጡ ከመሃል የሚቀመጡት ግን አባ ዲባውና ሌሎች ሽማግሌዎች ናቸው፡፡እነዚህ ሽማግሌዎች በቁጥር የተገደቡም አይደሉም ወደ መሸንጎያው የሚመጡትም በፍቃደኝነት ነው፡፡

ተበድያለሁ ብሎ ክስ የሚመሰርተው ሰው ወደ ሞራው እንደመጣ አባ ዲባው እግር ስር አምስት ብር ያስቀምጣል ይህም ተበድያለሁ ክስ አለኝ እንደማለት ይቆጠራል፡፡ ሆለታ የሚባለውም ይህ ነው፡፡

ከመረጃ አቀባዮቹ አንዱ የክስ አመሰራረት ሂደቱን እንዲህ ይገልፃል፡፡"ከሳሽ ሂዶ አምስት ብር ያስቀምጣል ፡፡ ሶስቱ ብር የክስ መመስረቻ ነው፡፡ሁለቱ ብር ሰውየውን ሂዶ ለሚያቀርብ የሚቀመጥ መጥሪያ ነው፡፡ከዛ ውጪ የምትፅፈው ነገር የለም አለቀ"(ተፈሪ ታደሰ ፣በተጠያቂው መኖሪያ ቤት ፣የካቲት 15/2006 ፣ 7) ፡፡

ይህ ክስ የሚቀርብ ሂደት ወይንም ሆለታ ከዚህ በተቃራኒው የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ይህም በዳይ በደሉን አምኖ አስቀድሞ ወደ አባ ዲባው ሂዶ እገሌን በድያለሁ እና አስታርቁኝ ብሎ ሽንጎውን ሲጠይቅ ነው፡፡ የብሩ መጠን ግን አይለወጥም፡፡ ይህ ግን ብዙ ጊዜ ተግባራዊ የሚሆነው በግድያ ወንጀል እንደሆነ መረጃ አቀባዮቹ ይናገራሉ፡፡

ክስ የቀረበለት አባ ዲባ የበዳዩን ማንነት ከተረዳ በኋላ በሞራው ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች መካከል ሰውየውን የሚያውቅና ለመላክ ፈቃደኛ የሆነ ሰው በድኋል የተባለውን ሰው ወደ መሸንጎያው ወዲያወኑ ይዞ እንዲመጣ ይላካል፡፡ በዚህ ጊዜ ከሳሽ በአባ ዲባው እግር ስር ካስቀመጠው አምስት ብር ለመላክ ፍቃደኛ የሆነው ሰው የተላከበትን ሁለት ብር ይወስዳል፡፡ ሰውየውንም ወደ ሞራው ይዞ ይመጣል፡፡ ይህን ሂደት ከአውራ መረጃ አቀባዮቹ አንዱ አቶ ፈይሳ ቃዊቶ በዝርዝር ይገልጹታል፡፡

> "ማመልከቻ አያስፈልግም ፡፡ድሮ ሁለት ብር ነው፡፡ አሁን አምስት ብር ነው፡፡ ይሄን ብር ይዞ ወደ /ሞራ/ መሸንጎያ ከሄደ ልክ እኛ አሁን እንደተሰባሰብን ልክ እዚያ ይቀመጣል፡፡ የቀጠና ሽንጎ አባዱባ ፊለፊት ሂዶ ፊት ላይ ያስቀምጣል፡፡ ብሩን ከዛ በኋላ የቀጠና ኃላፊው ምንድን ነው ብሎ ከጠየቀው በኋላ እከሌ እኔን በድሎኛል እና እከሌን አቅርብልኝ ይላል ፡፡ሁለት ብር መልዕክተኛ ይሰጣል ፡፡ከዛ ሽንጎ ላይ ካለው እከሌን አቅርብ ሲባል ሁለት ብር ይሰጣልና ሂዶ ግለሰቡን ያቀርባል፡፡

አባ ዲባው እዛው አካባቢ ካሉት ዝም ብሎ አንዱን ፍቃደኛ የሆነን ሰው ይልካል፡፡በዚህ መሰረት ሶስቱ ብር እንደ መከርከርያ ማለት ነው እዚያ ትጠብቃለች፡፡ እሱ ከመጣ በኋላ እርሱም ሶስት ብር ያስቀምጣል፡፡ ተከሳሹ ማለት ነው፡፡ ከዚያ ክርክር ያስቀጥላል እንግዲህ ተከራክረው የማይታማመኑ ከሆነ ተበደልኩ የሚለው ማስረጃ ይቆጥራል፡፡ ተበደልኩ የሚለው ማስረጃ ከቆጠራ በኋላ ወይም ተበደልኩ የሚለው ሊረታ ይችላል፡፡ አልያም በዳዩም ሊረታ ይችላል፡፡ በዛ መሰረት ማስረጃ ወደ ሸንጎም ሊቀርብ ይችላል አለዚያም ሰው ተወክሎ ሄደ ያስመሰክርና በወረቀት ሳይሆን የእነርሱ አመለካከት አውነት ይታይና በዚያ እውነት መሰረት ያንን ይዞ ይመጣል፡፡

> በዚህ የማስረጃ ሁኔታ ታይቶ እርሱ ይሄንን ውሳኔ አልቀበልም የሚል ከሆነ ከዛ በታች ጎጥ የሚባል አለ እርሱን እንቢ ብሎ ወደ ሞረ (ሸንጎ) ከሄደና ሸንጎ ላይም እንቢ ብሎ ከተሸነፈ ፡፡ቀጥታ እንግዲህ ቅደም እንዳልነው ወደ አባ ዲባ ይተላለፋል፡፡ ስለዚህ የኛ የህግ ስርዓት ይህን ይመስላል፡፡ " ነው፡፡(ፈይሳ ቀዊቶ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣የካቲት 20/2006 ፣34)

## 4.3.2.2.ማስረጃ

ይህ ከባህላዊው የፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ሁለተኛው እርከን ነው፡፡ ነገር ግን ተከሳሽ በከሳሽ የቀረበበትን አቤቱታ አምኖ ከተቀበለ የሚዘለል ይሆናል፡፡ ተከሳሹ ተጠርቶ ከመጣና ከሳሽ ክሱን ካሰማ በኋላ ይህን አላደረኩም ካለና ከተከራከረ አባዲባው ክርክሩን በማስቀጠል ከሳሽ ማስረጃ እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡ በሞራው ውስጥ ከታደሙት መካከል ጉዳዩን የሚያውቁ ጥፋቱ ሲፈፀም አይተናል ያሉ ሰዎች ተከሳሽ ለምስክርነት ሳይጠራቸውም ቢሆን አባ ዲባውን እጅ በማውጣት አስፈቀደው ያዩትን ነገር ይመሰክራሉ፡፡ እኔ ምልከታ በካሄድኩባቸው ሁለት የቀጠና ሸንጎዎችም ከታዳሚዎቹ መሃል በፍቃደኝነት ጉዳዩን እናውቃለን ያሉ ሰዎች ሲመሰክሩ በአስተርጓሚዬ እርዳታ ማየት ችያለሁ፡፡ ሆኖም ይህ የማስረጃ አቀራረብ በሰው ብቻ አይወሰንም ድርጊቱን ያሳያሉ የተባሉ ቁሶችም በማስረጃነት ይቀርባሉ፡፡ በቀጠና ዘጠኝ ከአባቱ ጋር ሲጣሉ የእርሱን ተቀሳቃሽ ስልክ የሰባበረው ወጣት የስልኩ ስብርባሪ በማስረጃነት ሲቀርብ ተመልክቻለሁ፡፡

በዋናነት ግን ተከሳሽ የሚያቀርባቸው የሰው ማስረጃዎች ይደመጣሉ፡፡ ሁሉቱም ወገኖች ጥፋቱ እስኪረጋገጥ ድረስ በማስረጃ የተደገፈ ክርክር ያደርጋሉ፡፡ አባዲባው ጉዳዩ በደንብ መጣራት አለበት ብሎ ሲያስብ ወደ ሶስተኛው ደረጃ ያሳልፋቸዋል፡፡

### 4.3.2.3 ሽማግሌ መጥራት

ይህ ደረጃ በሁለቱ ወገኖች መካከል ብዙ ክርክር ከተደረገ በኋላ ጉዳዩ ይበልጥ በሰከነ መልኩ እንዲታይና ሰዎቹ የሚግባቡበት መንገድ ካለ ይህንንም ለማየት ይረዳ ዘንድ በሞራው ከተሰበሰቡት ሁለቱም ወገኖች በዳይም ሆነ ተበዳይ ያሸማግሉናል ብለው የሚያስቡትን አንድ አንድ ሰው ይመርጣሉ፡፡ አባ ዲባውም ለተመረጠው ሰው ጉዳዩን በመስጠት ሁለቱን ወገኖች ከሸንጎ ጥቂት ራቅ ብሎ በሚገኝ ስፍራ ወሰደው እንዲያነጋግሯቸውና የመፍትሄ ሀሳብ ይዘው እንዲመጡ ያዛል፡፡ ቦታው ከሞራው ራቅ ይበል እንጂ ዛፍ ስር አልያም ሜዳ ላይ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜም ከሳሽም ይሁን ተከሳሽ በአባዲባው ስር ካስቀመጡት ብር ላይ አሸማጋዮቹ የሽምግልናቸውን ሶስት ብር በማንሳት ሊያሸማግሏቸው ይሄዳሉ፡፡ ሁለቱን ወገኖች በሚገባ ካነጋገሩ በኋላ ጥፋተኛውን ለይተው ይገባዋል የሚሉትንም ፍርድ ይዘው ወደ ሸንጎው ይመለሳሉ፡፡ ይህ ሂደት እስኪከናወን የሞራው መሪ አባ ዲባውም ሆነ በዚያ የተሰበሰበው ሰው ሌላ ክስ ካለ ያያል፡፡ ከሌለ የተለካው ሽማግሌ አንዳች እልባት ላይ ደርሶ እስኪመጣ ይጠብቃል፡፡

### 4.3.2.4 የቅጣት አስተያየት

ይህ በፍርድ ሂደት ውስጥ አራተኛው ደረጃ ነው፡፡ በሶስተኛው ደረጃ ላይ በበዳይና ተበዳይ የጋራ ፍቃድ የተመረጠው ሽማግሌ የክሱን ትክክለኛነት አረጋግጦ ጥፋተኛውን ለይቶ ለዚህ ጥፋት ይህ ፍርድ ይገባል የሚለውን ውሳኔ ይዞ ወደ ሞራው ይመለሳል፡፡ ይህንንም ለአባ ዲባው ያቀርባል፡፡ አባ ዲባውም ከሽማግሌው የደረሰውን መረጃ በሞራው ለተሰበሰቡት ሁሉ በመናገር በውሳኔው ላይ አሰተያየት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ አንፃል አልያም በዝቷል ካሉም የራሳቸውን አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ በተለይ በዳይ ከዚህ በፊት ጥፋት አጥፍቶ የማያውቅ ከሆነ ምህረት

እንዲያገኝ ብዙዎች ይጠይቃሉ፡፡ አስቸጋሪ ነው ብለው ካመኑና የሽማግሌው ቅጣት አነስተኛ ነው፣ አያስተምረውም ካሉ ከፍ ያለ ቅጣት እንዲጣልበት ያደርጋሉ። አባ ዲባው የሞራውን ሀሳብና የክሱን ሁኔታ አገናዝቦ ከአንድ ውሳኔ ላይ ይደርሳል፡፡

## 4.3.2.5 ብይን

በኩሰሜ ብሔረሰብ በቀረበ ክስ ላይ አስተያየት መስጠት በሞራው ለተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ የተፈቀደ ቢሆንም የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው ግን አባ ዲባው ነው፡፡ አባ ዲባው ጉዳዩን ከአቅሜ በላይ ነው ወደ ቀጣዩ ዋና አባዲባ ይተላለፍ ብሎ ካመነ ያስተላልፋል፡፡ አልያም ከአሽማጋይነት ከተመረጠው ሰው የተሰጠውን የፍርድ አስተያየት እንዲሁም በሸንጎው የታደሙት ሰዎች የሰጡትን የፍርድ አስተያየት ከግምት አስገብቶ የቅጣት ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ቅጣቱ በገንዘብ ነው የሚወሰነው፡፡ የሰው አካል ላይ ጉዳት ካደረሰ፣ ንብረት ካጠፋ ደግሞ ከሳ እንዲከፍል ይገደዳል፡፡ ስድብ፣ የዕለት ግጭት መጠነኛ ድብደብ፣ ስርቆት ከሆነ ደግሞ የሚወሰንበትን ቅጣት የሚከፈለው ለተበዳዩ ሳይሆን ለቀጠናው ሞራ ነው፡፡ ብሩ 250 ጀምሮ እስከ አንድ ሺህ ብር  ብር ይደርሳል፡፡ በዚህ መልኩ ከአጥፊዎች የሚሰበሰበው ገንዘብ በአባ ዲባው አማካኝነት ለጋራ የአካባቢ ልማት እንዲውል ይደረጋል፡፡

## 4.3.2.6 ማዕቀብ/ዱፈና/

ዱፈና አንድ በጥፋተኝነት ተከሶ ጥፋቱም በምስክር ተረጋግጦበት ብይን የተላለፈበት ሰው ብይኑን አልቀበልም ሲል ከህብረተሰቡ የሚገለልበት ሥርአት ነው፡፡ የኩሰሜ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓታቸው እስካሁን ዘልቆ እንዲቆይ ካደረጉ እሴቶች መካከል ዋነኛውም ይህ ማዕቀብ የመጣል ስርአት ነው፡፡

ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ የተበየነበት ሰው የብሔረሰቡን ሕገ ደንብ አልቀበልም በማለቱ ከማህበረሰቡ እንዲገለል ይደረጋል፡፡ ይህም በዛው በሞረው አካባቢ ላሉትም ሆነ በየቤታቸው ላሉ ሁሉ በአዋጅ ይነገራል፡፡ እከሌ የተባለ ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሳለ

የተጣለበትን ቅጣት ባለመቀበሉ ተዘግቷል እየተባለ ይነገራል መዘጋት /ዱፊና/ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን ከመረጃ አቀባዮች አንዱ ይገልፃሉ፡፡

> ተገሏል ማለት ከህብረተሰቡ ገለልተኛ ሆኗል ማለት ነው እንግዲህ ከተገለለ ይሄ ሰው ደግሞ ምንድን ነው የሚሆነው፡፡ ሚስቱ ብትወልድ ዞሮ ብሎ የሚጠይቅ የለም ሚስቱ ብትሞት ለቅሶ ማንም አይጠይቅም ማንም አይሄድም እሳት ከጎረቤት እንዲጭር አይፈቀድም የእርሱ ሚስት ውሃ ከወንዝ ሄዳ ከቀዳች የሚያሸክማት ሰው አይኖርም በማንኛውም ነገር ከህብረተሰቡ ይገለላል ማለት ነው(ጌታቸው ዲምባ ፣ጊዶሌ ገቢዎች ፅ/ቤት፣17/6/06) ፡፡

ስለዚህ የብሔረሰቡን ውሳኔ እንዳልተቀበለ ተቆጥሮ ፍፁም ከህብረተሰቡ እንዲነጠል በማድረግ ሰውየው ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኝ ያደርጋሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰውና ቤተሰቡን ማዕቀቡን ወደጎን ትቶ አብሮ መብላት መጠጣት ወደ ቤት እንዲገባ መፍቀድ እንደሚያስቀጣም ነው መረጃ አቀባዮቹ የሚናገሩት፡፡ ከዚህ የተነሳ አባትም ቢሆን ልጁ ላይ ይጨክናል፡፡ ልጅም ከማህበረሰቡ ላለመገለል ሲል በተመሳሳይ አባቱን ከደጁ እንዳይደርስ ይከለክላል፡፡ የቅጣቱን መጠን በተመለከተ ከሀገር ሽማግሌዎች አንዱ የሆኑት መረጃ አቀባዬ እንዲህ ይገልፃሉ፡፡

> እርሱ የሰው ቤት የሄደ እንደሆነ በፊት አስራ አምስት ብር ነበር የገባበት ቦታ የሚቀጣው ፡፡አሁን ግን 50 ብር ነው ፡፡የተገለለ ሰውየው ሰው ቤት ከገባ አሁንም ደግሞ ከሰው ቤት ከገባ ያስገባው ሰው ሁለት መቶ ሃምሳ ብር ሊቀጣ ይችላል (ፈይሳ ቀዊቶ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣የካቲት 20/2006 ፣34) ፡፡

በክርክሩ መረታቱን አምኖ ጥፋቱን ተቀብሎ ቅጣቱን ለመቀበል እስካልወሰነ ድረስ ማዕቀቡ እንደሚቀጥል ነው የገለፁት፡፡

### 4.3.2.7 ማርካ /ይቅርታ/

ማርካ በኩሰሜ ብሔረሰብ ዘንድ አንድ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ይቅርታ የሚጠይቅባት መንገድ ነው፡፡ አንድ በዳይ ማርካ /ይቅርታ/ የሚጠይቀው ቅጣቱን አምኖ ተቀብሎ

የተጣለበት የገንዘብ ቅጣት መጠኑ እንዲያንስለት ሲፈልግ ማዕቀብ ዱፈና ከተጣለበት በኋላ እርሱ ተነስቶለት ከማህበረሰቡ ጋር እንዲቀላቀል ሲፈልግ ነው፡፡

ሁለቱም የየራሳቸው አካሄድ አላቸው፡፡ የመጀመሪያው ማለትም የተጣለበት የቅጣት መጠን እንዲያንስላት የሚፈልገው 500 ብር ተቀጥቶ ከሆነ መጠኑን አሳንሶ 50 ብር ወይንም መቶ ብር አድርጎ እርጥብ አረንጓዴ ቅጠል አንድ ላይ አድርጎ አባ ዲባው ፊት ያስቀምጣል፡፡አባ ዲባው የብሩን መጠን ቆጥሮ ከይቅርታ ጋር ያስገባው የገንዘብ መጠን ይሄ ነው በማለት ይናገራል፡፡ ይቅርታ መጠየቁን ሞራው ከተቀበለው ይሁን ብሎ ይቅርታ ያደርግለታል። ሆኖም ሰውየው በተደጋጋሚ ጥፋት አጥፍቶ ይቅርታ ተደርጎለታል፣ ስለዚህ አሁን የብር መጠኑ ሊቀነስለት አይገባም ካለ ግን ይቅርታው ተቀባይነት ያጣል፡፡ በቀጠና ዘጠኝ በነበረኝ ምልከታ ግን የተቀጣው ሰው እንዲህ ዓይነት እንቢታ ሲያጋጥመው የብር መጠኑን እያሳደገና ከቅጠል ጋር እያጣመረ በተደጋጋሚ ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን በሞረው /ሸንጎ/ የተሰበሰቡ ሰዎች ይቅርታ ላለማድረግ አንዴ ምክንያት አስቀምጠው እንቢ ካሉ ደግሞ ሀሳባቸውን እንደማይቀይሩ በቀጠና ዘጠኝ ሞራ ላይ ባደረኩት ምልከታ ታዝቤያለሁ፡፡

ሁለተኛው ይቅርታ የሚጠይቀው ማዕቀብ የተጣለበት ሰው ነው፡፡ ይህ ሰው አረንጓዴ ቅጠል ይዞ በመምጣት በተሰበሰበው ሞራና አባ ዲባው ፊት ቆሞ ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ጊዜ አባ ዲባው ተበዳይን ይጠራና እገሌ አምኖ ይቅርታ ስለጠየቀ በሉ ሽማግሌ ተሰጣጡ ይላል። በዳይ የነበረውና አሁን ይቅርታ የጠየቀው ሰው ሁለት፣ ተበዳዩ ሁለት ሽማግሌዎች ይመርጡና ከዋናው ሞራ ራቅ ብለው ሜዳ ላይ አልያም ዛፍ ካገኙ ዛፍ ስር ይወያያሉ፡፡ ሆኖም ትኩረት የሚሰጠው ከሞራው መራቃቸው እንጂ የሚቀመጡበት ቦታ አይደለም፡፡

የአሁኑ ድርድር ሰውየው ጥፋተኝነቱን ስላመነ ትኩረቱን የሚያደርገው አዲስ የሚጣለው የቅጣት ውሳኔ ላይ ነው፡፡ በዚህ ድርድር ሽማግሌዎቹ ሁለቱንም ወገኖች አማክረው የሚደርሱበትን የውሳኔ ሀሳብ ለአባዲባው ያቀርባሉ፡፡ አባ ዲባው ቅጣቱን ለሞራው ያሳውቃል፡፡ ሁለቱ ወገኖች ተግባብተው ስለሚመጡ ብዙውን ጊዜ

የሽማግሌዎቹ የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያገኛል፡፡ ይሁን እንጂ አባ ዲባውም ሆነ የሸንጎው ታዳሚዎች በቅጣቱ ላይ አስተያየት ካላቸው ይሰጣሉ። በመጨረሻ ሁሉንም ያግባባ የቅጣት ውሳኔ ያሳልፋሉ፡፡ ብይን ይሰጣሉ ይቅርታ ጠያቂው የተጣለበትን ቅጣት ወዲያው ከፈፀመ አልያም እንደሚፈፅም ቃል ገብቶ ዋስ ከጠራ ተጥሎበት የነበረው ማዕቀብ ይነሳለታል፡፡ ይህም ሲጣል እንደተደረገው ሁሉ መነሳቱ በአዋጅ ይነገርለታል፡፡

## 4.4.ትዕምርቶች በባህላዊ የእርቅ ስነ ስርዓት ውስጥ

የኩስሜ ብሔረሰብ ተግባራዊ በሚያደርገው የእርቅ ስነ ስርዓት ውስጥ የተለያዩ ትዕምርቶች አሉ፡፡ እነዚህ ትዕምርቶች የየራሳቸው የሆነ ፍቺ አላቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ዋነኛ የሚባሉና በእርቅ ሥነ ሥርዓቱ የሚታዩ ትዕምርቶችን በመውሰድ ስለምንነታቸው ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

4.4.1 **እርጥብ ቅጠል፡-** እርጥብ ቅጠል በባህላዊ የእርቅ ስነ ስርዓቱ ላይ ማርካ /ይቅርታ/ በሚጠየቅበት ሰዓት ያገለግላል፡፡ አንድ ጥፋተኝነቱ ታምኖ በሞራው በገንዘብ የተቀጣ ሰው ቅጣቱን አምኖ ከተቀበለ በኋላ የተመደበለት የቅጣት ገንዘብ እንዲቀነስለት ሲፈልግ የተቀጣውን ግማሽ አሊያም ሩብ የገንዘብ መጠን ከእርጥብ ቅጠል ጋር አድርጎ ያቀርባል፡፡ ይህም ምህረት ለመጠየቁ ማሳያ ነው፡፡

> አጥፍቻለሁ ማረኝ ካለ እና ቅጠል ይበጥሳል ቅጠል በጥሶ አረንጓዴ ቅጠል ይዞ ይመጣል ማርኩ ይላል ማረኝ ያን ካለ በኋላ ሽማግሌዎቹ የወሰኑት ቅጣት ሚሂረት ይደረግለታል፡፡ ይሂ የመጀመሪያ ፈተና ነው ለእርቅ ሰውየው ውስጡን እንዲለቅ ወደ እርቅ እንዲመጣ የሚደረግ ነው (ተፈሪ ታደሰ፣መኖሪያ ቤት፣15/06/06፣ገፅ6) ፡፡

4.4.2 **እርድ፡-** የእርድ ስነ ስርዓት የባህላዊ እርቅ የመጨረሻ ማሳረጊያ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የፍጹም እርቅ መፈጸምና የመንፃት ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እርድ ከተከናወነና በአንድ ላይ ከተበላ በኋላ ሁለቱ ወገኖች ዳግም ለበቀል አይፈላለጉም

ማለት ነው፡፡ እርቃቸውም በሁለቱም ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘቱ ማሳያ ነው፡፡ የእርድ ስነ ስርዓት ከመንጻት ጋር የሚዛመድም ነው፡፡ ለምሣሌ አንዲት ሴት ሞራ ውስጥ ብትገባ እርሷ በመግባቷ ሞራው ረክሷል ተብሎ ስለሚታሰብ ሞራው እንዲነፃ እርሷም ይቅርታ እንዲደረግላት ፍየል ታመጣለች፡፡ ያመጣችው ፍየል በሽማግሌዎች ታርዶ ደሙ በሞራው ላይ ይረጫል፡፡ ስጋውም እዚያው ተጠብሶ ይበላል፡፡ከዚህ በኋላ እርሷም ከጥፋቷ ነፃ ትሆናለች ሞራውም ነጽቷል ተብሎ ይታመናል፡፡"ፍየል የምታደርበት ምክንየት ደፍራ ስለገባች ነው፡፡ሞራው እንትን ካልተረጨ ሰውም እዚህ አይገባም ሞራው በደንብ ካልነፃ ሰዎች እዚህ አይገቡም ከተረጨ በኋላ እርሷም ከሰው ጋር ተቀላቅላ መኖር ትችላለች፡፡"(አቡዴ በራንጉዴ፣ቀጠና ሶስት ሞራ አካባቢ፣02/07/06፣ገፅ48)

## 4.5. ከመደበኛው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት ውጪ የሚታዩና የሚፈቱ የግጭት ዓይነቶች

በኩሰሜ ብሔረሰብ ዘንድ ከመደበኛ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች መጠነኛ ለውጥ የሚደረግባቸው የግጭት ዓይነቶች አሉ፡፡ እነዚህም ግድያና ከሌላ ብሔር ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶች ናቸው፡፡ የግጭቱን ዓይነቶች በተናጠል በመውሰድ ከመደበኛው ባህላዊ የግጭት አፈታት ሂደት የተለዩበትን ለማጉላት ይሞከራል፡፡

### 4.5.1.ግድያ

ቀደም ባሉት ዘመናት የኩሰሜ ብሔረሰበ አባላት በንጉስ በሚተዳደሩበት ወቅት ግድያ የፈፀመ የብሔረሰቡ አባል ጥፋቱን አምኖ ይቅርታ ለመጠየቅ ሲሻ ከንጉሱ ቤት ይገባ እንደነበር ይገለፃል (ብ/ህ/ፕሮፋይል፣2002፣198)፡፡ አሁን ደግሞ የግድያ ወንጀልን ሙሉ በሙሉ በባህላዊ የፍርድ ስርዓቱ ማየት ማቆሙንና እንዲህ ዓይነቱ ክስተት ሲያጋጥም መረጃውን አጠናቅረው ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት እንደሚልኩት ከመረጃ አቀባዮቼ አንዱ ሲገልፁ"ግድያማ እኛ ጋር አይደለም ይሄማ ወንጀል ነው ፖሊስና ፍርድ ቤት ነው የስህተት ነው እንጂ ሆን ብሎ የሚሰራው ይሄማ ባህላዊ አይገባም" (ታደሰ ጎይታ፣ጋቶ ቀበሌ ጤና ጣቢያ፣20/6/6) ፡፡

አቶ ፈይሳ ቃዊቶ ግን የመግደል ሙከራ ተደርጎ ከተረፈ እኛ ማስታረቅ እንችላለን ይላሉ፡፡ አንድ በስለት ተወግቶ የተረፈን ሰው እንደምሳሌ በማቅረብ "በወንጀል ነፍስ ግድያ የነፍስ ግደያ እና ማስታረቅ የምንችለው ተወግቶ በህይወት የተረፈ ከሆነ ይሄን ያደረገው ሰው ግለሰብ እሱ ታስሮ ቤተሰብ እዚህ ካለ ሰውየው የተወጋበት ቤተሰብ ሽማግሌ ይላክበታል፡፡" (ፈይሳ ቀዊቶ፣ጋቶ ጨና ጣቢያ፣የካቲት 20/2006 ፣34)

ሌላኛው መረጃ አቀባይ አቶ ጌታቸው ዲምባ ደግሞ የግድያ ወንጀሉን የፈፀመው ሰው በፍርድ ቤት ቢበየንበትም የገዳይና የተገዳይ ቤተሰቦች በጠብ እንዳይፈላለጉ ለማድረግ የእርቅ ስነ ስርዓቱን ማካሄድ የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ ተግባር ነው ይላሉ፡፡

> ‹‹ … እኔ ከሞትኩ አንተ በመንግስት ስትራክቸር ትከሰስና ትታሰራለህ ወህኒ ቤት ማረሚያ ቤተ ገብተህ 10እና15 አመቲ ይፈረድብሃል ሆኖም በግዲያው ሳቢያ የአንቴና የኔ ጎሳ አባላት በጥሩ አይን አይተያዩም የኔ ቤተሰብ ያንተን ቤተሰብ ይፈልጋል ለበቀል ማለት ነው ያ እንዳይኖር የኔ ጎሳ መሪ የአንቴ ጎሳ መሪ ተዋናይ ይሆናሉ እነዚህ ሁለቱ ቤተሰቦች መታረቅ አለባቸው፡፡››(ጌታቸው ዲምባ ፣ጊዶሌ ገቢዎች ፅ/ቤት፣17/6/06 ፣ገፅ 14)

ስለዚህ በዳዩ በመንግስት ብያኔ ከተሰጠው በኋላ የእርሱ ጎሳ አባላት ወይንም ቤተሰቡ ከሟች ቤተሰብ ጋር ጠብ ውስጥ እንዳይገቡ የእርቅ ስነ ስርዓት ይፈፀማል ይህኛው የእርቅ ስነ ስርዓት ቀደም ሲል ካየነው የተለየ መልክ ያለው ነው፡፡ ከልዩነት ነጥቦቹ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ በሞራ ሳይሆን ቤት ለቤት ነው የሚደረገው

ለ/ አባ ዲባው እንደ አንድ ሽማግሌ ሆኖ ያገለግላል እንጂ ስልጣኑ እንደሞራው አይደለም

ሐ/ ገዳዩ ጥፋተኝነቱ አስቀድሞ የታወቀ በመሆኑ ክርክር አይካሄድበትም

መ/ ተበዳይ ሳይሆን ወደ ሽማግሌ የሚሄደው በዳይ ነው ከሃይማኖት መሪዎች ከጎሳ መሪዎች ከሀገር ሽማግሌዎች የተውጣጣ አሸማጋይ ቡድን ይዞ ሄዶ ይቅርታ ይጠይቃል፡፡

ግድያን ወይንም የግድያ ሙከራን የፈፀመው ሰው እርቅን ከበደለው ወገን ለማግኘት ሲሻ በቅድሚያ የሚያደርገው የራሱን የጎሳ መሪ የሃይማኖት አባቶች ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎችን ይዞ የግድያ ሙከራ ወደ ተደረገበት አልያም ወደ ተገደላባቸው ቤተሰቦች ዘንድ ይልካል፡፡ ሽማግሌዎቹም ጉዳዩን ገልፀው ለይቅርታ ጥያቄ መምጣታቸውን ለተበዳይ ወገን ይገልፃሉ፡፡ ወገናቸውን በሞት ያጡት ቤተሰቦች ይቅርታውን የሚቀበሉ ከሆነ በመጀመሪያው ቀን እሺም እንቢም ሳይሉ በፊታቸውና በአካላቸው እንቅስቃሴ መልስ ይሰጣሉ፡፡

እንደ አቶ ሉዳይደ ጉጋ ገለፃ ከሆነ የተበዳይ ወገኖች የሽማግሌዎቹን አይን እያዩ ፈገግ ካሉ ለእርቅ ተዘጋጅተዋል ማለት ነው ሽማግሌዎቹም ለሌላ ቀን ቀጠሮ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ የተበዳይ ወገኖች እርቁን የማይፈልጉ ከሆኑ ፊታቸውን ያጨማድዳሉ ጥርስና ከንፈራቸውን ይነክሳሉ፡፡ ይህ ማለት ለእርቁ አሁን ፈቃደኛ አይደሉም ማለት ነው ሽማግሌዎቹ በሌላ ቀን ነገር ሲበርድ ለመምጣት ወደመጡበት ይመለሳሉ፡፡

ይህ ሂደት የግድያ ሙከራ በተደረገበት ሰው ቤተሰቦቹ ዘንድም ይሰራል። አመላለሳቸው ግን ይለያያል ሽማግሌዎቹ ሲመጡ የመጡት በትኩስ ከሆነና ቁስሉ ካልዳነ እስቲ ከሽምግልናው በፊት መዳን አለመዳኑን እናረጋግጥ ብለው ይመልሳሉ፡፡

በኋላ ላይ ግን ቀጠሮ ያረዝሙ ይሆናል እንጂ ሁለቱም ከመታረቅ ወደ ኋላ አይሉም፡፡ የመግደል ሙከራ ተደርጎበት ከሆነ ሰውየው ከዳነ ሽግሌዎቹ ይህን ወንጀል የሰራው ሰው ሆነ ቤተሰቦቹ የህክምና ወጪውን እንዲችሉ የቁስል መጠገኛ የሚሆን የሞራል ካሳ እንዲሰጡ ያደርጋሉ፡፡ የተፈፀመ ግድያ ከሆነ ግን ካሳ አይወስዱም የተለያዩ ጎሳ አባላት ከሆኑ ተመሳሳይ ችግር በዚያኛውም ጎሳ ቢፈጠር ካሳ ላለመብላት ውል ያስራሉ። ይህ ክንውን በሁለቱ በገዳይና ተገዳይ ጎሳ መሪዎች አማካኝነት ይፈፀማል፡፡

እርቁን ፍፁም ለማድረግ ገዳይ በተገዳይ ወገን ቤት ፍየል ያርዳል። የታረደውን ፍየል በጋራ ሆነው መጀመርያ አንጀቱን ይበላሉ። ይህም ከአንጀታችን ታርቀናል በሚል የሚከናወን ነው፡፡ ከዚያ በኋላ በግድያው ሳቢያ ተኮራረፈው የነበሩት ጎሳዎች በአንድ መብላት መጠጣት ይጀምራሉ ከሁለቱም ወገን የሚያስፈልገው ነገር ቀርቦ እየተባለ እየተጠጣ ሰላምና እርቅ እንዲወርድ ይደረጋል፡፡ይህን ሂደት በተመለከተ ከመረጃ አቀባቹ አንዱ ዘርዘር አድርገው ይገልፁታል፡፡

> በባህሉ እንታረቃለን የሚሉ ከሆነ ሽማግሌ ይላካሉ ወደ ተበደለው ሰው ሽማግሌ ይልካሉ፡፡ በሚልኩት ሰው ከሃይማኖት መሪዎች ከጎሳ መሪዎች ከባባቢው እውቅና ያሉ ሽማግሌዎች እንደዚያ አይነት ሽማግሌዎች እነዛ ወደ እዚያ የሚላኩ ከሆኑ እርቅ ውስጥ እሽታም አለ እንቢታም አለ እነዚህን ነገሮች መርምረው አቅጣጫ ለእነርሱ ያሳያሉ በክርክር ጊዜ ከመጨረስ የተወሰደው ነገር የጠፋው ነገር ይኸው ይታያልና ወደ እርቅ ቢመለስ ይሻላል አንድ ጊዜ ሆኗል ወደፊት በአንድነት በጋራ ብትኖሩ በሰላማዊ መንገድና በፌቅር አብራችሁ መንገድ ላይ ብትገናኙ በሰላም ብትነጋገሩ ይሻላል፡፡ አብራችሁ እንዲኖራችሁና በሰላም እስከዚህ እንዳይደርሳችሁ ብትኖር በማለት አቅጣጫ በእነርሱ ያሳያሉ እነዚህ የተመረጡ ሽማግሌዎች ይሄንን ለእነርሱ የእርቅ አቅጣጫ ያሳያሉ እርቅ የሚፈልግ ግለሰብ ከሆነ እንግዲህ ዝም ይልና እነዚህ ለእርቅ የመጡ ሽማግሌዎችን አይን ያያል እሺ የሚል ከሆነ ደግሞ እርቅ ይፈልጋል ሰለዚህ ተበዳዩ ፈገግታ ያሳያል፡፡
>
> እርቅ የማይፈልገው ደግሞ ሽማግሌዎች ሲነጋገሩ ወደ እርቅ መስመር ለማምጣት ሲሞክሩ እርቁ የማይገባውና የማይመሰለው ከሆነ ፊቱን ያጨማድዳል ጥርሱን ከንፈሩን ይነክሳል ይሄ እርቅ የማይፈልግ ሲሆን እንቢተኛ ስለሆነ ይሄ እርቅ የማይፈልግ ስለሆነ ከሽማግሌዎች በቃ ከመሰረቱ ያያሉ ነገሩን ከዚያ በኋላ ለሌላ የህግ አካል ያስተላልፋሉ ወደ መንግስት (ሉዳይደ ጉጋ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣የካቲት 20/2006 ፣ 26) ፡፡

## 4.5.2 የብሔር ግጭት

የኩሰሜ ብሔረሰብ አብዛኛውን ጊዜ ግጭት የሚፈፅመው ከአጎራባቾቹ ሁሉ ጋር ሳይሆን ከኮንሶ ጋር ነው። ከደራሼ ከማሾሌና ከሙስዬ ጋር እነርሱ የሚያውቁት የተፈፀመ ግጭት እንደሌለ የሀገር ሽማግሌዎቹ ይገልፃሉ፡፡

በ1987 አካባቢም ከዚህ ከኩሰሜና ከኮንሶ አጎራባች ቀበሌዎች አካባቢ በተፈፀመ ግድያ እርስ በእርስ ብዙ ሰው የተገደለበት ግጭት ተከስቶ እንደነበርም ይናገራሉ፡፡

በጊዜው ግጭቱ የቆመው የመንግስት ኃይል በመሀል ገብቶ ቢሆንም እርቁን ለዘለቄታው የፈፀሙት ግን የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ ሽማግሌዎቹ ከጎሳ መሪዎች ከሃይማኖት መሪዎች ከሀገር ሽማግሌዎች የተውጣጡ ናቸው የኩሰሜ ብሔረሰብ ዋና አባ ዲባም እዚህ ውስጥ ይካተታል የሀገር ሽማግሌዎቹ ከሁለቱም ብሔር የሚውጣጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ሽማግሌዎች በአንድ ቤት ተቀምጠው ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት እንደሚመክሩ ዋና መረጃ አቀባዬ ታደሰ ጉይታ ይገልፃሉ፡፡

"እኔ በራሴ የዚህ አካባቢ ነዋሪ ነኝ፡፡ የሀገር ሽማግሌ፣ የቡድን ግጭት እስከዛሬ ያየሁት ጎሳ ለጎሳ ተጋጮ የሚባል ነገር አላየሁም፡፡ ከሌለ አጎራባች ቀበሌያት ጋር ግጭት ግን አሌ ፡፡ይሄ የአጎረባች ቀበሌያት ግጭት አንድ ድንበር ነው፡፡ በጉልበት ሴትን ልጅ ጠልፎ የራስ ሚስት ማድረግ ፣መንገድ ላይ ሰውን መግደል ፣መንግድ ላይ ሰውን መዝረፍ ፣በእንደዚህ ዓይነት ወንጀሎች ግጭት ይነሳል ፡፡ይሄ ግጭት ከተነሳ ብዙ ነፍስ ይጠፋል ብዙ የህዝብ ንብረትም ይጠፋል የቤት መቃጠል ይኖራል፡፡ እንግዲህ የዚህ ባህል እርቅ አፈታት እንደኩስሜ ባህል እንዲያስታርቁ ሽማግሎች ይመረጣል፡፡ከዚያ ለእርቁ አንድ ቤት ይቀመጣሉ፡፡ከዚያ መነሻ ምክንያቱን ትንታኔ ከሰው ያዳምጣሉ፡፡ይሄ ሁሉ ከተነገረ በኋላ ምን እናድርግ ብለው ወደ መፍትሄ ይመጣሉ፡፡ አሁን ያለፈው አልፏል ወደፊት ያለውን በማየት ወደ ግጭት አንገባም፡፡ ይሄ የሰው ዘርንም ያጠፋል፣ ድህነትንም ያስከትላል ፣እኛ ሽማግሌዎች እያለን ይሄ ግጭት ይከሰት እንዴ? በኋላ ይሄ ግጭት ስር ሰዶ እንዳያድግ ጫፉን ቆርጠን እናሳጥረው ይላሉ ፡፡ለማሳጠር ባህል አለ፡፡

የሀገር ባህል የሆኑት ሽማግሌዎች የተወከሉት ከብት ይገዛሉ፡፡ ከብቱን ከገዙ በኋላ ከዚያ ወገን የመጡ ሽማግሌዎችና ከእኛ ቀበሌ የተወከሉት ያንን ከብት ካረዱ በኋላ አንዱን ታፋ ወደዚያ በኩል ያሉ እነዛ ሽማግሌዎች ጫፉን ይይዛሉ፡፡ እዚህ ወደዚህ ያሉትም ደግሞ አንዱን ጫፍ ይይዛሉ፡፡ ሃላፊ የሆኑት የበላይ የጎሳ መሪዎች ሁለተኛ ይሄ ግጭት መፈጠር የለበትም በማለት ይሄንን ጭን በቢላዋ ማሃሉን ይመታሉ ከዛ በኋላ እርቅ ይሆናል፡፡ (ታደሰ ጉየታ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣የካቲት 20/2006 ፣26--28) ፡፡

በዚህ መልኩ ሽማግሌዎቹ ከተሰማሙ የሁለቱ ብሔረሰቦች መገናኛ ድንበር ላይ በጋራ ሆነው ትልቅ ከብት ያርዳሉ። ከብቱን ከባረኩ በኋላ በአንድ በኩል ያሉ የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች አንዱን ታፋ ወደ እራሳቸው ይስባሉ። በዚህ በኩል ያሉ ሽማግሌዎችም በተመሳሳይ እንዲሁ ያደርጋሉ፡፡

ከዚህ በኋላ የሁለቱም ብሔር ዋነኛ የጎሳ መሪዎች ጭኑን መሃል ለመሃል በቢላዋ በመከትከት ለሁለት ይሰነጥቃሉ። ሁለተኛ ይሄ ግጭት መፈጠር የለበትም ይሄ ግጭት የሚፈጥር አካል ካለ እንደዚህ ጭን ይስበረው ብለው ይራገማሉ፡፡ ከዚህ በኋላ የታረደውን በጋራ ይበላሉ ከሁለቱም ወገን የመጣውን ባህላዊ መጠጥ ጨቃ ይጠጣሉ፡፡ ከዚያም እርስ በእርስ ይመራረቃሉ ኑሯችን አንድ ይሁን ቋንቋችን አንድ ይሁን የእኛ ልጅ ከእናንተ ታግባ የእናንተ ልጅ ወደኛ ታግባ ተባብለውም ይመራረቃሉ ከዚህ በኋላ ቂማቸውን አስወግደው በሰላም ይኖራሉ፡፡

## 4.6. የኩሰሜ ባህላዊ የፍትህ ስርዓትና ሴቶች

በኩሰሜ ብሔረሰብ ዘንድ ሴቶች መክሰስም መከሰስም ይችላሉ፡፡ ሆኖም ይህን የሚያደርጉት ከሞራ ውጭ ቆመው እንጂ ሞራ ውስጥ መግባት በባህሉ ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ እንኳን በፍርድ ሂደት ጊዜ ይቅርና ባዶ ሆኖ እንኳ በውስጡ ሴት ልጅ ብታልፍ ታረክሰዋለች ተብሎ ይታመናል፡፡ይህን በማድረጓም የምትሰራው አይጣፍጥላትም መሃን ትሆናለች ብታረግዝም በወሊድ ጊዜ ጭንቋ ይበዛል ብለው ያምናሉ፡፡ ያነጋገርኳቸው መረጃ አቀባይ ወንዶችም ይህን በአንድ ድምፅ ይናገራሉ፤ ሴቶችም ባህሉ እንደሚገድባቸው አምነው ተቀብለዋል፡፡

ምን አለበት ውሰጥ ብትገባ እንዴት ታረክሰዋለች ለሚለው ጥያቄ ከመረጃ አቀባዮች አንዱ ኩሴ ኡሽረት ሴት ልጅ ተቀምጣ ስለምትሸና ነው ለዚያ ነው የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡ በድንገት ገብታ ብትገኝ ሞረው የመንፃት ስርዓት እስኪፈፀምበት ድረስ ረክሷል ተብሎ ስለሚገመት ማንም አይገባም አይገለገልበትም፡፡ በሞረው ውስጥ የገባችው ሴት ግን ማህበረሰቡ የሚለው ነገር

እንዳይደርስባት ፍየል አሳርዳ ደሙ በሞረው ላይ እንዲረጭ ታደርጋለች የዚህን ጊዜ ሞራውም እንደነፃ ይቆጠራል እርሷም ከእርግማኑ ነፃ ትሆናለች፡፡

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው የኩሰሜ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት ሴቷን ወደ ሞራው እንዳትገባ አገዳት እንጂ በደሏን በውጭ ሆና የማቅረብና የመከራከር መብቷን ግን አልነፈጋትም፡፡ እኔም በአገኘሁት የተፈጥሯዊ መቼት ምልከታ አራት ሴቶች ተካሰው መጥተው ጉዳያቸውን በየተራ በሚገባ ሲያስረዱና በሞራው የተሰበሰበው ሰውም ያለ ልክ ለወንዶቹ እንዳደረገው የፍርድ ውሳኔ አስተያየት ሲሰጥ ተመልክቻለሁ፡፡ ስለዚህም ገደቡን የቦታ ብቻ ነው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በቦታው ላይ የተጣለው ገደብ ብዙ ጊዜ ሴቶች ካልከሰሱ አልያም ካልተከሰሱ ወደ ሞራው እንዳይመጡ አድርጓቸዋል፡፡ ይሄ ደግሞ በፍርድ ሂደቱ ውስጥ ከወንዶቹ እጅግ ያነሰ ሚና እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡

ክስ በመመስረት እና ፍትህ በማግኘት ረገድ ግን ክልከላ እንደሌለ አንድ ሰው ከሶም ይሁን ተከሶ ጉዳዩን በሚገባ ማቅረብ እስከቻለ ድረስ እድሜው ትንሽ ነው ትልቅ ነው ተብሎ እንደማይከለከል አቶ ፈይሳ ቀዊቶ ያብራራሉ፡፡‹‹… መናገር መከራከር የሚችል ከሆነ ቆሞ ማስረዳት የሚችል በራሱ ነው የሚናገር ማስረጃም ከሆነ በራሱ ይቆጥራል…›› (ፈይሳ ቀዊቶ ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣20/06/06፣ገፅ33) ፡፡

## 5.ባህላዊና መደበኛ ፍርድ ቤት በኩሰሜ ብሔረሰብ

### 5.1.ሀገረሰባዊ የፍትህ ስርዓት ከመደበኛው ጋር በንፅፅር ሲቃኝ

ይህ ሀገረሰባዊ የፍትህ ስርዓቱን ከመደበኛው ጋር የተደረገ ንፅፅር በብሔረሰቡ አባለት በተሰጠ አስተያየት ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ ነው፡፡በንፅፅሩ የቀረቡ የማነፃፀሪያ ደረጃዎች በአጥኚው ለገለፃ እንዲያመች ይሰጥ እንጂ ሙሉ ሃሳቡ የብሔረሰቡ ነው፡፡

### 5.1.1.በኩሰሜ ብሔረሰብ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት

በአንድ ቀበሌ ብቻ ተከልሎ በሚኖረው የኩሰሜ ብሔረሰብ አንድ መደበኛ ፍርድ ቤት ብቻ ነው ያለው፡፡ ተዘዋዋሪ ልዩ ችሎት ግን በየጊዜው ይመጣል፡፡ ሆኖም በብሔረሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት አነስተኛ መሆኑንነው መረጃ አቀባዮቹ የሚናገሩት፡፡ ለጥናቱ መረጃ ሲሰበሰብ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ሰዎች ሁሉም ከዘመናዊው ይልቅ ለባሕላዊ የፍትህ ስርዓቱ እውቅና ይሰጣሉ፡፡ አንዳንዶቹ እንደውም ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት የሚሄድ ሰው እውነትን የያዘ አይደለም ብለው እንደሚያምኑ ይገልጻሉ፡፡

ከሀገር ሽማግሌዎቹ አንዱ አቶ ሉዳይደ ጉጋ ዘመናዊው ፍርድ ቤትበውሸትም ቢሆን ከሳሹ ሁለት ምስክሮች አምጥቶ ካስመሰከረ ያላጠፋውን ሊያስፈርድበት ይችላል ይላሉ፡፡እርሳቸው እንደሚሉት በቀበሌያቸው ፍርድ ቤት ቢኖርም ከኩሰሜዎች ይልቅ የሚጠቀሙት የአጎራባች ቀበሌዎችና ብሔረሰቦች ናቸው፡፡“ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማለት ተዘዋዋሪ ችሎት እዚህ አለ በወረዳው የተሰየመ ግን ከሌለ አጎራባች ቀበሌያት ናቸው እንጂ የሚያውቁት የእኛዎቹ ወደ እዚያ አይሄዱም” (ሉዳይደ ጉጋ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣20/06/06፣ገፅ28) ፡፡

## 5.1.2. ከጊዜና ከኢኮኖሚ አንፃር

የኩሰሜ ብሔረሰብ አባላት ዘመናዊ የፍርድ ስርዓቱን ከሚጠሉበት ምክንያት አንዱ ጊዜና ገንዘብን ይበላል ብለው ማመናቸው ነው፡፡ በባህላዊ የፍትህ ስርዓት አንድን ጉዳይ ወዲያው ዕልባት ላይ ያደርሳሉ ቢበዛ ሊቆይ የሚችለው ለሁለት ቀን ነው፡፡በመደበኛ ፍርድ ቤት ግን ለወራት መመላለስ ይኖራል። በዚህ ሳቢያም ስራ ይስተጓጐላል፣ ለዚህም ነው የብሔረሰቡ ተወላጅ መደበኛ ፍርድ ቤት ተበድሎም መንከራተት ገንዘብ መከስከስ ነው ብለው የሚያምኑት፡፡"በመንግስት ደረጃ ብትበደልም ተበድለህም ስራህን ታጣለህ ጊዜህን ታጣለህ ከዚያ ገንዘብህን ታባክናለህ ሰአትህንም ቢዚ አድርገህ ሜዳ ላይ እየተጉላላህ እየከሰርክ ትሄዳለህ ያንን የባህሉ አንድ አይደለም"(ተፈሪ ታደሰ ፣በተጠያቂው መኖሪያ ቤት ፣የካቲት 15/2006 ፣ 8) ፡፡ይህን የተፈሪን ሀሳብ አቶ ሉዳይዶ ጉጋም ይጋሩታል፡፡"አንዱ ዘመናዊ ህግን የሚጠሉበትና ባህላዊ ህግን የሚወዱበት ምክንያት የመንግስት ህግ ከሆነ ይቆያል የባህሉ ደግሞ ከሁለት ቀንና ሶስት አይበልጥም ለዚያ ነው ባህላዊም ህግ አፈታትን የሚወደው"(ሉዳይደ ጉጋ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣20/06/06፣28) ፡፡

በመረጃ መሰብሰብ ሂደት ያገኘኋቸው 32 የሚደርሱ የብሔረሰቡ ተወላጆች በሙሉ ከላይ ሁለቱ መረጃ አቀባዮች ያቀረቡትን ሃሳብ ይጋሩታል፡፡ እናም ኩሰሜዎች ባህላዊው ገንዘብንም ጊዜንም የማይጐዳ አድርገው ሲወስዱት መደበኛ ፍርድ ቤትን ግን በተቃራኒው ያስቀምጡታል፡፡

## 5.1.3. ትክክለኛ ፍርድን ከመስጠት አንፃር

ይህ አመለካከትም ከቀደመው አስተሳሰባቸው ጋር የተዛመደ ነው፣ እነርሱ እንደሚሉት መደበኛ ፍርድ ቤት አንድ ተበድያለሁ ያለ ሰው የሀሰት ምስክር መቁጠር ከቻለ ውሳኔ ሊያገኝ ይችላል በባህላዊው ግን በፍርድ ሂደት ውስጥ ብዙ ሰው ስለሚያሳትፍ በክርክሩ የውሸት ማስረጃ እንኳ ቢቀርብ ይጋለጣል፡፡ እና ሽማግሌዎችም በሀሰት የመሰከሩ ሰዎች አግኝተን በባህላዊ ፍርድ ቤት ቀርበው ለምን በሀሰት እንደመሰከሩ እንዲያብራሩ አድርገን በገንዘብ ተገዝተው

መመስከራቸውን ተናግረዋል፡፡ እኛም ይህን መረጃ አቅርበን ያዘጋነው ዶሴ አለ በማለት ይገልፃሉ ስለዚህም የዘመናዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በሚገባ ስለማያጣራ የፍርድ ውሳኔውም እንዲሁ የተዛባ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

> ወደ መንግስት የሚሮጠው አካል በዚህ ደሃ የሆነው ወደ መንግስት ሲሄድ ያኛው በውሸት የሚሮጠው ገንዘብም አለው በጀርባ አቃቢ ህግንም ዳኛንም በገንዘብ ሊታለል ይችላል ሊጉላላ ይችላል ደሃ ይረታል በዚያን ጊዜ ለዚህ የመንግስት ፍርድ ቤቶች ብዙ መጉላላት ከታች  ጀምሮ ሄደህ ሄደህ ፊትህ ለማግኘት የሚያጉላሉ ስለሆነ ጊዜ ይበላል ፊትህ ሊገኝ ላይገኝም ሰለሚችል ይሄኛው የባሕል ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ አግኝቶ ፊትህ ተገኝቶበት ሰውየው ፊትህ አግኝቶ ወደ ልማት ይመለሳል ለዚህ ነው ወደ ባህል ህግ የሚያደሉት፡፡ የሚወደው፡፡(ሉዳይደ ጉጋ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣20/06/06፣ገፅ29)

## 5.1.4.ዘላቂ እርቅን ከማስገኘት አንፃር

የኩሰሜ ብሔረሰብ አባላት በዋናነት በዘመናዊውና በባህላዊ ፍርድ ቤት መካከል አለ ብለው የሚያምኑት ልዩነት ዘላቂ እርቅን ከመፍጠር አንፃር ያለውን ነው፡፡

ዘመናዊ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ባለው ላይ ውሳኔ ከመስጠት አልፎ በበዳይና ተበዳይ ወገን መካከል  ስለተፈጠረው እርስ በእርስ የመፈላለግ የበቀል ስሜት ምንም አይነት ተግባር አይፈፅምም፡፡ ስለዚህ ዘላቂ እርቅን ከማምጣት አንፃር ሲቃኝ ምንም ሚና የለውም፡፡ ይህንን ጉዳይ ከመረጃ አቀባዮቹ አንዱ እንዲህ ይገልፁታል፡፡

> ተጠልተህ ትኳረፋለህ ሳትነጋገር ትቀራለህ፡፡ መንግስት አስታርቆህ በፍርድ ቤት ታርቀህ  ከተበደልክም የተበደልከውን ካሳ ተቀብለህ ሂዱ ተባብላችሁ ልትሄዱ ትችላላችሁ ግን ተኮራርፋችሁ ፡፡በባሂሉ አባ ዲባው  መጥቶ ካስታረቃችሁ ግን እርቃችሁን የሚመለከት አነድነገር አባ ዲባው ይሰጣችኋል፡፡ ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ የተለመደው፡፡ ጨው ነው ጨው ይወስዳል ምግብ መመገቢያው ሳህን ገበታ ምናምን ከእንጨት ተጠርቦ

የሚሰራ አለ እርሱ ስር ያስቀምጣል ከጨው ለሁለታችሁም ያቀምሳችኋል፡፡ ከአንድ ጨው ሁለታችሁም በጋራ ትቀምሳላችሁ፡፡ ያ ማለት ምን ማለት ነው ታርቃችኋል፡፡ ማንኛውንም ነገር ትረሰዋለህ ከዚህ በፊት የነበረውን ይሄ ባህላዊ መሪ የሚያስታርቀው እርቅ ነው ማለት ነው። በዚያ ሰዐት ትክክለኛ እርቅ መሆነን በእርሱ ታረጋግጣለን ትላንት የተጣላችሁበትን ነገር አታስታውሰውም ፡፡ በመንግስት ግን ታርቀናል ብለህ አንተ በፍርድ ቤት አንዱ ረቶ አንዱ ተረቶ ይሆናል፡፡ በባህል ፍርድ ቤት የእርቅ ስነስርዓት ግን አንድ ረቺ አንድ ተረቺ የሚሆንበት ነገር የሚባል ነገር የለም፡፡(ጌታቸው ዲምባ ፣ጊዶሌ ገቢዎች ፅ/ቤት፣17/6/06 ፣ገፅ 14--15)

ለዚህ ነው የብሔረሰቡ አባላት ደረቅ ወንጀል ነው አናየውም ያሉትን ግድያ እንኳን በመደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሰጥቶ ገዳይ ከተፈረደበት በኋላ በሽማግሌ አማካኝነት የገዳይና የሟች ቤተሰቦች ለበቀል እንዳይፈላለጉ የእርቅ ስነ ስርዓት እንዲከወን የሚያደርጉት፡፡

በመሆኑም ዘላቂ እርቅንና ሰላምን በመፍጠር ረገድ የባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቱ የጎላ ሚና ያለው ነው ሁሉንም ግጭቶች ሲፈታ ዋና ዓላማው አድርጎ የሚንቀሳቀሰው ዘላቂ ሰላም ማስፈን እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በብሔረሰቡ አባላት ሞራውን ለመምራት የሚመረጠው አባ ዲባም ዋናው ስራ ይሄ ነው፡፡ የስሙ ትርጓሜ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው፡፡

አባ ዲባ ማለት አጠቃላይ የህዝቡን ሰላም የሚጠብቅና ህዝቡን የሚያስተዳድር የሚያስታርቅ ማለት ነው በአካባቢው ያለውን ባህል እየጠበቀ የሚያኖር ማለት ነው፡፡ (ሉዳይደ ጉጋ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣20/06/06፣ገፅ25)

## 5.2.ባህላዊና መደበኛው የፍትህ ተቋማት ያላቸው ግንኙነት

### 5.2.1.ባህላዊና መደበኛው የፍትህ ተቋማት ተባብሮ ከመስራት አንፃር

በኩሰሜ ብሔረሰብ ዘንድ ለመደበኛው ፍርድ ቤት ያለ አመለካከት ቀደም ሲል እንዳየነው ያነሰ ነው፡፡ ነገር ግን በመደበኛው ፍርድ ቤት ነው የሚታየው ተብሎ ለተወሰነው ግድያም ይሁን በሌሎች የብሔረሰቡ አባል ይሁነኝ ብሎ በመደበኛው ፍርድ ቤት ክስ በመሰረተባቸው ጉዳዮች ላይ ተባብረው ይሰራሉ፡፡

ግድያን በተመለከተው በጥናቱ ክፍል በጥልቀት እንዳየነው በገዳይ ላይ ፍርድ ቤቱ ብይን ሰጥቶ በእስር እንዲቀጣ ሲያደርግ የገዳይና ሟች ወገኖች ዳግም ለበቀል እንዳይፈላለጉ አድርጎ ዘላቂ ሰላም የማውረድን ተግባር ደግሞ ባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ ይሰራሉ፡፡ ይህ አንድ ተደጋግፈው ለመስራታቸው ማሳያ ነው፡፡

ሌላው በባህላዊ የፍትህ ተቋሙ በሽምግልና ከሚያገለግሉ የብሔረሰቡ አባላት ዘንድ ተውጣጥቶ የተቋቋመ የሀሰት አጣሪ ኮሚቴ መኖሩ የሁለቱን ተባብሮ መሰረት በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡ ብሔረሰቡ በሚኖርበት ቀበሌ ካሉ ዘጠኝ ወረዳዎች ሁለት ሁለት ሽማግሌዎች ተውጣጥተው በህዝብ የሚሰየመው ይህ የሀሰት አጣሪ ኮሚቴ ዋነኛ ተግባሩ በመደበኛ ፍርድ ቤት በሀሰት ተከስሻለሁ እነ እገሌም በሀሰት መስክረውብኛል ያለ የብሔረሰቡ አባል ወደ እነርሱ መጥቶ በደሉን ሲስረዳ ጉዳዩን በጥልቀት መርምሮ መፍትሄ መፈለግ ነው፡፡ ስማቸው በቀበሌ አማካኝነት ስለሚተላለፍ የመደበኛ ፍርድ ቤት አካላትም ያውቋቸዋል፡፡ በተለይ አቃቢ ህግ፡፡

"ከአቃቢ ህጎች ጋር አዎ ይሰራሉ ጉዳዩ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲጣራ ሲደረግ አብረው ይሰራሉ፡፡"(ባዩሽ አምባዬ፣በቀበሌው ፍትህ ፅህፈት ቤት፣22/06/06፣ገፅ37)

እነርሱም ተበድያለሁ የሚል ሰው ሲገጥማቸው ከያሉበት ተጠራርተው በመገናኘት በሀሰት ከሷል ያሉትን ሰውም ሆነ መስካሪዎቹን በመጥራት እውነታውን ያጣራሉ፡፡ ትክክለኛውን እውነት ሲያገኙ አመልካቹ እንደገለፀው ክሱም ሆነ ምስክሩ የሀሰት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ፋይሉን እንዲዘጋ ምስክሮቹም ሀሰተኞች መሆናቸውን ገልፀው

ለመደበኛ ፍርድ ቤቱ ያቀርባሉ፡፡ ፍርድ ቤቱም ሰምቷቸው ፋይሉን ይዘጋል ፡፡ የሐሰት አጣሪ ሽማግሌዎች ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ ታደሰ ጎይታ ስለ ኮሚቴው ያብራሉ፡፡

> አንተ በውሸት የከሰስክ እንደሆነ የተከሰሰው ግለሰብ እርሱ ወደ እኛ ይቀርባል፡፡ እኔን በሀሰት ከሶል እነ እከሌ ሶስት ሰዎች ሄደው በሀሰት መስክረዋል፡፡ እኛ በዚህን ጊዜ ጥሪ እናደርግና ወደ አንድ ቦታ እንሰበሰባለን፡፡ መስካሪዎቹን እናቀርብና ከሳሹንም እናቀርባለን እና እውነታውን እናጣራለን ፡፡እውነታውን እስክናጣራ ጊዜ ይወስዳል እንጂ አንተውም፡፡ ዛሬ ካሸነፈ ለነገ እንቀጥላለን፡፡ ነገም ካሸነፈ ውጤት እስከምናገኝ አናቋርጥም፡፡ ከጨረስን በቃ አስታርቀናል ጨርሰናል አጣርተን ደርሰንበታል ውጤቱ ይሄ ነው ብለን እከሌ በሀሰት ነው የከሰሰው ብለን ለፍርድ ቤቱ እንገልፃለን፡፡ ፍርድ ቤቱ ይቀበላል ከፍተኛ ፍርድቤቱም ይሁን ወረዳ ፍርድ ቤት ይቀበላል(ታደሰ ጎይታ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣20/06/06፣ገፅ31) ፡፡

ከዚህ ነገር የምንረዳው የመደበኛ ፍርድ ቤቱና የባህላዊ የፍትህ ተቋሙን መደጋገፍን ብቻ አይደለም፡፡ ከላይ በንፅፅር ያየነውና በተቀባይነት ደረጃ ካላቸው ልዩነት አንፃር ህዝቡ ለባህላዊው የፍትህ ስርዓት የሚሰጠው ቦታ የላቀ መሆኑንም በሚገባ ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ከመረጃ አቀባዩ ገለፃ እንደተረዳነው መደበኛ ፍርድ ቤቱ በሀሰት መስካሪዎች ሳቢያ በተዛባ መረጃ የተሳሳተ ፍርድ የሚሰጥበት አጋጣሚ ሲኖር ባህላዊው ግን ሁሉን ነገር በሚገባ አጣርቶ አስተማማኝ ፍትህ ይሰጣል ይህም ህብረተሰቡ በባህላዊ የፍትህ ስርዓት እምነት እንዲኖረውና የተሻለ ዳኝነት አገኛለሁ ብሎ እንዲያስብ አድርጎታል፡፡

## 5.2.2 ባህላዊው የፍትህ ስርዓት ለመደበኛው ፍርድ ቤት ብይን የሚያደርገው አስተዋፅኦ

የኩሰሜ ብሔረሰብ እየተገለገለበት ያለው ባህላዊው የፍትህ ተቋም ከርሱ አልፎ የመደበኛ ፍርድ ቤት ብይን በተስተካከለ መረጃ ላይ ተመስርቶ ብይን እንዲሰጥ ቀደም ሲል በጠቀስነው የሀሰት አጣሪ ኮሚቴ አማካኝነት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከት ባህላዊው የፍትህ ተቋም የመደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን የማሻር አቅምም አለው በብሔረሰቡ ዘንድ እንዲህ ዓይነት ገጠመኝ እንደነበር በመረጃ አቀባይነት ከተሳተፉት አንዱ ፈይሳ ቀዊቶ ይገልፃሉ። በቅርብ ጊዜ የተፈፀመ ገጠመኝን በማሳያነት በመጥቀስ፡፡

ክሱ ከጠለፋ ጋር የተያያዘ ነው ፡፡ ነገር ግን ሴቲቱ ወዳ ፈቅዳ ከወንድ ጋር አብራ ሄደች ኋላ ግን ቤተሰቦቿን ፈርታ በግድ ጠልፏት እንደሆነ ተናገረች። ቤተሰቦችም ወዳ መሄድን እያወቁ ተጠልፋብናለች በሚል ከሰሱ ጠለፋውን አየን ያሉ ሰዎችም በሀሰት መሰከሩ ሰውየውም በፖሊስ ተይዞ ፍርድ ቤት ቀረበ ምስክሩ ተሰምቶ ለመረጨሻ ፍርድ ከተቀጠረ በኋላ ግን የባህላዊ ሽማግሌዎች ገብተው ያመጡትን ለውጥ እንዲህ ይገልፁታል፡፡

> በሀሰት ፖሊስ ጣቢያ ከከሰሱ በኋላ የውሸት ማስረጃ ገዙ አስመስክረው ዶሴው ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተላለፈ ከዚያ ማስረጃውን ያዝን እዚህ አስመጣናቸው አዎ እውነት ነው ተገዝተን ሄደን በውሸት መስክረናል አሉ፡፡ እኛ ከዚህ ደብዳቤ ፅፈንና እነሱ ባለፈው የመሰከሩት እና አሁን ዛሬ የሚናገሩት ቃል አያይዘን ወደ ፍርድ ቤት ላክን ፍርድ ቤት ደግሞ አሁን ወደ ውሳኔ የተቃረበውን ከዛ ዶሴውን ዘጋ (ፈይሳ ቀዊቶ፣ጋቶ ጤና ጣቢያ፣20/06/06፣ገፅ30) ፡፡

ይህ አስረጅ የሚያሳየን ባህላዊው የፍትህ ተቋም ለመደበኛው ፍርድ ቤት ብይን ስኬት የጎላ ሚና እንዳለው ነው፡፡ ከግድያ ጋር በተያያዘም ባህላዊው የፍትህ ተቋሙ የገዳዩን ማንነት አጣርቶ ለመደበኛው ፍርድ ቤት በማቅረብ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

በመሆኑም ባህላዊው የፍትህ ተቋም ለዘመናዊው የመደበኛ ፍርድ ቤት ስራ የተሳካ መሆንና እውነተኛ ብይን እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ በሁሉም የክስ ሂደቶች ላይ የሚገለፅ ነው በይባልም በተወሰኑት ላይ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ስለዚህም የባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ በዘመናዊው የፍትህ ስርዓት የተወሰኑ ውሳኔዎችን የማስገልበጥ አቅም አለው፡፡ በተቃራኒው ግን መደበኛ ፍርድ ቤት በባህላዊው የተወሰነውን ከማፅናት በዘለለ በባህላዊው የተወሰነውን ውሳኔ የሚገለብጥ ብይን የሰጠበት አጋጣሚ በኩሰሜ ብሔረሰብ ዘንድ ተከስቶ እንደማያውቁ መረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ፡፡

መደበኛ ፍርድ ቤቱ እንደውም አንድ አንዴ ከመደበኛው ይልቅ በባህላዊው የፍትህ ስርዓት የተሻለ ብይን ይኖራል ብሎ የሚያስበውን ጉዳይ ወደ ባህላዊው የፍትህ ስርዓት የሚመልስበት ሁኔታ  እንዳለ በጋቶ ቀበሌ የዳኛ ረዳት ኦፊሰር ባዩሽ ትናገራለች፡፡

> እኛ ደግሞ ለምሳሌ ጉዳት አድርሶ የመጣ በእርቅ እንዲጨረሱ እንትን እንላለን ከአቅም በላይ የሆነ ለምሳሌ ጠለፋ የአካል ጉዳት የሆኑ ወንጀሎች ብቻ ናቸው። እንደዚህ ቅጣት እንትን የሚባለው ከዛ በተረፈ በእርቅ እንደጨረሱ አሁን ለምሳሌ የእጃ እልፊት ስድብ ምናምን ቀላል የሆኑ እንትኖችን በሽማግሌ እንዲጨርሱ ነው የምናደርገው (ባዩሽአምባዬ፣በቀበሌው ፍትህ ፅህፈት ቤት፣22/06/06፣37) ፡፡

መደበኛው ፍርድ ቤትም ለባህላዊው እውቅና ሰጥቶ ከኔ ይልቅ በእነርሱ መፍትሄ ያገኛል የሚላቸው ጉዳዮች መምረጡ በመግባባት የመስራታቸው አንድ ማሳያ ነው፡፡

# 6.ማጠቃለያና ይሁንታ

## 6.1.ማጠቃለያ

የኩሰሜ ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንዳየነው በከፍተኛ ደረጃ ማህበረሰቡን አሳታፊ ነው፡፡ የባህላዊ የፍርድ ተቋማቱን የሚመራው የሞራው መሪ አባ ዲባ የሚመረጠው በህዝብ ይሁንታ ሲያገኝ መሆኑ ከተመረጠ በኋላ የፍትህ ስርዓቱን በዋናነት የመምራት ስልጣን በእጁ ቢሆንም ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በፍርድ አደባባይ የተሰበሰቡት ሰዎች የቅጣት አስተያየት እንዲሰጡ ማድረጉ የማህበረሰቡ ተሳትፎ የጎላ ለመሆኑ ዋነኛ ማሳያዎች ናቸው፡፡

ህብረተሰቡ በፍትህ ስርዓቱ እንዲህ ያለ ተሳትፎ ማድረጉ ደግሞ አመኔታውን ያጠናከረ ሆኗል፡፡ ለዚህም ነው ወደ ዘመናዊ ፍርድ ቤት መሄድን በሀሰት ፍርድ ለማግኘት እንደ ውሸታምነት ወደ ባህላዊው የፍትህ ተቋም መምጣትን እንደ ሀቀኝነት እየቆጠረ ያለው፡፡

ይህ አመለካከትና ተሳትፎ ደግሞ የብሔረሰቡ ባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት ዋነኛ የጥንካሬ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ከዚያ በተጨማሪ ዘላቂ ሰላም በማውረድ እርቁን የማያዳግም በማድረግ ረገድ በብሔረሰቡ ዘንድ ከዘመናዊው ልቆ መገኘቱም የጥንካሬው አንድ መገለጫ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የኩሰሜ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት የሴትን ልጅ ተሳትፎ በቦታ መገደቡ እንደ ድክመት ይነሳበታል፡፡ ምንም እንኳ ከሞራው ቅጥር ራቅ ብላ መክሰስ ፣ ለተከሰሰችበት ጉዳይ ምላሽ መስጠት ፣ መከራከር የምትችል ቢሆንም ከርሷ ጉዳይ ውጪ እንደ ወንዶች በሌሎች የብሔረሰቡ አባላት የፍርድ ሂደት ላይ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት አለመቻሏ በዘመናዊ ፍርድ ቤት አንድ ሰው ከችሎት ህግ ውጪ ሲሆን ችሎት ደፍረሃል ተብሎ እንደሚቀጣ እሷም ከሞራው መሃል በመግባቷ መቀጣቷ  የፆታ መድሎ መኖሩ የባሕላዊ ፍትህ ስርዓት ዋነኛ ድክመት ነው፡፡

በጥቅሉ ሲታይ ግን ማህበረሰባዊ ተቀባይነቱ የጎላ ፤ የብሔረሰቡን አብሮ በሰላም የመኖር ህልውናን ማስጠበቅ የቻለ ስርዓት ነው ማለት እንችላለን ፡፡ነገርግን በሂደት ለውጦችን እያሰተናገደ መምጣቱን ጥናቱ አሳይቷል፡፡የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች አንዱ የደቡብ ክልል የብሔረሰቦች ፋይል የተሰኘው መፃሃፍ ስለብሔረሰቡ የግጭት አፈታት ስርአት ሲያትት የገደለ የብሔረሰቡ የወቅቱ ንጉስ ዘንድ ይሄዳል የሚል ነገር አስቀምጧል ፡፡ሆኖም በጥናቱ እንደታየው አሁን ንጉሳዊው ስርዓት ስለሌለ ሰው የገደለ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድቤት እንዲታይ ሆኗል ፡፡አሁንም ግን ደም በተቃቡት ወገኖች መካከል ዘላቂ እርቅ ማውረድ የባህላዊ ግጭት አፈታት ስርአቱ ተግባር ሆኖ መቀጠሉ ታይቷል፡፡

### 6.2.ይሁንታ

1. በኩሰሜ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት ይሁነኝ ተብሎ ዘመናዊውን ፍርድ ቤት ለማገዝ የተቋቋመው ኤርባ ኔሃምባያ የህሰት አጣሪ ኮሚቴ ከሁሉም በላይ ይሁንታ የሚቸረው ነው፡፡

በመላ ሀገሪቱ ባሉ ዘመናዊ የፍትህ ተቋማት በተሳሳቱ ማስረጃዎች ሳቢያ የሚሰጡ የተዛቡ ፍርዶችን ከማስቀረት አንፃር የሚኖረው ሚና ሲታይ በአንድ የኩሰሜ ብሔረሰብ ዘንድ ብቻ ተወስኖ የቀረውን ይህን ልማድ ለሌሎች ማዳረስ ቢቻል የሚል ሀሳብን ያጭራል፡፡ይህን ለማድረግ ደግሞ የፍትህ ስርዓቱን ለማዘመንና ትክክለኛ ፍርድ የሚሰጥባቸው ተቋማት ለማድረግ የሚሰራው ፍትህ ሚኒስቴርም ሆነ ሌሎች ፖሊሲ አውጪዎች ስለ ጉዳዩ ማወቅና እንደምን ወደ ሁሉም አካባቢዎች ማስፋት ይቻላል የሚለውን በጥልቀት ቢያጤኑት መልካም ነው፡፡

2.በእርቅ ስነስርአቱ የሚጣል ገንዘብ ቅጣት ለአካባቢ ልማት መዋሉም ይሁንታ ሚቸረው ጉዳይ ነው፡፡

3. የብይን አሰጣጥ ሂደቱ ሁሉን አሳታፊ መሆኑም አንድ በመልካም ጎኑ የሚነሳ ነው፡፡ህብረተሰቡን በባህላዉ የእርቅ ስርአቱ ውስጥ ያለውን የኔነት ስሜት ያጎላል ፡፡

4. ባህላዊ የእርቅ ስነስርአቱ ለሚያስተላልፈው ውሳኔ አልገዛም ያለ የብሄረሰኑ አባል መገለል እንዲደረስበት መደረጉ ምንም እንኳ በዘመናዊው የፍትህ አካሄድ ከሰባዊ መብት ረገጣ የሚቆጠር ቢመስልም ለባህላዊ የፍትህ ስርአቱ ግን የዘላቂነቱ ማረጋገጫ የመከበሩም ዋስትና በመሆኑ ይሁንታ የሚቸረው ነው፡፡

## ዋቢ መፃህፍት


ተመስገን ታደሰ፡፡ "ራጋ ሚጋ የግጭት አፈታት ስርአት በአላባ" የኤምኤ ድግሪ ማሚያ ፅሁፍ፡፡አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፤የኢትዮጵያ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣2005፡፡

አብርሃም ታደሰ፡"ህገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሔረሰብ" የኤምኤ ድግሪ ማሚያ ፅሁፍ፡፡አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፤የኢትዮጵያ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣1999፡፡

አንዱአለም አባተ ፡፡ "ግጭት አፈታት በመኤኒት ብሔረሰብ" የኤምኤ ድግሪ ማሚያ ፅሁፍ፡፡አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፤የኢትዮጵያ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣2004፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1993፡፡

የወንደሰን አውላቸው ፡፡"የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደር የግጭት አፈታት" የኤምኤ ድግሪ ማሚያ ፅሁፍ፡፡አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፤የኢትዮጵያ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣1998፡፡

የደቡብ ክልል ብሔረሰቦችምክርቤት፣<u>የደቡብብሔሮችብሔረሰቦችናሕዝቦችፕሮፋይል</u>፣ ሀዋሳ፣ ፍቅረ ሰላም ማተሚያቤት፣ 2001፡፡

ገብሬ ይንቲሶ፣ ፈቃደ አዘዘ፣ አሰፋ ፍስሀ፤ <u>ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዐቶች</u> በኢትዮጵያ፤አዲስ አበባ ፣2004 ፡፡

ፈቃደ አዘዘ፣ <u>የስነ ቃል መምሪያ</u> አዲስ አበባ፤አልፋ አሳታሚዎች፣1991 ዓ.ም።

______________፣ቴምፕሌት በአማርኛ፣ የካቲት 18 2003

*Blake, R.R., Shepard, H.A., & Mouton, J. S. Managing intergroup conflict in industry. Houston, Texas: Gulf, 1964.*

Bender M.L.and etal (eds)Languge in Ethiopia,London Oxford Universty Press, 1976.

Coser, Lewis A. The functions of social conflict 1sted.New York:free press.1964.

*Deutsch, M. and Coleman, P. (eds.). The handbook of conflict resolution: Theory and practice.San Francisco: Jossey-Bass, 2000.*

*Fisher, R.J. The social psychology of intergroup and international conflict resolution. NewYork: Springer-Verlag, 1990.*

Glassie, Henry. Tradition.Philadelphia: Univ. of Pennsylvania Press, 1995.

Imobighe, Thomas A. The OAU(AU)and OAS in Regional conflict management a complete assessment,spectrum book limited, 2003.

*Katz, D. Nationalism and strategies of international conflict resolution. In H.C. Kelman(ed.), International behavior: A social psychological analysis. New York: Holt,Rinehart & Winston, 1965.*

*Kriesberg, L. Constructive conflict: From escalation to resolution. Lanham, MD: Rowman &Littlefield, 1998.*

Lamber and Myers ,Activities for Conflict Resolution ,Human Resourse Devlopment Press ,US and Canada, 1999.

Lesiu wolf English-Amharic Context Dictionery Belgium, sowtiz, 1973.

*Marth C.Sims,and Marthine Sthephens.LIVING FOLKLORE An Introduction to the study of people and Their Traditions .logan,utha:* Utah State University Press,2005

*Schmid,Alex , The Function of Social Conflict :New York free press: 2000*

*Tadele Tayeso,2006, "Ethino-historic study of the kuseme people"SNNPR Bureau of Culture and Tourism:Hawassa.*

## *የዋና መረጃ አቀባዮች ግለ-ታሪክና የተመረጡበት መስፈርት*

### *1. ሉዳይዶ ጉጋ*

አቶ ሉዳይዶ ጉጋ የ65 ዓመት የእድሜ ባለጸጋ ሲሆኑ የ6 ልጆች አባት ናቸው፡፡ የሚተዳደሩት በግብርና ነው፡፡ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ናቸው፡፡ አቶ ሉዳይዶ ጉጋ ዘመናዊ ትምህርት ባይኖራቸውም ከአባቶቻቸው የሰሙትን የብሔረሰቡን ታሪክ እርሳቸው ከኖሩበትና ካዩት ጋር በመደባለቅ በሚገባ የብሔረሰቡን ባህላዊ ክንውኖች የሚገልፁ የሀገር ሽማግሌ ናቸው፡፡

ብሔረሰቡ ከሌላ ብሔረሰብ ጋር ሲጋጭም ሆነ እርስ በእርስ ከበድ ያሉ ጠቦች ሲፈጠሩ ለመዳኘት ከዋናው አባ ዲባ ጋር በመሆን ከሚሰሩት የሀገር ሽማግሌዎች አንዱ ናቸው፡፡ አሁን ከጤና እና ከእድሜ መግፋት ጋር በተያያዘ አባ ዲምባነቱን ቢተውትም ለብዙ ዓመታት አባ ዲምባ ሆነው አገልግለዋል፡፡

ስለዚህ ስለብሔረሰቡ ታሪክም ሆነ ስለባህላዊ ስርዓቱ በተሻለ የሚገልጹ ሆነው በመገኘታቸው በብሔረሰቡ ዘንድ ክብርና ተቀባይነት ካላቸው ሽማግሌዎች አንዱ በመሆናቸው በቁልፍ መረጃ አቀባይነት ተመርጠዋል፡፡

### *2. አቶ ገዳይቶ ከመኑ*

አቶ ገዳይቶ ከመኑ የሰባ ዓመት የእድሜ ባለጸጋ ሲሆኑ አራት ልጆች አሏቸው፡፡ ዋነኛ መተዳደሪያቸው ግብርና ቢሆንም አሁን ግን ከእድሜ መግፋት ጋር በተያያዘ እርሻ አያርሱም፡፡ ሆኖም በልጆቻቸው እያሳረሱ ይጠቀማሉ፡፡ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ናቸው፡፡ በኩስሜ ብሔረሰብም ዘንድ ክብር ካላቸው ታዋቂ ሽማግሌዎች አንዱ ናቸው፡፡

ልክ እንደ ሉዳይዶ ጉጋ ሁሉ ዋነኛ የሀገር ሽማግሌ በመሆን በአካባቢው በደንብ ይታወቃሉ፡፡ በሞራ ውስጥ ባህላዊ የእርቅ ሥነ ሥርዓት ሲካሄድ አባዲባውን በማማከር ከሚሰሩ ሽማግሌዎች አንዱ ናቸው፡፡ በዚህ የተነሣ ለጥናቱ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ሆነው ተመርጠዋል፡፡

### *3. በጎሮ ጠሊፉ*

አቶ በጎሮ ጠሊፉ ባለትዳርና የ8 ልጆች አባት ናቸው፡፡ እድሜያቸውም 50 ሲሆን በእርቅ ስነስርዓት ውስጥ ከሚሳተፉ ታዋቂ የብሔረሰቡ አባላት አንዱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በቁልፍ የመረጃ አቀባይነት ያስመረጣቸው የፕሮቴስታንት እምነት መሪ በመሆናቸውና ከብሔረሰቡ ደግሞ አብዛኛው የዚህ እምነት ተከታይ በመሆኑ የተሻለ ተደማጭነት ስላላቸው ነው፡፡ በእርቅ ስነ ስርዓትም ይህንኑ ውክልናቸውን ይጠቀሙበታል፡፡

### *4. ታደሰ ጐይታ*

አቶ ታደሰ ጐይታ ሁለት ሚስቶች አሏቸው፡፡ ከሁለቱም 7 ልጆች አሏቸው፡፡ በቀበሌው ሃብታም ከሚባሉት አርሶአደሮች ቀዳሚ ናቸው፡፡ እምነታቸው ፕሮቴስታንት ነው፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ ተሰሚነት ያላቸው ሰው ስለሆኑ በተደጋጋሚ በሀገር ሽማግሌነት ይመረጣሉ፡፡ አሁንም መደበኛ ፍ/ቤቱና ባህላዊ የእርቅ ሥነ ሥርዓቱን በጋራ የሚጠቀሙበት 16 አባላት ያሉት የሀሰት አጣሪ ኮሚቴ አባል ናቸው፡፡

ይህ በብሔረሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነትና በሀሰት አጣሪነት ውስጥ አባል መሆናቸው በዋቁልፍ መረጃ አቀባይነት አስመርጧቸዋል፡፡

### *5. ፊይሣ ቃዊቶ*

አቶ ፊይሣ ቃዊቶ በእድሜ ቢታይ ከሀገር ሽማግሌዎቹ አነስተኛ ናቸው፡፡ በቁልፍ መረጃ አቀባይነት ያስመረጣቸው የኩስሜ ብሔረሰብ አባላት ዋንኛ መኖርያ የሆነው የጋቶ ቀበሌ አስተዳዳሪ ወይም ሊቀመንበር በመሆናቸው ነው፡፡ ይህ ሥልጣናቸው በተደጋጋሚ ከኅብረተሰቡ ጋር ስለሚያገናኛቸውና በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚከሰቱ ተደጋጋሚ የግጭት አይነቶችን ስለሚለዩ በመረጃ አቀባይነት ተመርጠዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በብዙ ሞራዎች ላይ ስለሚሳተፉ የባህላዊ ሕግ ሥነ ሥርዓቱን በሚገባ መግለጽ ይችላሉ በሚል ነው የተመረጡት፡፡

*6. አቶ ተፈሪ ታደሰ*

አቶ ተፈሪ ታደሰ እሜው 35 ነው፡፡ የትምህርት ደረጃ በቀድሞው 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ነው፡፡ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ነው፡፡ ዋነኛ መተዳደሪያው ግብርና ነው፡፡ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ሲሆን፣ በሰባኪነትም ያገለግላል፡፡ ይህም በህብረተሰቡ ዘንድ ከእድሜ እኩዮቹ በተሻለ ተቀባይነት እንዲኖረው አድርጓል፡፡ አባቱ አቶ ታደሰ ጉይታ በእርቅ ስነ ስርዓቱ ውስጥ ዋናና ሽማግሌ በመሆን ስለሚሳተፈ እርሱም ስለባህላዊ የእርቅ ስነ ስርዓቱ በቂ ግንዛቤ አለው፡፡ በቀጣይም ሥርዓቱን በመሪነት ይቀበሉታል ተብሎ ከሚጠበቁት ሰዎች መካከል ስለሚመደብ በቁልፍ መረጃ አቀባይነት ተመርጧል፡፡

*7. አቶ ጌታቸው ዲምባ*

አቶ ጌታቸው በአካውንቲ ዲግሪ አለው፡፡ እድሜው 36 ሲሆን በደራሼ ወረዳ የገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ ነው፡፡ ዋነኛ መኖሪያው በጊዶሌ ከተማ ቢሆንም በየጊዜው እየሄደ በሞራ ውስጥ የሚካሄዱትን የእርቅ ሰነ ስርዓቶች ይከታተላል፡፡ በሞራው ለተሰበሰቡ ሰዎችም የእለቱ የእርቅ ስነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ ስለ ግብር ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስተምራል፡፡ በፍርድ ሂደቱም ነገሮችን አገናዝቦ ለአባ ዲምባው አስተያየት ይሰጣል ስለሚባል በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አለው፡፡ በቀጣይም የባህላዊ የእርቅ ስነ ስርዓቱን ተረካቢ ናቸው ከሚባሉት አንዱ በመሆኑ ለቁልፍ መረጃ አቀባይነት ተመርጧል፡፡

*8. አቡዴ በራንጉዴ*

ወ/ሮ አቡዴ በራንጉዴ የ60 ዓመት ዕድሜ ባለፀጋ የቤት እመቤት ናቸው፡፡ ስድስት ልጆችም ወልደዋል፡፡ በቁልፍ መረጃ አቀባይነት ያስመረጣቸው ባህላዊ የእርቅ ስነ ስርዓቱ ሲከናወኑም ሆነ በማንኛውም ሰዓት ሴቶች ከሞራ ውስጥ አይገቡም ስለሚባል ስለዚህ ጉዳይ እንዲያብራሩና ሴቶቹ ጉዳዩን እነዴት ይመለከቱታል የሚለውን ለመቃኘት እንዲቻል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሴቶች በዳይም ሆነ ተበዳይ ሆነው ሲቀርቡ የባህላዊ የሕግ ሥነ ሥርዓቱ ሴቶችን

እንዴት ይመለከታል የሚለውን እንዲያብራሩ ነው፡፡ በሞራ ውስጥ ገብተው ሲገኙ ምን አይነት ቅጣት ይጣልባቸዋል ለሚለውም ማብራሪያ ይሰጣሉ በሚል ተመርጠዋል፡፡

*9. ባዩሽ አምባዬ*

ወ/ሮ ባዩሽ አምባዬ የ28 ዓመት ወጣት ስትሆን በሕግ ዲፕሎማ አላት፡፡ ስለዚህም በቀበሌው ባለው መደበኛ ፍ/ቤት የጸኛ ረዳት ሆና እየሰራች ነው፡፡ትዳር አልመሰረተችም ፡፡ ይህ ያለችበት ቦታ በባህላዊውና በመደበኛው የፍትህ ስርአት ውስጥ ያለውን ግንኙነት እንድታብራራ ወደ እነርሱ የሚመጡትን የክስ አይነቶች እንድትገልጽ ያስችላታል በሚል በቁልፍ መረጃ አቀባይነት ተመርጣለች፡፡

*10.ኩሴ ኡሽረታ*

ኩሴ ኡሽረታ የ25 ዓመት ወጣት ሲሆን እስከ 8ኛ ክፍል ተምሯል፡፡ ቤተሰቦቹን በግብርና ሥራ እየረዳ ነው የሚኖረው ፡፡በቁልፍ መረጃ አቀባይነተ እንዲመረጥ ያደረገው የብሔረሰቡ ወጣቶች ስለባህላዊ የእርቅ ስነ ስርዓቱ ያላቸውን ግንዛቤ ለመገምገምና ሥርዓቱን ቀጣይ ለማድረግ የሚያስችል እውቀት አላቸው ወይ ለስርአቱስ ቦታ ይሰጣሉ ወይ የሚለውንም ለማረጋገጥ ነው፡፡

### የመረጃ አቀባዮች ዳራ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ስም | ፆታ | የሚኖርበት አከባቢ | ስራ | እድሜ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተፈሪ ታደሰ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 35 |
| | ጌታቸው ዲምባ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | የመንግስት ሰራተኛ | 36 |
| | ሉዳይዶ ጉጋ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 65 |
| | ፈይሳ ቃዊቶ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | የቀበሌ ሊቀመንበር | 55 |
| | ገዳይቶ ከመኑ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 70 |
| | ቦጎሮ ጠሊፋ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 60 |
| | ታደሰ ጉየታ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 60 |
| | መንግስቱ ገኖ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | የመንግስት ሰራተኛ | 40 |
| | ባዩሽ አምባዬ | ሴት | ጋቶ ቀበሌ | የመንግስት ሰራተኛ | 28 |
| | ወንጀሌ ደያሳ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 42 |
| | ኩሴ ኡሽረታ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 25 |
| | አብርሃም ያየ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 28 |
| | ኩማሎ ከተማ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 20 |
| | አቡዴ በራንጉዴ | ሴት | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 60 |
| | ክፍሌ ተዋኖ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 48 |
| | ካፒኖ ሉዳይዳ | ሴት | ጋቶ ቀበሌ | ግብርና | 25 |
| | ዝናቡ ትርፌ | ወንድ | ጋቶ ቀበሌ | የመንግስት ሰራተኛ | 28 |

## ስዕላዊ መግለጫዎች




ፎቶ 2 የጥናቱ ዋነኛ ቦታ የሆነው የጋቶ ቀበሌ የሚገኝበት የደራሼ ወረዳ ካርታ



ፎቶ 3 በየቀጠናው ካሉ ሞራዎች (ሸንጎዎች)አንዱ የሆነው የቀጠና ሶስት ሞራ



ፎቶ 4 በዋናው አባዲባ የሚታዩና የቀበሌው ህዝብ ሁሉ የሚሳተፍባቸው ጉዳዮች የሚታዩበት ዋነኛው ሞራ(ቆራኦኛ)



ፎቶ 5 በእርቅ ስነስርአት ውስጥ ከእርድ ቀጥሎ መታረቅን ከሚያበስሩ ባህላዊ መጠጦች አንዱ ጨቃ ሲዘጋጅ በከፊል



ፎቶ 6 በዳይና ተበዳይ በሞራው መሃል ከአባዲባው ፊት ሲሟገቱ



ፎቶ 7 ሴቶች ከሞራው ውጭ በመሆን ሲሟገቱ



ፎቶ 8 ሽማግሌዎቹ መረጃ ሲሰጡ ከግራ ወደ ቀኝ መንግስቱ ገኖ፣ ሉዳይዶ ጉጋ ፣ገዳይቶ ካመኑ ቦጎሮ ጦሊፍ ፣ፈይሳ ቃዊቶ ፣ታደሰ ጉይታ



ፎቶ 9 አቶ መንግሰቱ ገኖ ከሽማግሌዎቹ የተገኘውን መረጃ ወደ አማርኛ

ሲተረጉሙ



ፎቶ 10 ወ/ሮ አቡዴ በራንጉዴ  ሴቶች ሞራ ቢገቡ ምን ቅጣት እንደሚጣልባቸው ሲያብራሩ



ፎቶ 11 ከስምንቱም ጎሳ መሪዎች ጋር በባህላዊ የእርቅ ስነስርአቱ ውስጥ ስለነበራቸው ሚና ውይይት ሲደረግ



ፎቶ 12 በቀጠና ዘጠኝ ሞራ የነበረን ፍትህ ሂደት በመመልከት ላይ



ፎቶ 12 ከካፒኖ ሉዳይዳ ጋር ሴቶች በባህላዊ የእርቅ ስነስርአቱ የሚሰጣቸውን ቦታ በተመለከተ የተደረገ ቃለ ምልልስ